አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

# በቦንጋ ከተማ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች አጠቃቀም እና የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም

ጌታቸው ኮቺ

ሰኔ፣ 2000
አዲስ አበባ

# በቦንጋ ከተማ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች አጠቃቀም እና የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ ጥናት
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም. ኤ. ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ

ጌታቸው ኮቺ
ሰኔ፣ 2000 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በቦንጋ ከተማ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች አጠቃቀም እና የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም

በ

ጌታቸው ኮቺ

ቋንቋ ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምሥጋና ................................................................................ i

የሠንጠረዥ ማውጫ ................................................................... ii

አጠቃሎ.................................................................................. iv

ምዕራፍ አንድ ........................................................................... 1

መግቢያ ................................................................................. 1

1.1. የጥናቱ ዳራ............................................................................ 1

1.2. የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ.................................................................. 3

1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት ........................................................................ 4

1.4. የጥናቱ ክልል.............................................................................. 5

1.5. የጥናቱ ወሰን ............................................................................ 5

1.6 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ........................................................... 5

ምዕራፍ ሁለት............................................................................ 6

ክለሳ ድርሳን ............................................................................ 6

2.1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምንነት ........................................ 6

2.1.1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለምን እንጠቀማለን?........................ 7

2.2. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዓይነትና አከፋፈላቸው.................................. 9

2.2.1. ድምፃዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ........................................ 12

2.2.2. ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች......................................... 13

2.2.3. ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች................................ 15

2.3. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥ ................................ 16

2.3.1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥ መርሖዎች ........................ 17

2.3.2. የጥሩ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ባሕሪያት ....................................... 19

2.4. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ................................. 20

2.5. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም.................................... 22

2.5.1. የትምህርት መርጃ መሣሪያን የማቅረብ (የማሳየት) መርሕ.............................. 26

2.5.2. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሥነ ልቡናዊ ሁኔታ (The Psychology of Using Teaching Aids)........................................................... 28

2.5.3. በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮች 29
2.5.4. በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ የሚደረግ ሥልጠና ..................... 32
2.6. የመማር-ማስተማርን ተግባር በማመቻቸት ረገድ የሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት ሚና.. 35
2.6.1. በሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት የሚሠጡ አገልገሎቶች ........................................ 36
2.6.2. የሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት የሚያስፈልጓቸው መሠረታዊ ነገሮች (Basic Requirements) ........................................................................................ 39
2.7. የሐገርኛ ጽሑፎች ቅኝት ........................................................................ 43
ምዕራፍ ሦስት ........................................................................................ 44
የአጠናን ዘዴ ......................................................................................... 44
3.1. የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች ............................................................. 44
3.1.1. ምልከታ ........................................................................................... 44
3.1.2. የጽሑፍ መጠይቅ ................................................................................ 45
3.1.3. ቃለመጠይቅ ...................................................................................... 45
3.2. ናሙና አመራረጥ ዘዴ ............................................................................ 45
3.2.1. የወረዳ /ከተማ አስተዳደር/ ናሙና አመራረጥ ............................................ 45
3.2.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ............................................................ 45
3.2.3 የሳይክል ናሙና አመራረጥ ...................................................................... 46
3.2.4 የትምህርት ዓይነት ናሙና አመራረጥ ........................................................ 46
3.2.5 የመምህራን ናሙና አመራረጥ .................................................................. 47
3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ ............................................................................ 47
ምዕራፍ አራት ......................................................................................... 48
የጥናቱ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ ........................................................... 48
4.1. የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎችና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ............................................................................. 48
4.1.1. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት የተደረገ ዕቅድ ................... 48
4.1.2. በዕቅዱ መሠረት የሚመረጡት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መገኛ ...... 55
4.1.3. በትምህርት ቤቶች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ሁኔታ ................ 55
4.1.4. በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ሂደት የተማሪዎች ተሳትፎ ............. 58
4.2. የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም፤ ................................... 58

4.2.1. በአገልግሎት ላይ የዋሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት ........ 61
4.2.2. የመምህራ ተኣማኒ በሆኑ የትምህርት መሣሪያዎች (Real objects) የመጠቀም ልምድ ........ 62
4.2.3. የመምህራን በዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ልምድ ........ 64
4.2.4. የመምህራን በድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣረያዎች የመጠቀም ልምድ ........ 65
4.2.5. የመምህራን በሕትመት ውጤቶች የመጠቀም ልምድ ........ 66
4.2.6. የመምህራን በተለያዩ ሠሌዳዎች የመጠቀም ልምድ ........ 68
4.3. የመምህራንን የመርጃ መሣሪያ አዘጋጃጀትና አጠቃቀም ብቃት የሚወስኑ ተላውጦዎች (Variables) ........ 69
4.3.1. ግለሰባዊ ተላውጦዎች ........ 69
4.3.2. ተቋማዊ ተላውጦዎች ........ 73
ምዕራፍ አምስት ........ 77
ማጠቃለያ እና አስተያየት ........ 77
5.1. ማጠቃለያ ........ 77
5.2. አስተያየት ........ 79
ዋቢ ጽሑፎች ........ 80
አባሪ 1. የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅጽ ........ 82
አባሪ 2. የትምህርት ቤት ሚዲያ ማዕከላት ምልከታ ቅጽ ........ 86
አባሪ 3. በመምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ ........ 89
አባሪ 4. በሚዲያ ማዕከላት ሠራተኞች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ ........ 96
አባሪ 5. ከርዕሰ መምህራን ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ ጥያቄዎች ........ 102

# ምሥጋና

በቅድሚያ አስጀምሮ ያስጨረሰኝ ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ:: በመቀጠልም ውድ ጊዜያቸውን ሠውተው ረቂቅ ጽሑፌን በማረምና አካሄዱን በማስተካከል አሁን ለደረሰበት ደረጃ ላበቁልኝ አማካሪዬ ለዶክተር አረጋ ኃይለሚካኤል ጥልቅ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ::

ይህን መርሐ ግብር ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው በአካልና በስልክ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፋቸው ላልተለየኝ ጓደኞቼ አቶ ግርማ ግዛው፣ አቶ ታደሠ የቦ እና አቶ መንበሩ መንገሻ ልባዊ ምሥጋናዬ ይድረሳቸው::

በማቴሪያልና ጠቃሚ አስተያየቶችን በመሠንዘር የዘወትር ተባባሪዬ የሆነው አቶ ዑመር ዳውድ ባለውለታዬ ነው::

ከባዱን የኑሮ ጫና ለብቻዋ በመሸከም እኔ ያለሐሳብና ጭንቀት ትምህርቴን እንድከታተል ላበረታታችኝ ባለቤቴ ወይዘሮ ወጋየሁ ወልደሰንበትና ልጆቼ ዮናስና ባምላክ ጌታቸው ለሁሉ ትዕግስታቸው ላቅ ያለ ምሥጋና ይገባቸዋል::

በመጨረሻም የጥናቱ ውጤት ቅርጽና ይዘቱ አምሮ በዚህ መልኩ እንዲወጣ ያደረገች የኮምፒዩተር ባለሙያዋ ወይዘሪት ኅብረት ኃይሉን ላመሠግናት እወዳለሁ::

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ሠንጠረዥ 1፣ በAggrwal የቀረበ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ዓይነትና አከፋፈላቸው........................................................ 10

ሠንጠረዥ 2፣ በ Nkuuhe የቀረበ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አከፋፈል........... 11

ሠንጠረዥ 3፣ አዳዲስ የትምህርት መሣሪያዎች ያላቸው መምህራን፤............... 49

ሠንጠረዥ 4፣ አዳዲስ የትምህርት መሣሪያዎች ባለመኖራቸው ምክንያት መምህራን የተጠቀሙባቸው አማራጮች፤.............................. 49

ሠንጠረዥ 5፣ በ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ የተጠቆሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር /ሁለተኛ ሴሚስተር/................................................ 50

ሠንጠረዥ 6፣ በ2000 ዓ.ም ለ2ኛ ሴሚስተር ለ3ኛ ክፍል በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር/ከታላሚ ትምህርት ቤቶች መካከል የአንዱ በናሙናነት የተወሰደ/፤ ................................................. 52

ሠንጠረዥ 7፣ በ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ የተጠቆሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር፤............ 52

ሠንጠረዥ 8፣ በ2000 ዓ.ም ለ2ኛ ሴሚስተር ለ4ኛ ክፍል በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር/ከታላሚ ትምህርት ቤቶች መካከል የአንዱ በናሙናነት የተወሰደ/፤ ................................................. 54

ሠንጠረዥ 9፣ በመምህራን የተመረቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፤ ............ 56

ሠንጠረዥ 10፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያ እንዲዘጋጅ ከመምህራን ቀርበው በሚዲያ ማዕከል የተመዘገቡ ትዕዛዞች መጠን፤............. 57

ሠንጠረዥ 11፣ ተማሪዎች በመርጃ መሣሪያዎች ዝግጅት እንዲሳተፉ በመምህራን በኩል የተደረገ ጥረት፤................................... 58

ሠንጠረዥ 12፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ ከተካሄደባቸው ሠላሳ ክፍለ ጊዜያት መካከል መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት ብዛት፤............................... 59

ሠንጠረዥ 13፣ በምልከታ ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉትን የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጥራት፤ ............................................ 60
ሠንጠረዥ 14፣ በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን /ስፋትና ጥበት/ ............... 61
ሠንጠረዥ 15፣ በምልከታ ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት፤ ....................................... 62
ሠንጠረዥ 16፣ በክፍል ምልከታ ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት ከዓይነት አንጻር ሲታይ፤......... 63
ሠንጠረዥ 17፣ በ2000 ዓ.ም. ሁለተኛ ሴሚስተር ከታላሚ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ከተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዕቅዶች ውስጥ የተጠቀሙት የትምህርት ሚዲያ ብዛት በዓይነት፤............... 64
ሠንጠረዥ 18፣ ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያን በሚመለከት ከርዕሠ መምህራን የተገኘ መረጃ፤.......................................... 66
ሠንጠረዥ 19፣ የማስተማሪያ መጻሕፍት ዕጥረትን በሚመለከት የርዕሠ መምህራን ምላሽ፤................................................................ 67
ሠንጠረዥ 20፣ የመምህራንና የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች የትምህርት ደረጃ፤... 70
ሠንጠረዥ 21፣ የመምህራንና የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች መደበኛ የሚዲያ ሥልጠና ሁኔታ፤...................................................... 70
ሠንጠረዥ 22፣ ከትምህርት መርጃ መሣሪያ ጋር በተያያዘ ለመምህራን የተሰጠ የሥራ ላይ ሥልጠና፤............................................ 71
ሠንጠረዥ 23፣ ሳምንታዊ የመምህራን የክፍለ ጊዜ ጫና፤ .............................. 72
ሠንጠረዥ 24፣ የትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ያሉበት ደረጃ፤..................... 73

# አጠቃሎ

ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሞ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ምን እንደሚመስል መፈተሽ የዚህ ጥናት ዓቢይ ትኩረት ነው:: በዚህም መሠረት በቦንጋ ከተማ በሚገኙ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ናሙናነት ጥናቱ ተካሂዷል:: የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚሰጥባቸው ሠላሳ ክፍለ ጊዜያት የተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች፣ በአምስት የተለያዩ ሚዲያ ማዕከላት የተደረጉ አምስት ምልከታዎች፣ በአሥር የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራንና በአምስት የትምህርት ቤት ሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች የተሞሉ ሁለት የተለያዩ የጽሑፍ መጠይቆች እና ለአምስቱም ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ ለጥናቱ የሚበጁ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶች ናቸው:: የጥናቱ ውጤትም እንዳመለከተው በትምህርት ቤቶቹ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች /መርሐ ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪ መጽሐፍ/ ያለመኖር፣ ትምህርት ቤቶቹ በግዥም ሆነ በስጦታ የሚያገኙት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ብዛት አነስተኛ መሆን፣ መምህራንና የማዕከል አስተባባሪዎች ቅድመ ሥልጠና እና የሥራ ላይ ሥልጠና ያለማግኘት፣ የክፍለ ጊዜ ጫና ስለሚበዛባቸው የሚዲያ ማዕከላት አገልግሎትና ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣ አብዛኞቹ መምህራን /73.3%/ ያለ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አጋዥነት ትምህርትን በቃል ብቻ ማስተማር፣ በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ከጠመኔ ሠሌዳ በስተቀር ሌሎች ሠሌዳዎች ያለመኖርና በክፍል ውስጥ የሚገኙት መርጃ መሣሪያዎች የሚሰቀሉበትና የሚለጠፉበት መታጣት፣ የሚዲያ ማዕከላቱ የሰው ኃይልና የውስጥ አደረጃጀት ተገቢነት ማጣት፣ ሚዲያ ማዕከላቱ የራሳቸው በሆነ በጀት መርሐ ግብራቸውንና ዕቅዳቸውን መፈጸም ያለመቻል በዋነኛነት የቀረቡ ድክመቶች ናቸው:: በመጨረሻም በዚህ ጥናት ውስጥ በማጠቃለያው ክፍል የቀረቡትን ድክመቶች ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሔ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል::

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በአሁኑ ጊዜ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዙሪያ ጥናት የሚያደርጉ ባለሙያዎችን የሚያስማማቸው ነገር፣ መምህራን በሚያስተምሯቸው የትምህርት ዓይነቶች የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ከተጠቀሙ ተማሪዎች ትምህርቱን ግልፅና ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ ይረዱታል የሚለው ነው:: Harmer (2001), Flanigan and Boone (1977), Aggarwal (1996), Nkuuhe (1995) የሚስማሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለውጤታማና ዘላቂ ትምህርት ወሳኝ መሆናቸውን ነው:: ከዚህም ጎን ለጎን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በትምህርት ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ፣ የመማር ፍላጎትና ተነሳሽነትን ይጨምራሉ:: ባጭሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ ከፍ የሚያደርጉ ነፃ ተላውጦዎች (independent variables) ናቸው (Amare 1995):: ከዚህ ተቃራኒ ደግሞ እጅግ የበዛ የቃል ትምህርት ወይም በቃል ብቻ ማስተማር ተማሪዎች የቃላትን ወይም የዕውነትን ዓለም ተጨባጭ ትርጉም ሳይረዱ እንዲሁ ብቻ እንዲሸመድዱ ይገደዳሉ:: ይህ ማለት ደግሞ ተጨባጭነት የሌለው ረቂቅ ትምህርት መሆኑ ነው:: በመሆኑም በመናገር ብቻ ማስተማር፣ በማዳመጥ ብቻ መማር፣ በተማሪዎች ላይ ቀስ በቀስ የሚያመጣው ውጤት የተዛባ ወይም ያልተሟላ ግንዛቤን የሚያስጨብጡ ይሆናል:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ የተማረ ተማሪ የቃላትን ተጨባጭ ትርጉምና አጠቃቀም የሚያውቅ ሳይሆን፣ የቃላት ስብስብ ብቻ ሸምድዶ የወጣ ነው የሚሆነው:: እንደዚሁም ደግሞ ተማሪዎች አንድን ነገር በማየት፣ በመስማት፣ በመዳሰስ፣ በመፈተሽ፣ በመሞከር እና በመሥራት እንዲማሩ ካልተደረገ፣ በአዕምሯቸው ውስጥ ተቀርፆ የሚቀር የግንዛቤ መጠን ይቀንስና የመርሳት ወይም ያለማስተዋል ሁኔታ ይጨምራል (Betsate 2000:2):: እኚሁ ምሁር Nacino-Brown (1982)ን ጠቅሰው እንደሚያብራሩት፣ የመምህራን የድምፃዊ ወዕይታዊ መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ዝቅተኛ መሆን፣ የተማሪዎችን የማስታወስ መጠን ይቀንሳል::

ስለዚህ ቃላዊና ረቂቅ ብቻ የሆነ የመማር-ማስተማር ሂደት ውጤቱ በቂ ዕውቀትና ክሂሎት የሌለውን ተማሪ ማፍራት ይሆናል:: ባጠቃላይ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአጥጋቢ ሁኔታ መጠቀም የትምህርት ጥራትን ከፍ ያደርጋል:: በአንፃሩ ደግሞ ያለትምህርት መርጃ መሣሪያ ማስተማር/መማር ለትምህርት ጥራት መሽቆልቆል ትልቅ አስተዋጽኦ አለው::

ቋንቋ ውስብስብና ረቂቅ የሆነ የመግባቢያ መሣሪያ ነው:: በተለይም አፋቸውን በቋንቋው ላልፈቱ ጀማሪ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ውስብስብነቱና ረቂቅነቱ እጅግ የበዛ ነው የሚሆነው:: በመሆኑም በመማር-ማስተማር ሂደት እነሱንም ሆነ መምህራንን እየተፈታተነ ያለው ትልቁ ችግር በዚህ ውስብስብና ረቂቅ ነገር መግባባትና መረዳዳት ያለመቻል ጉዳይ ነው:: ይህን ችግር ለመቅረፍ ከሚወሰዱት ርምጃዎች አንዱና ምናልባትም ዋነኛው በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ከረቂቅነትና ውስብስብነት ወደ ተጨባጭነትና ግልፅነት አቅልሎ ማቅረብ ነው::

በዓለም ላይ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጀማመር በተመለከተ ከቋንቋ ትምህርት መጀመር ጋር ተመሳሳይ ዕድሜ እንዳለው ይታመናል (Wookock, (nd) የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በልማዳዊውም ሆነ በዘመናዊው የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ መጠናቸው ይነስም ይብዛም አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ እስካሁንም በመስጠት ላይ ይገኛሉ:: ለምሳሌ በልማዳዊው የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት መጻሕፍት፣ የተፈጥሮ ቀለምንና መቃ ብዕርን መጥቀስ ይቻላል:: በዘመናዊው የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥም ቢሆን የመማሪያ መጻሕፍት፣ ጠመኔ፣ ሠሌዳ እና ሬዲዮ ክብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ናቸው:: የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ - ትምህርት ተነድፎለት ከወጣበት ከ1944 ዓ.ም (ትምህርት ሚኒስቴር 1984 ዓ.ም.) ጀምሮ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከላይ በተገለፀው መልኩ በመጠኑም ቢሆን ለቋንቋው ትምህርት መጠናከር አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ:: ከዚህ ከዘመናዊው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጀማመር ሳንወጣ ሬዲዮ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በትምህርት መገናኛ ዘዴነት አገልግሎት መስጠት የጀመረው ወደ ሃምሳ አርባ ስምንት ዓመት አካባቢ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በማሰራጨት ነው (ጌታቸው ለገሰ፣ 1992)::

በአሁኑ ጊዜ ይበልጥ ተፈላጊና ውጤታማ በሆነው ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብና ዘዴዎች መሠረት በተለይ ለሁለተኛ ቋንቋ ጀማሪ ተማሪዎች በተለያዩ ተገቢነትና ተዛማጅነት ባላቸው የድምፃዊ ወዕይታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ የመማር-ማስተማሩን ሂደት ማቀላጠፍ ቸል የማይባል ጉዳይ ነው (Harmer, 2001፡12፣ Aggarwal, 1996፡253)::

ጥናቱ የሚካሄድበት ቦንጋ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ሥር ከሚገኙት ዞኖች አንዱ የሆነው የካፋ ዞን ዋና ከተማ ስትሆን፣ በውስጧ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ:: በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ትምህርት የሚሰጠው በአፍ መፍቻ (ካፍኛ) ቋንቋ ሲሆን፣ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጠው ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ ነው:: የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት አጥኚው የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህር ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ሠልጣኝ መምህራንን ለፕራክቲከም ልምምድ ወደ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ሲወስዳቸው እግረመንገዱን በትምህርት ቤቶቹ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሠጣጥ ሂደት በመርጃ መሣሪያዎች ያመደገፍ ችግሮችን በማስተዋሉ ነው:: በመሆኑም የዚህ ጥናት ዐቢይ ትኩረት በቦንጋ ከተማ ውስጥ በሚገኙ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች አጠቃቀም እና የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀምን ተገቢነትና ተዛማጅነት በጥናቱ አማካይነት ማወቅ ነው::

## 1.2. የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ በቦንጋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀምን በተመለከተ በተጨባጭ ተግባራዊ መሆን አለመሆኑን መፈተሽ ነው::

በዚህ አጠቃላይ ዓላማ ላይ በመመሥረትም ጥናቱ በሂደት ለሚከተሉት የጥናቱ ቁልፍ ጥያቄዎች መልስ ለመሻት ይሞክራል፤

1. መምህራኑ በቋንቋ መርሐ ትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዕለታዊ የትምህርት ዕቅዳቸው ውስጥ ያካትታሉ?

2. መምህራኑ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት፣ ለመጠቀም፣ ባጠቃላይም በክፍል ውስጥ መማር-ማተማር ሂደት ውስጥ በተገቢ ሁኔታ በአገልግሎት ላይ ለማዋል ያላቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት ምን ያህል ነው?
3. መምህራኑ በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ላይ የአቅም ግንባታ ሥልጠና አግኝተዋል?
4. በትምህርት ቤቶች የተደራጁ የትምህርት ሚዲያ ማዕከላት (School Pedagogical Centers) አሉ? ካሉስ አገልግሎታቸው እስከምን ደረጃ ድረስ ነው?
5. እነዚህ የትምህርት ቤት የትምህርት ሚዲያ ማዕከላት ተገቢ አገልግሎት ለመስጠት ይችሉ ዘንድ የተደረገላቸው የአደረጃጀት ዕገዛ (በፋይናንስ፣ በማቴሪያል፣ በሰው ኃይል፣ በተሳትፎ፣ ወዘተ.) ምን ይመስላል?

ለእነዚህ የጥናቱ ቁልፍ ጥያቄዎች የሚገኙት መልሶች የጥናቱን ዓላማ ያሳካሉ ተብሎ ይታመናል::

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ የሚከተሉትን ጥቅሞች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፤

1. ከጥናቱ ውጤትና ከሚሰጡት አስተያየቶችና የመፍትሔ ሐሳቦች በመነሳት በከተማው በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን የሚሰጠውን የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በመርጃ መሣሪያ በመጠቀም ማስተማር ጥ⁄ ቱን ለማሻሻል እንደሚረዳ ፍንጭ ይሰጣል::

2. ለከተማው አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤት የትምህርት ባለሙያዎች፣ ለትምህርት ቤት ኃላፊዎችና ለመምህራን በጥናቱ ውጤትና በጥናቱ መጨረሻ በሚሰነዘሩ አስተያየቶችና የመፍትሔ ሐሳቦች በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ረገድ ጠቃሚ ሐሳቦችን ይጠቁማል::

3. በዚህና በተዛማጅ ርዕስ ዙሪያ ወደፊት ሰፊ ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኚዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ እንደመነሻ ሐሳብ በመሆን ያገለግላል:: በአጠቃላይ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ላይ ጥናት ለሚያካሂዱ ምሁራን የበኩሉን መረጃ ይሰጣል፤ ለውይይትም መነሻ ይሆናል::

## 1.4. የጥናቱ ክልል

ጥናቱ የተካሄደው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ሥር ከሚገኙ ዞኖች አንዱ በሆነው በካፋ ዞን ርዕሰ ከተማ በቦንጋ ውስጥ በሚገኙ አምስት የመንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው:: ትምህርት ቤቶቹም ግራዝማች ጳውሎስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ባርታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ባንዲራ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ሸታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ካያኬላ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው::

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በቦንጋ ከተማ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ላይ ብቻ ያተኩራል:: ከዚህ ውጪ በሌሎች የትምህርት ዓይነቶች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀምም ሆነ አማርኛን በአፍ መፍቻነት የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶችን ጥናቱ አያካትትም::

## 1.6 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ

1. Sound Distribution System Sets- የድምፅ ማሠራጫ ዘዴዎች
2. Drawings - ንድፎች
3. Flannel Board – ከወፍራም ሱፍ ጨርቅ የተሠራ ሠሌዳ
4. Magnetic Board - መግነጢሳዊ ሠሌዳ
5. Visuals - ዕይታውያን
6. Audio Visual Aids - ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች
7. Flip Charts - ተሰቃይ ወረቀቶች
8. Motivation - ተነሳሶት

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

## 2.1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምንነት

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የተለያዩ ምሑራን የተለያየ ስያሜ ቃል (Terminology) በመስጠት ይጠሯቸዋል:: መርጃ መሣሪያዎች፣ የማስተማሪያ ሚዲያዎች፣ ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ የመማሪያ ምንጮች (learning resources) የሚሉት ስያሜዎች ለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተሰጡ የተለያዩ ስያሜ ቃላት ናቸው:: Aggarwal (1996፣157)፣ Quist (2000፣27)፣ Nkuuhe (2000፣224)፣ Harrison (1958፣58) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ምንነት Teach your Best (2000) በሚለው መጽሐፍ ውስጥ "የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በተለያዩ መንገዶች ሊተረጎም ይችላል Johnson Nkuuhe በማለት ይገልጻሉ:: የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሲባል በየትኛውም ደረጃ በሁሉም የትምህርት መስኮችና የትምህርት ዓይነቶች በመምህራንና በተማሪዎች ዘንድ ለመማር-ማስተማር ተግባር የሚውሉትን ጽንሠ ሐሳቦች ሁሉ ይመለከታል::" Nkuuhe (2000፣224) በማለት ይገልጻሉ:: እኚሁ ምሑር አያይዘውም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሲባል የሕትመት ውጤቶችን፣ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን፣ ምሥሎችን፣ ሞዴሎችን፣ ዕውነተኛ ነገሮችን (real objects)፣ የተለያዩ ሠሌዳዎችን ባጠቃላይም ለመማር ማስተማር ሂደት የትምህርትን ዝርዝርና አጠቃላይ ዓላማ ከግብ ለማድረስና የትምህርት ይዘትን በተጨባጭ ለማብራራት አገልግሎት የሚሰጡ የትምህርት አጋዥ መሣሪያዎች (devices) መሆናቸውንም ያስረዳሉ::

Heinich et al. (1996:8) በበኩላቸው ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምንነት እንደሚከተለው ይበይናሉ:: "የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተማሪዎች ትምህርታዊ ይዘቶችን /ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት/ ከተለያዩ ምንጮች እንዲይዙ የሚያግዙና ትምህርታዊ ዓላማዎችን እውን የሚያደርጉ መሣሪያዎች ወይም ቁሳዊ አካላት ናቸው::" ከኢንተርኔት የተገኘው መረጃ ደግሞ ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምንነት እንደሚከተለው ይገልጻል::

- ተማሪዎች የንባብና ሌሎች ክሂሎትን እንዲያሻሽሉ የሚረዳ፣

- አንድን ክሂል፣ ሃቅ ወይም ሐሳብ የሚያጎላና የሚያዳብር
- በተማሪዎች ትምህርት አቀባበል ላይ ፍርሃትን፣ ጭንቀትን ወይም መረበሽን የሚያስወግድ ነው::" (Wookock (nd)

### 2.1.1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለምን እንጠቀማለን?

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ጠቀሜታ በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ አስተያየት ሰጥተዋል:: ከእነዚህም መካከል Harmer (2001፣134) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለሁለት ምክንያቶች ያገለግላሉ፤ አንድም ለተግባራዊ ልምምድ፣ አንድም የተማሪን የትምህርት ፍላጎት ለማነሳሳት፤ በማለት አስፈላጊነቱን ሲገልፁ፣ Nkuuhe (2000፣225) በበኩላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ጠቀሜታ ከሥነ-ትምህርታዊ ሥነ-ልቡና (Educational Psychology) ሳይንስ አንፃር እያንዳንዱ ሰው መማር የሚችለው በስሜት ሕዋሳቱ ማለትም በጆሮዎቹ፣ በዓይኖቹ፣ በአፍንጫው፣ በአፉ፣ በምላሱ፣ በእጆቹ እና በቆዳው አማካኝነት የተለያዩ መረጃዎችን መሰብሰብ ወይም ማግኘት ሲችል እንደሆነ ይገልጻሉ::

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በቃላዊ ትርጉም ብቻ ቢገለፁ ለመረዳት እጅግ አስቸጋሪ የሚሆኑትን ዕንስ ሐሳቦች እንደየተገቢነታቸው በመወከል ተማሪዎች የመማር ልምዶችን በቀላሉ እንዲያካብቱና እንዲያጎለብቱ የሚያደርጉ፣ መምህራንም ረቂቅ የሆኑ ንድፈ ሐሳባዊ የትምህርት ይዘቶችን በተጨባጭና እሙናዊ በሆነ መልኩ እንዲያቀርቡ የሚረዳቸው መሆኑን Quist (2000፣104) ያስረዳሉ:: በምንናገርበት ጊዜ ለንግግር ተግባር የምናውላቸው ቃላት ነገሮችን የሚወክሉ ረቂቅ ዘልማዳዊ ምልክቶች ናቸው፤ በመርጃ መሣሪያዎች በተለይም በዕይታዊ መርጃ መሣሪያዎች በማስደገፍ የምንናገራቸው ቃላት ግን የቃላቱን ትርጉም ይበልጥ ተጨባጭ በማድረግ ለግንዛቤ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ::

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ጠቀሜታዎች Nkuuhe (2000፣226) እንደሚከተለው በነጥብ በነጥብ ይዘረዝራሉ::

- የአንድን ድርጊት ወይም የአንድን ነገር ቅደም ተከተላዊ ሂደት (Procedure) ምስያ (reproduction) በቀላሉ እንዲደጋገም ያደርጋሉ::
- አንድ ሂደት ወይም አንድ ቴክኒክ በተጨባጭ እንዲታይ ዕድል ይሰጣሉ::

- በአንድ ውስን አካል ወይም ቡድን የተደረገ ወይም የተሠራ ልምድ በርካታ ቁጥር ባላቸው ተማሪዎች በቀላሉ እንዲታይ ወይም እንዲደመጥ የጋራ ማዕቀፍ ይፈጥራሉ::
- የዕውነታን የትርጉም ግርታ ያስወግዳሉ::
- የተማሪዎችን ትኩረት በመሳብ የትምህርት ፍላጎትን ያነሳሳሉ::
- በዋና ዋና የትምህርት ይዘቶች ወይም ቁልፍ ሐሳቦች ላይ ትኩረት እንዲደረግ የማድረግ ኃይል አላቸው::
- ለቃላዊ ትርጉም ፍለጋና ለማንዛቤውም የሚጠፋውን ጊዜ ይቆጥባሉ::
- የተማሪዎችንና የመምህራንን የፈጠራ አድማስ ያሰፋሉ::
- ረቂቅ ፅንሰ ሐሳቦችን በቀላሉ ለመረዳት ያግዛሉ::

በተመሳሳይ ሁኔታም የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተለይም ዕይታዊ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የመገልገል ጠቀሜታዎችን በተመለከተ Bowen (1982፣1) የሚከተሉትን ነጥቦች ይጠቅሳሉ::

- የቋንቋ ትምህርትን በጥልቀትና በስፋት የማስተላለፍን ዕድገት ያፋጥናሉ::
- ተማሪዎች ዓይኖቻቸውን ከመማሪያ መጽሐፋቸው ቀላልና ተፈጥሯዊ ወደሆነውና አንዱን ከሌላው ጋር ሲያነጋግር ወደሚችለው ነገር እንዲያማትሩ ያግዟቸዋል:: በሌላ አነጋገር ተማሪዎች ከመማሪያ መጽሐፍ በተጨማሪ በሌሎች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ይወያዩበታል::
- በቃላዊ ትምህርት ላይ ብቻ የሚያተኩረውን የመምህሩን የንግግር ጊዜ በመቀነስ የተማሪዎችን ተሳትፎ እንዲጨምር ያደርጋሉ::
- በሚታዩ ምሥሎች አማካኝነት ከክፍል ውጪ ባሉ ውጫዊ ዓለም ተጨባጭ ነገሮች ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩ የማድረግ ፋይዳ አላቸው::
- ቶሎ ሊረሱ የሚችሉትን ረቂቅ የሆኑ አስተሳሰቦችን፣ የነገሮችን እንቅስቃሴ፣ የነገሮችን ስፋት፣ ጥልቀት፣ ክብደት፣ ጠረን፣ ጣዕም፣ ስሜት፣ ቀለም፣ ጊዜ እና የመሳሰሉትን

ለግንዛቤ አስቸጋሪ የሚሆኑትን በግልፅና በተጨባጭ ከማስረዳት አኳያ ጠቀሜታ አላቸው::

- አንድ ተማሪ አንድን አዲስ ቋንቋ (ቃል) ከመማሪያ መጽሐፍ ወይም ከመዝገበ ቃላት ለመማር ይከብደው የነበረውን፣ በፈጠራዊ ምናቡ አማካኝነት በቀላሉና በሚያስደስት አኳኋን በሥዕሎች በመታገዝ መማር ይችላል::
- የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብን ቀላልና ተፈጥሯዊ የማድረግ ፋይዳ አላቸው::
- መምህሩ አራቱን የቋንቋ ክሂሎት (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መፃፍን) በተናጠልና በቅንጅት ለማስተማር ይችል ዘንድ ያግዙታል::
- በተማሪዎችና በመምህሩ መካከል የሚካሄዱትን ክርክሮች፣ ውይይቶች፣ ገለፃዎች፣ አስተያየቶች፣ ግምታዊ ሐሳቦች፣ ወዘተ. ከምናባዊነት ይልቅ ተጨባጭነት እንዲኖራቸው በማድረግ ምልልሶቹ በተጨባጭ ዕውነታዎች ወይም መረጃዎች እንዲጠናከሩ ያደርጋሉ::
- በሁሉም የትምህርት እርከኖች የቋንቋ ብቃትን ያጎናፅፋሉ፤ መርጃ መሣሪያዎች ለየትኛውም የትምህርትና የዕድሜ ደረጃ አገልግሎት ይሰጣሉ::

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ዓይነትና አከፋፈል እንመለከታለን::

## 2.2. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዓይነትና አከፋፈላቸው

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በተናጠል ሲታዩ ቁጥራቸው ብዙ ነው:: በመስኩ ጥናት ያደረጉት ምሁራን እነዚህን በርካታ ቁጥር ያላቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደየተቀራራቢነታቸውና እንደየአገልግሎታቸው በማቧደን በውስን ምድቦች ይከፍሏቸዋል:: በዚህ ሁኔታ ሁለት ዓይነት አከፋፈሎች አሉ:: የመጀመሪያው የAggarwal (1996፣161) አከፋፈል ሲሆን ይህንንም እንደሚከተለው እንመለከታለን:: Aggarwal የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የሚደመጡ መሣሪያዎች (Audio materials)፣ የሚታዩ መሣሪያዎች (Visual Materials) እና ድምፃዊ ወዕይታዊ መሣሪያዎች (Audiovisual Materials) በማለት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፍሏቸዋል::

ሠንጠረዥ 1፣ በAggaraal የቀረበ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ዓይነትና አከፋፈላቸው፤

| ተ.ቁ | የሚደመጡ መሣሪያዎች | ተ.ቁ | የሚታዩ መሣሪያዎች | ተ.ቁ | የሚደመጡና የሚታዩ መሣሪያዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሬዲዮ | 1 | ማስታወቂያ ሠሌዳዎች | 1 | ለዕይታ የቀረቡ መረጃዎች |
| 2. | የድምፅ ማሠራጫ ዘዴዎች | 2 | ጠመኔ ሠሌዳዎች | 2 | ፊልሞች |
| 3. | ቴፕና ዲስክ መቅጃዎች | 3 | ቻርቶች | 3 | ከተቀዳ ድምፅ ጋር የተቀረፁ ውጤቶች |
| | | 4 | ንድፎች | 4 | የድምፅ ፊልም ስትሪፖች |
| | | 5 | ለዕይታ የሚቀርቡ ነገሮች | 5 | ጥናታዊ ጉዞ |
| | | 6 | ፊልም ስትሪፖች | 6 | ቴሌቪዥን |
| | | 7 | ፍላሽ ካርዶች | 7 | ቪዲዮ ቴፖች |
| | | 8 | ከወፍራም ሱፍ ጨርቅ የተሠሩ ሠሌዳዎች | | |
| | | 9 | በፍጥነት የሚገለጡ መጻሕፍት | | |
| | | 10 | በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መጻሕፍት | | |
| | | 11 | መግነጢሳዊ ሠሌዳዎች | | |
| | | 12 | ካርታዎች | | |
| | | 13 | ሞዴሎች | | |
| | | 14 | ሥዕሎች | | |
| | | 15 | ፎቶግራፎች | | |
| | | 16 | ፓስተሮች | | |
| | | 17 | ድምፅ አልባ ፊልሞች | | |
| | | 18 | ስላይዶች | | |

ምንጭ:- Aggarwal (1996:161)

በዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ እንደምንመለከተው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በሦስት ዋና ዋና ምድቦች ሥር ማለትም ድምፃቸው በጆሮ ብቻ የሚደመጡትን ለብቻ በመለየት የሚደመጡ መሣሪያዎች በማለት፣ ገፅታቸው በዓይን ብቻ የሚታዩትን በመለየት ደግሞ ዕይታዊ መሣሪያዎች በማለት፣ እንደዚሁም ደግሞ ድምፃቸው እየተሰማም ገፅታቸው በዓይንም የሚታዩትን መርጃዎች በመለየት የሚደመጡና የሚታዩ መሣሪያዎች በማለት ከሞላ-ጎደል ተዘርዝረዋል:: ምናልባት በዚህ ክፍፍል ዝርዝር ውስጥ ያልተጠቀሱት ቢኖሩ እንኳ እንደየባሕሪያቸው ከሦስቱ ምድቦች ውስጥ በአንደኛው ሥር መመደብ ይቻላል:: ይኸውም መርጃ መሣሪያው በጆሮ ብቻ የሚደመጥ ከሆነ በድምፃዊ መሣሪያ ምድብ ሥር፣ መርጃ መሣሪያው በዓይን ብቻ የሚታይ ከሆነ በዕይታዊ መሣሪያ ምድብ ሥር፣ ወይም ደግሞ መርጃ መሣሪያው በጆሮም የሚደመጥ በዓይንም የሚታይ ከሆነ በድምፃዊ ወዕይታዊ ምድብ ሥር መመደብ ይቻላል:: ለምሳሌ "ከበሮ"ን ብንወስድ በዚህ ሰንጠረዥ ውስጥ ከተዘረዘሩት የትምህርት

መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር ውስጥ አልተካተተም:: ነገር ግን ከበሮን እንደ አንድ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ብንቆጥርና "በዬትኛው ምድብ ሥር ይካተት?" የሚል ጥያቄ ቢያስነሳ ያለምንም ጥርጥር በድምፃዊ ወዕይታዊ ምድብ ሥር ማስቀመጥ ይቻላል ማለት ነው፤ ምክንያቱም ከበሮ፣ ድምፁ በጆሮ ይሰማል፤ ገጽታውም በዓይን ይታያልና::

የትምህርት መርጃ መሣሪያ አከፋፈልን በተመለከተ ደግሞ Nkuuhe (2000:225) እንደሚከተለው በአምስት ምድቦች ሥር ይሸነሽኗቸዋል፤

ሠንጠረዥ 2፣ በ Nkuuhe የቀረበ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አከፋፈል፤

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የታተሙ | በራሪ ወረቀቶች፣ ማስታወሻዎች፣ የማጥኛ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎች |
| 2 | ዕይታውያን | ቻርቶች፣ ዕውነተኛ ነገሮች፣ ፎቶግራፎች፣ ብርሃን አስተላላፊዎች |
| 3 | ድምፃዊ ወዕይታውያን | ስላይዶች፣ ቴፖች፣ ፊልሞች፣ ፊልም ስትሪፖች፣ ቪዲዮ፣ መልቲ ሚዲያዎች |
| 4 | የማይንቀሳቀሱ | ሠሌዳ፣ ማስቀመጫዎች ፣ ተሰቃይ ወረቀቶች ፣ ሻሸ ሠሌዳዎች ፣ መግነጢሳዊ ሠሌዳዎች |
| 5 | ኤሌክትሮኒክስ | ሬዲዮ፣ ኮምፒዩተር፣ የኤሌክተሮኒክስ መልዕክት መቀበያዎች፣ መልቲ ሚዲያዎች |

የሁለቱን ምሑራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመዳደብ በምንመለከትበት ጊዜ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይነት እንዳላቸው እንገነዘባለን:: ለምሳሌ Nkuuhe በተራ ቁጥር 1 ያስቀመጡት "የታተሙ" በሚለው ምድብ ሥር የተዘረዘሩት መርጃ መሣሪያዎች (በራሪ ወረቀቶች፣ ማስታወሻዎች፣ የማጥኛ መመሪያዎች ማንዋሎች፣) እንደዚሁም በተራ ቁጠር 4 ሥር የተዘረዘሩት ሠሌዳ፣ ማስቀመጫዎች (display easels)፣ ፍሊፕ ቻርቶች፣ ሻሸ ቦርድ፣ እና መግነጢሳዊ ሠሌዳ አንድ ላይ በመጠቃለል Aggarwal የሚታዩ መሣሪያዎች ብሎ ባስቀመጡት ምድብ ሥር ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው:: እንደዚሁም Nkuuhe "ኤሌክትሮኒክስ" በማለት በተራ ቁጥር 5 ሥር ያስቀመጡዋቸውን ሬዲዮ፣ ኮምፒዩተር፣ ወዘተ. እንደየባሕሪያቸው በድምፃዊ እና በድምፃዊ ወዕይታዊ ምድቦች ሥር በመመደብ ከAggrarwal አመዳደብ ጋር ማስማማት ይቻላል:: በመሆኑም ከዚህ አሳማኝ ሁኔታ በመነሳት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን

አከፋፈል በAggarwal (1996) መሠረት በሦስት ምድቦች ማለትም፣ ድምፃዊ፣ ዕይታዊ እና ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በማለት ከፍለን እያንዳንዳቸውን በተናጠል ለማብራራት እንሞክራለን::

### 2.2.1. ድምፃዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

ከዚህ በላይ በቀረበው ማብራሪያ በተለይም በAggarwal (1996) በቀረበው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምደባ መሰረት በድምፃዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምድብ ሥር የተመደቡት የቋንቋ ቤተ-ሙከራ፣ ሬዲዮ፣ የድምፅ ማሠራጫ ዘዴዎች ቴፕና ዲስክ መቅጃዎች እና የመሳሰሉት ድምፃቸው በጆሮ ብቻ የሚደመጡት ናቸው:: የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዋና ዓላማ አራቱን የቋንቋ ክሂሎት ማዳበርና በመማር ሂደት ውስጥ ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብን ማቀላጠፍ ነው:: ከዚህ አንፃር ድምፃዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎት በተለይም የማዳመጥንና የመናገርን ክሂሎት በማጎልበት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተናጋሪዎች የተቀዱትን ወይም የተቀረፁትን ንግግሮች በማዳመጥና አስመስለውም እንዲናገሩ በማገዝ የላቀ ሚና ይጫወታሉ:: በተለይም ሬዲዮና ቴፕሪኮርደር፣ ኤሌክትሪክ ባልደረሰባቸው የኢትዮጵያ ገጠር አንደኛ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ድረስ ዘልቆ በመግባት በባትሪ ድንጋይና በሶላር ሲስተም እየታገዙ ለገጠሩ ተማሪ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎትን ማስጨበጫ ትምህርት ሂደት ውስጥ ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረጉ እንዳሉ ይታወቃል:: (ጌታቸው ለገሰ 1992)

በአብዛኛው የኢትዮጵያ ገጠር ትምህርት ቤቶች በተለይም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ጀማሪ ተማሪዎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ናቸው:: የአንደኛ ደረጃ መምህራንም በየአካባቢያቸው ተምረውና ሠልጥነው በምደባም ይሁን በዝውውር ወደየአካባቢያቸው በመመለስ በማስተማሩ ሥራ የተሰማሩና አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ናቸው:: በመሆኑም አማርኛን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በመምህሩም ሆነ በተማሪዎች ተግባቦታዊ የንግግር ልውውጥ ሂደት ሲፈጠር (ሲከሰት) የሚችለውን የንበት፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የዓረፍተ ነገር አገነባብና የሐሳብ አገላለፅ ችግሮችን በመቅረፍ፣ ወደ ትክክለኛው ንበትና አነጋገር እንዲመጡ ለማድረግ ድምፃዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው::

### 2.2.2. ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

ቋንቋ በትምህርትነት መሰጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የቋንቋ ትምህርትን በማገዝ ረገድ ቀዳሚውን ሥፍራ እንደሚይዙ በርካታ ጥናቶች Wright (1989)፣ Bowen (1982) እና Aggrwal (1996) ያመላክታሉ::

ከ1466-1536 የኖረውና የደች ተወላጅ የሆነው የሰብአዊ መብት ተሟጋችና ጸሐፊ Desiderious Erasmus በዘመኑ የነበረውን ቃላዊና በሽምደዳ ላይ ብቻ ያተኮረ የትምህርት አሰጣጥን በመቃወም ሕፃናት በሥዕሎችና በሌሎች ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ መማር እንዳለባቸው በይፋ ማወጁን Aggarwal (1996፣152) ይገልጻሉ:: እንደዚሁም Aggarwal በዚህ ዳሰሳ ጥናታቸው Jhon Amos Comenius (1592-1670) የተባሉ ምሑር "Sensulium Pictus" በእንግሊዝኛ ትርጉሙ "The World Sense Objects) በመባል የሚታወቅና 150 ሥዕሎችን ያካተተ የመማሪያ መፅሀፍ እንዳዘጋጁና ስዕሎቹም በዕለት ተዕለት የሕይወት እንቅስቃሴ ላይ ያተኮሩ እንደነበሩ፣ መጽሐፉ በሕፃናት ትምህርት የመጀመሪያው በሥዕል የተደገፈ የሕፃናት መማሪያ መጽሐፍ ተደርጎ ሲቆጠር እንደሚችልና መጽሐፉም በመላው ዓለም በሚገኙ የሕፃናት የትምህርት ማዕከላት ዘንድ ሰፊ ሥርጭትና አገልግሎት እንደሰጠ አበክረው ይገልጻሉ:: ሥዕላዊ የመማሪያ መጻሕፍትን በተመለከተ Nunan (1998፣136) የሚከተለውን ይላሉ፤

> ሥዕላዊ መግለጫዎች (illustration)... ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ የተማሪን ስሜትና ፍላጎት ከመቀስቀስ ባሻገር የቋንቋውን መድበለ - ቃላት ዕውቀቱን ከማጎልበትና በቃላቱ ሃረጋትንና ዐረፍተ- ነገሮችን ከመመሥረት አንፃር ጥሩ ልምምድ እንዲያደርግ ያስችሉታል::

በማለት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ በሥዕል የተደገፉ የመማሪያ መጻሕፍት የሚኖራቸውን ሚና ይገልጻሉ:: በተመሳሳይ ሁኔታም ዕይታዊ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አገልግሎት በተመለከተ Bowen (1982፣iv) "መማር ውስብስብ ሂደት ነው፤ እናም ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሁለተኛ/ የውጪ ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ ትልቅ የማነቃቂያ ዕገዛ ያደርጋሉ::" በማለት ይገልጻሉ:: ዕይታዊ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አገልግሎት ተማሪዎችን ማነቃቃት ወይም የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት ማነሳሳት ብቻ ሳይሆን፣ የትምህርትን ይዘት በቀላሉና በተጨባጭ እንዲገነዘቡ

የሚያግዟቸውም ጭምር መሆናቸውን ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ከ(Nunan፣1998) ሐሳብ መረዳት ይቻላል::

ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በሁሉም የትምህርት ዕርከኖች ለሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች የሚያገለግሉ ቢሆኑም፣ በተለይም ለአንደኛ ደረጃ አንደኛ ሳይክል የቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን አቅልሎና ተጨባጭ በሆነ መልኩ በማቅረብ ሂደት ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጿል:: ከዚህ አንፃር Bowen (1982፣ 13-74) ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እንደየአገልግሎታቸውና የሥራ ባሕሪያቸው በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፍሏቸዋል:: እነዚህም ሥዕሎች፣ ሠሌዳዎችና ፕሮጀክተሮች ሲሆኑ፣ በእያንዳንዳቸው ሥርም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደተካተቱ ከላይ የተጠቀሱት ምሁር ጥናት ያመለክታል:: በዚህም መሠረት፡-

- ሥዕሎች በሚለው ዋና ክፍል (ምድብ) ሥር:-
  - የግድግዳ ሥዕሎችና የግድግዳ ቻርቶች
  - ተከታታይ ሥዕሎች
  - ፍላሽ ካርዶች
    - የቃላት ፍላሽ ካርዶች
    - የሥዕል ፍላሽ ካርዶች
    - የሥራ ካርዶችና የሥራ ወረቀቶች
- ሠሌዳዎች በሚለው ሥር:-
  - የጠመኔ ሠሌዳዎችና ነጭ ሠሌዳዎች
  - የማሳያ ሠሌዳዎች
  - ከወፍራም ሱፍ ጨርቅ የተሠራ ሠሌዳ
  - መግነጢሳዊ ሠሌዳ
- ፕሮጀክተሮች በሚለው ሥር:-
  - ከአናት በላይ ፕሮጀክተሮች
  - ስላይድ ፕሮጀክተሮች
  - ሌሎች ፕሮጀክተሮች ናቸው::

ከዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል አብዛኞቹ ለቋንቋ ትምህርት መማር ተግባር መቀላጠፍ፣ በተለይም በቀላሉ ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ፣ በርካሽ ዋጋ እንደልብ ለማግኘትና ለመሥራት የሚቻሉ የመሆናቸው ጉዳይ ከጠቃሚ ጎን የሚመዘገብ ሲሆን፣ እንደ ፕሮጀክተሮችና አንዳንድ ሠሌዳዎች የመሳሰሉት ጥቂቶች ደግሞ በተቃራኒ ወገን የመመደቡ ጉዳይ ደግሞ የዕይታዊ መርጃ መሣሪያዎች ጎጂ ጎን ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተመለከተ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በሌሎች ንዑሳን ምዕራፎች ውስጥ የተነሳ በመሆኑ ቀጥሎ ወደሚነሳው ድምፃዊ ወዕይታዊ መሣሪያ እናልፋለን፤

2.2.3. ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

ድምፃዊ ወዕይታዊ መርጃ መሣሪያዎች ቃሉ እንደሚያመለክተው ድምፅንና ምሥልን አካትተው በመያዝ በመማር ሂደት ውስጥ ተማሪው በአንድ ጊዜ የአንድን ነገር ምሥል በዓይኑ እያየ ድምፁንም እየሰማ መማር እንዲችል የሚያግዙ መርጃ መሣሪያዎች ናቸው:: Aggarwal (1996፣153) ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ምንነት በስፋት ለመግለፅ ሞክረዋል:: ከእኚህ ምሑር ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው ድምፃዊ ወዕይታዊ መርጃ መሣሪያዎች የትምህርት ይዘቶችን ይበልጥ ግልፅ እንዲያደርጉ፣ ይበልጥ እንዲያረጋግጡ፣ የትክክለኛ ግንዛቤዎች፣ ትርጉሞችና አድናቆቶች ተዛምዶና ተዋሕዶ መኖራቸውን እንዲለይ የሚያግዙት ተጨማሪ መሣሪያዎች ናቸው:: እንደዚሁም ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መምህሩ የመማር ሂደቱን የበለጥ ተጨባጭ፣ ውጤታማ፣ አስደሳች፣ ትርጉም ያለውና የሚታይ እንዲያደርግ ያስችሉታል:: እነዚህ መሣሪያዎች ሦስትዮሻዊ የመማር ሂደትን ማለትም ተነሳሶትን (motivation)፣ ክፍፍልን (Classification)፣ እና ማነቃቂያን (Stimulation) በማሟላት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ::

በቴክኒዮሎጂካዊ ሚዲያ የማስተማር ተቀዳሚ ዓላማ በተማሪውና በሚሠጠው የትምህርት ይዘት (ፅንሠ ሐሳብ) መካከል የሚኖረውን ግንኙነት መሥመር ማጥራት እንደሆነ Aggarwal (1996) አክለው ይገልጻሉ:: በዚህም ረገድ ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመማር ሂደት ውስጥ የሚተላለፉትን መረጃዎች እንዳይረሱ ይዞ የማቆየትና እንዲታወሱ የማድረግ፣ በምክንያት እንዲደገፉ የማስቻል፣ በተግባር እንዲተረጎሙ የማድረግ፣ ተወዳጅ

እንዲሆኑና ምናባዊ ምሥል እንዲፈጥሩና ከተማሪው ጋር እንዲዋሐዱ የማድረግ ፋይዳ አላቸው::

በድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምድብ ሥር የሚካተቱት መርጃ መሣሪያዎች ለዕይታ የቀረቡ መረጃዎች (demonstrations)፣ ፊልሞች፣ ከተቀዳ ድምፅ ጋር የተቀረፁ ውጤቶች፣ የድምፅ ፊልም ስትሪፖች፣ ጥናታዊ ጉዞ (Study trips)፣ ቴሌቪዥን፣ ቪዲዮ ቴፖችና የመሳሰሉት እንደሆኑ ቀደም ሲል ተዘርዝሯል::

የእነዚህ መሣሪያዎች አገልግሎትም ድምፅን ከምሥል ጋር በማጣመር የቋንቋን በተለይም የሁለተኛ ቋንቋን የመማር - ማስተማር ሂደት ከውስብስብነትና ከረቂቅነት ወደ ቀላልና ተጨባጭነት በመቀየር የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ በቀላሉ እንዲገነዘብ ማስቻል መሆኑም ተደጋግሞ ተገልጿል::

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ሥር የተነሱትን ነጥቦች በዚህ ቋጭተን በመቀጠል ደግሞ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥ ወደሚለው ንዑስ ምዕራፍ እናልፋለን::

## 2.3. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥ

አንድ መምህር የዕለት ትምህርት ዕቅድ ከማዘጋጀቱ በፊት የትኛው መርጃ መሣሪያ በትምህርት ዕቅዱ ውስጥ መካተት እንዳለበትና በሚያስተምርበት ወቅትም በዕቅዱ መሠረት መገልገል እንዳለበት በበርካታ ጥናቶች የተደገፈና የሚታመንበትም ነው:: ከዚህ አኳያ Bower (1982፣53) መምህሩ ማጤን ያለባቸውን ነጥቦች እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፤

1. የዕለት ትምህርት ዓላማንና የመርሐ ትምህርቱን አጠቃላይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያግዝ መሆኑን፣
2. ዝርዝር የትምህርት ዓላማን የሚያሳካ መሆኑን፣
3. በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን ልዩ ልዩ ባሕሪያት (ዕድሜ፣ ፆታ፣ ትምህርታዊ ዳራና ቋንቋውን ለመማር የሚፈልጉበትን ምክንያቶች) ከግምት ማስገባት መቻሉን፣
4. እንደዓይነ-አፋርነት፣ ጭንቀት፣ ወይም ከክፍል ጓደኞች ጋር የሚፈጠር የመግባባት ችግር የተነሳ ትምህርቱን ሊያደናቅፉ የሚችሉ የመግባቢያ ዕክሎችን ያገናዘበ መሆኑን፤

5. በትምህርት ዕቅዱ አነዳደፍ ምንን ለማስተማር ወይም የትኛውን ክሂል ለማዳበር ታስቦ እንደሆነ ያገናዘበ መሆኑን፣

6. ለዕለቱ ትምህርት የሚመረጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደልብ ሲገኙ፣ ሲንቀሳቀሱ፣ ሲተገበሩ መቻላቸው/አለመቻላቸው መጤን ይኖርበታል::

ምንም እንኳ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመማር ሂደት ውስጥ የሳቢነትና የፍላጎት ቀስቃሽነት ባሕሪይ ቢኖራቸውም አንድ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለሁሉም ክፍለ-ትምህርት ዓላማ ማሳኪያና ይዘት ማብራሪያ ይውላል ማለት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት:: ለምሳሌ ማዳመጥን ለማስተማር ድምፃዊ ወይም ድምፃዊ ወዕይታዊ መሣሪያዎችን እንጂ በዕይታውያን መጠቀም አይቻልም::

### 2.3.1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥ መርሖዎች

አንድ መምህር በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በደጋፊነት ለመጠቀም በቅድሚያ የትኛው መርጃ መሣሪያ ለየትኛው ትምህርት መቼ መቅረብ አለበት? እንዴትስ መቅረብ ይኖርበታል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አመራረጥ መርሖች መከተል ይኖርበታል:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚመረጥ መርጃ መሣሪያ ለትምህርቱ ዓላማ ግብ መምታት፣ ለመምህሩ የማስተማር ክንውን መቀላጠፍም ሆነ ለተማሪው የትምህርት አቀባበል ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያረጋግጣሉ::

Aggarwal (1996፣158-160) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሂደት ውስጥ መከተል የሚገባንን መርሆዎች በተመለከተ የአመራረጥ፣ የአዘገጃጀት፣ የአካላዊ ቁጥጥር፣ የአቀራረብ፣ የፍላጎት ምላሽ እና የግምገማ መርሖዎች በማለት በዝርዝር ያቀርቡአቸዋል:: ከእነዚህ መካከል ለዚህ ንዑስ ርዕስ የሚስማማውን የአመራረጥ መርሕን ብቻ ወስደን እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፤

የአመራረጥ መርሕ (Principle of Selection)

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ውጤታማነት የሚረጋገጠው ለመማር ዓላማዎች ግብ መምታትና ለሚማሩባቸው ተማሪዎች የተለያዩ ባህሪያት አመቺ ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው:: የሚከተሉት ነጥቦች ይኽን ሃሳብ ይበልጥ የሚያጠናክሩ ናቸው:: የሚመረጡት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች:-

ሀ. ከተማሪዎች ዕድሜ፣ የክፍል ደረጃና ሌሎች ባሕሪያት ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው::

ለ. ስሜትን ከማነሳሳትና ፍላጎትን ከመቀስቀስ ባሻገር የተለየ ትምህርታዊ ዕሴት (Specific educational value) ያላቸው ሊሆን ይገባል::

ሐ. የሚወክሉትን እውነተኛ ነገር በትክክል መምሰል ይኖርባቸዋል::

መ. የተፈለገውን የትምህርት ዓላማ ዕውን ለማድረግ ዕገዛ የሚያደርጉ መሆን ይኖርባቸዋል::

አንድ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለማስተማር ሥራ በሚመረጥበት ጊዜ ከተማሪዎቹ ዕድሜና የትምህርት ደረጃ አንጻር እጅግም ያልተወሳሰበ፣ እንደፈለጉት ፈትተው/ ገጥመው የሚሞክሩትና በቀላሉ የሚረዱት ሊሆን ይገባል:: እንደዚሁም ደግሞ የሚመረጠው መርጃ መሣሪያ የሚማሩበትን ተማሪዎች ባሕሪያት ማለትም አፍ መፍቻ ወይም ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች መሆናቸውን፣ ከተማሪዎቹ መካከል የተለያዩ አካል ጉዳተኞች መኖር/አለመኖራቸውን፣ ካሉም መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም ይችሉ/አይችሉ እንደሆነ፣ የሚመረጠው የትምህርት መርጃ መሣሪያ የተማሪዎችን ያታዊ ልዩነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን አስቀድሞ መገመት ያስፈልጋል::

የሚመረጠው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ፋይዳው በውበቱና በሳቢነቱ የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎትና ስሜት መቀስቀስ ብቻ መሆን የለበትም:: ከዚያ ባለፈ አንዳች ትምህርታዊ ዕሴት ያለውና የተማሪውን ሁለንተናዊ ባሕሪይ ከመለወጥ አንፃር የተለየ ሚና የሚጫወት መሆን ይኖርበታል::

የሚመረጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በተቻለ መጠን የሚወክሉትን እውነተኛ ነገር ሊመስሉ ይገባል:: መርጃ መሣሪያዎቹ የሚወክሉትን እውነተኛ ነገር ካልመሰሉ የትርጉም አሻሚነትን (ambiguity) ከመፍጠራቸውም በላይ በተማሪዎቹ ዘንድ ተቀባይነትን ያጣሉ፤

የመምህሩንም የማስተማሪያ መማሪያ አመራረጥ ብቃትና የትምህርቱን ይዘት ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ ይከታሉ።

የሚመረጡት የትምህርት መርጃ መማሪያዎች የተፈለገውን የትምህርት ዓላማ ዕውን ለማድረግና ከግብ ለማድረስ የሚያግዙ ሊሆን ይገባል፤ የተፈለገውን የትምህርት ዓላማ ከማረጋገጥ አንፃር የሚመረጡት የትምህርት መርጃ መማሪያዎች ቀጥተኛ ሚና የማይጫወቱ ከሆነ ምንም እገዛ እንዳላደረጉ ይቆጠራል።

## 2.3.2. የጥሩ ትምህርት መርጃ መማሪያ ባሕሪያት

አንድ የትምህርት መርጃ መማሪያ ለአንድ የትምህርት ዓላማ ማሳኪያና ለመማር -ማስተማሩ ክንውን ማቀላጠፊያ ይሆን ዘንድ ታስቦ ከመመረጡ፣ ከመዘጋጀቱም ሆነ አገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት መርጃ መማሪያው እንዴትና በምን ዓይነት ሁኔታ መመረጥ፣ መዘጋጀትና አገልግሎት ላይ መዋል እንዳለበት መገመትና ማወቅ ብልህነት ነው።

Aggarwal (1996፣157) የጥሩ ትምህርት መርጃ መማሪያዎች ባህሪያት ብለው ያስቀመጡዋቸው አሥር ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፤

- ትርጉም ሰጭና ምክንያታዊ መሆን አለባቸው።
- ለማናቸውም ለሚሠሩበትና እንዲያገለግሉ ለታሰቡበት ዓላማ ትክክለኛ መሆን አለባቸው።
- ለአያያዝ ቀላል እና ምቹ መሆን አለባቸው።
- ዋጋቸው ተመጣጣኝ እና ርካሽ መሆን አለበት።
- በተቻለ መጠን በሙከራ የተረጋገጡ መሆን አለባቸው።
- በክፍል ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ በሚታይ ሁኔታ ሰፋና ተለቅ ባለ መጠን መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።
- ወቅቱን የጠበቁ ማለትም በዕለቱ ለሚሠጥ ትምህርት አገልግሎት ሊሠጡ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
- በየትኛውም ቦታና ሁኔታ በቀላሉ ከቦታ ወደቦታ ለማንቀሳቀስ የሚቻሉ መሆን አለባቸው።

- ከተማሪዎች የዕድሜና የዕውቀት ደረጃ ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው::
- የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት የሚያነሳሱና ማራኪ /ሳቢ/ መሆን አለባቸው::

## 2.4. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት

በርካታ መምህራን ሥዕል የመሳል ችሎታ እንደሌላቸው ይናገራሉ:: ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ሥዕል መሳልን ተለማምደው ስለማያውቁ ለመሞከር ድፍረቱ እንደሚጎላቸው ነው:: አንድ መምህር አንድን ለቋንቋ ማስተማሪያ የሚሆን ሥዕል በጥቁር ሠሌዳ ላይ ለመሳል የግድ በጣም ታዋቂ የሆነ ሰዓሊ መሆን አያስፈልገውም፤ የሚፈለገው ቁም ነገር ሥዕሎቹ ሊተረጎም ለተፈለገው ነገር ተገቢውን ትርጉም ሠጥተው ማግባባት መቻላቸው ብቻ ነው:: በዓይነትና በቁጥር በርካታ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመምህሩ ሊሠሩ ይችላሉ፤ ነገር ግን የሚሠሩት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመብዛታቸውን ያህል ለረዥም ጊዜ አገልግሎት እንዲሠጡ ተደርገው ቢሠሩ አንድን መርጃ መሣሪያ በተደጋጋሚ በመሥራት የሚጠፋውን ጊዜና ወጪ መቆጠብ እንደሚቻል ደግሞ Harris (1958፣113) ያስረዳሉ:: Harris አያይዘውም፣ በጣም የተደራጀና በመርሐ ትምህርት የሚመራ የመስክ ጉብኝት አንድን የተለየ የትምህርት ፕሮጀክት በግልፅና በተጨባጭ ለመረዳት በየትኛውም ደረጃ አስፈላጊ መሆኑን፣ በተለይም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ የሚደረገው የመስክ ጉብኝት በትምህርት ቤት አካባቢ በሚገኙ በጣም ቀለል ባሉ ተፈጥሯዊ ገጽታዎች እና ሰው ሠራሽ ማሕበራዊና መንግሥታዊ ተቋማት ላይ ባተኮሩ የዕለት ተዕለት ክስተትና ተግባራትን በዓይን መመልከት ሲሆን እንደሚችል ያስረዳሉ::

ከእኚሁ ምሑር ጥናት መረዳት እንደሚቻለው በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ከበላይ አካሎቻቸው ማለትም ከትምህርት ቢሮዎች ወይም በአካባቢያቸው ከሚገኙ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በመጠኑ ያገኛሉ:: ሌሎች ትምህርት ቤቶች ለራሳቸው በማዘጋጀት ይገለገላሉ፣ የሚዘጋጁትም በአካባቢያቸው ከሚገኙ ቁሳቁሶች ሲሆን ዋጋቸውም አንፃራዊ በሆነ መልኩ ዝቅተኛ ነው::

አንድ መምህር በሴሚስተር መጀመሪያ ላይ ትምህርቱን በሚያቅድበት ጊዜ እሱና ተማሪዎቹ እንዴትና በምን ዓይነት ሁኔታ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀትና መጠቀም እንዳለባቸው፣ ለየትኛው ትምህርት ምን ዓይነት መርጃ መሣሪያ ሊሆን እንደሚችል፣ ወጪም

የሚያስፈልግ ከሆነ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግ፣ ተሠርቶ የሚያልቅበት ጊዜ፣ ለሥራው የባለሙያ ዕገዛ የሚያስፈልግም ከሆነ አስቀድሞ በማሰብ መርጃ መሣሪያው በተያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ደርሶ ለመማር-ማስተማሩ ተግባር እንዲውል በቅድሚያ ከሴሚስተሩ የትምህርት ዕቅድ ውስጥ አስገብቶ አብሮ ማቀድ ይኖርበታል:: እንዲህ ካልሆነና ያለዕቅድ በደመ- ነፍስ የተገኘውን የትምህርት መርጃ መሣሪያ ይዞ ወደ ክፍል መግባት፣ አሊያም ጊዜው ሲደርስ ገና ለመሥራት መሯሯጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያውን ተገቢነትና ተዛማጅነት (appropriateness and relevancy) ያጓድለዋል::

ማንኛውም ሥራ ማሕበራዊ ነው:: በአንድ ሰው ብቻ ተጀምሮ ከፍፃሜው የሚደርስ ሥራ አይኖርም፤ ቢኖርም ውጤቱ የተፈለገውን ያህል አይሆንም:: የትምህርት መርጃ መሣሪያ አዘገጃጀት ላይም ቢሆን በአንድ መምህር ብቻ የሚዘጋጅ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ውሱን ሊሆን ይችላል:: ሳዘጋጅ ቢልም ብዙ ጊዜ ሊወስድበት ስለሚችል ለተፈለገው ትምህርት በወቅቱ ላይደርስለት ይችላል:: በዚህም ላይ ሥራው አድካሚና አሰልቺ ይሆንበታል:: በዚህም የተነሳ ለተለያዩ የትምህርት ይዘቶች ማስተማሪያና ለተለያዩ የትምህርት ዓላማዎች ማሳኪያ የሚሆኑ በዓይነትና በመጠን የተለያዩና የበዙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አግኝቶ መጠቀም እጅግ ሊቸግር ይችላል:: በአንፃሩ በርካታ መምህራን እንደየፍላጎታቸውና እንደየዝንባሌያቸው በየፊናቸው ተከፋፍለው የሚያዘጋጁት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዓይነትና በመጠን የበዙ፣ ለሥራው ብዙ ጊዜ የማይፈልጉ፣ አድካሚና አሰልቺ ያልሆኑ፣ ለተፈለገው ጉዳይ በወቅቱ የሚደርሱ፣ በፍላጎትና በዝንባሌ እንዲሁም በምክክርና በመተጋገዝ ስለሚዘጋጁ ጥራታቸው የተጠበቀና በተቻለ መጠን እውነተኛውን ነገር የሚመስሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ይዘጋጃሉ ተብሎ ይታመናል (Quist 2000) ፣ Harris (1958) ፣ Aggarewal (1996)::

ባጠቃላይ Harris (1958፣112) ስለመርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት የሚከተለውን ማሳሰቢያ ይለግሳሉ:: መምህራን የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ጉጉት ለማነሳሳት ሲባል አዳዲስና የተሻሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ያለማቋረጥ ማሰባሰብና ማምረት ይጠበቅባቸዋል:: በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጁ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ቃላዊ ትምህርትን በተጨባጭ ምሳሌ በማቅረብ ጠቃሚና ረጂ ነገር በመሆን የመማር-ማስተማሩን ክንውን ያቀላጥፋሉ::

## 2.5. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መምረጥና ማግኘት ብቻውን ለመማር ማስተማሩ ተግባር ፋይዳ አይኖረውም:: Heinich et al. (1996:22) እንደሚያስገነዝቡን መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ከመረጡና ካደራጁ በኋላ የሚቀጥለውና የመጨረሻው ሥራ መምህራን ራሳቸው መርጃ መሣሪያውን ለማስተማር ተግባር እንዴት ይገለገሉባቸዋል? ተማሪዎቻቸውንስ በመርጃ መሣሪያዎች በመገልገል ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱ እንዴት ይመሩአቸዋል? የሚሉት ቁልፍ ጥያቄዎች በመርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ረገድ የሚኖረውን ሁኔታ በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው::

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም የመማር-ማስተማሩን ሂደት ይበልጥ ውጤታማና ዕውናዊ ያደርጋል:: Aggarwal (1996፣154) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን አስመልክተው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በነገሮች ላይ ለሚኖረን ዕሳቤ እና ግንዛቤ ተጨባጭ መሰረት የሚጥሉ፣ ለግንዛቤያችን ትርጉም የሚሰጉ፣ የግንዛቤያችንን አቋም በተሟላ ትርጉም የሚያዋቅሩ፣ ለቃላዊ ትምህርት በሽታ ፈዋሽ ሃይል ናቸው በማለት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ በአፅንኦት ይገልፁታል:: በማስከተልም እኚሁ ምሁር ከድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አግባባዊ አጠቃቀም ጠቃሚ ዕሴቶች መካከል የሚከተሉትን ይዘረዝራሉ፤

1. **ለቃል ትምህርት በሽታ ፈዋሽ መሆን /Antidote to the disease of verbal instruction/**
በቃል ብቻ የሚሠጠው ትምህርት እንዲቀንስ ይረዳሉ፤ ግልፅ የሆነ ግንዛቤን ይፈጥራሉ፤ በመማር ሂደት ውስጥ ትክክለኛነትን ያስገኛሉ:: ተማሪዎቻችን በቃል በርካታ ቃላትና ሐረጋትን ልናስተምራቸው እንችላለን፤ ቃላትንና ሐረጋትን በቃል ብቻ ማስተማር ጥሩ ነገር ነው፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ቃላትንና ሐረጋትን ማፍለቅ ይቻላል፤ ከመጠን በላይ የሆኑ ቃላትና ሐረጋትን የማፍለቅና የማስተላለፍ ማለትም የቃላዊ ትምህርት ቁልፍ ችግር ተማሪዎች የተላለፉላቸውን ቃላትና ሐረጋት በሙሉ በአዕምሯቸው ይዘው መተርጎምና መጠቀም ያለመቻላቸው ነው:: በመሆኑም ቶሎ ይረሱዋቸዋል፤ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም ከእንደዚሁ ያለ ችግር ያድናል::

2. የበለጠ መነሳሳትን ይፈጥራሉ (Best Motivators)

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከፍተኛ የሆነ የማነሳሳት ሃይል ስላላቸው የተማሪዎችን ስሜት የትምህርት ይቀሰቅሳሉ፤ጉጉትም ይፈጥሩባቸዋል።

3. ምናባዊ አስተሳሰቦችን ያጠራሉ (Clear Images)

የጠሩ ምናባዊ አስተሳሰቦች የሚፈጠሩት አንድን ነገር በአይናችን ስናይ፣ በጆሮአችን ስንሰማው፣ በእጃችን ስንዳስሰው፣ በምላሳችን ስንቀምሰው እና በአፍንጫችን ስናሸተው ነው። በዚህም በምናካብተው ልምድ ነገሮች (መረጃዎች) ቀጥተኛ፣ ተጨባጭ፣ እና ይነስም ይብዛም ቋሚ መሆናቸውን እናረጋግጣለን። በስሜት ሕዋሳት በመታገዝ መማር ትምህርቱን ይበልጥ ተፈጥሯዊ እና ወዲያውም በጣም ቀላል እንዲሆን ያደርጋል።

4. እውነተኞቹን የትምህርት ልምዶች ይወክላሉ (Vicarious Experiences)

አዲስና ወጥ የሆነ (first hand) ዕውነተኛ የትምህርት ልምድን ተጠቅሞ ማስተማር የተሻለ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፤ ነገር ግን እንደዚህ ያለን ነገር ለተማሪ ማቅረብ ወይንም እንዲያቀርብ ማድረግ ብዙውን ጊዜ ተግባራዊ የማይሆንበትና የማይቻልበት ሁኔታ ያጋጥማል። በርካታ ለመተግበር የማይቻሉ ነገሮችና ክስተቶች ይኖራሉ። ለምሳሌ አንድ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ተማሪ ኤክሲሞን በተጨባጭ በዓይኑ ለማየት አይችልም፤ በተመሳሳይም አንድን የደቡብ ወይንም የኦሮሚያ ክልል ነዋሪ የሆነ ተማሪን በአካል ወስደን የራስ ዳሸንን ተራራ እንዲወጡ ለማድረግ ሁኔታዎች ላይፈቅዱልን ይችላሉ። እነዚህን ለአብነት አነሳን እንጂ እንደነዚህ ያሉ በቀላሉ ለመተግበር ዕድል የማያስገኙ ለቁጥር የሚታክቱ ነገሮችና ክስተቶች አሉ። በመሆኑም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የተነሳ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የወካይነትን ሚና ይጫወታሉ።

5. የተለያየ ዓይነት መሆን (Variety)

በንግግርና ጠመኔ (talk and chalk) ብቻ የሚሠጥ ትምህርት ለተማሪው እምብዛም የሚሠጠው ጥቅም አይኖርም። ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዓይነትና በመጠን የተለያዩ ነገሮችን በተማሪውና በመምህሩ እጅ እንዲገኝ በማድረግ ለመምህሩም የማስተማር፣ ለተማሪውም የመማር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥሩላቸዋል።

6. **ነፃነት** (Freedom)

ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በሚቀርቡበት ጊዜ ህፃናት መሣሪያዎቹን የማንቀሳቀስ፣ ስለመሣሪያዎቹ የመነጋገር፣ በመሣሪያዎቹ የመደሰትና የመሳሳቅ፣ በመሣሪያዎቹ ላይ አስተያየት የመስጠት ሁኔታ እጅግ፣ የሰፋ ነው:: በዚህ ዓይነት ድባብ ውስጥ ተማሪዎች መሥራት ስለሚፈልጉ፣ መምህራንም ተማሪዎችን ማሰራት ስለሚፈልጉ ተማሪዎቹ እንደልባቸው በነፃነት ይሠራሉ::

7. **ለመያዝና ለመፈተሽ ወይም ለመመራመር የሚሰጡት ዕድል** (Opportunities to handle and manipulate)

በርካታ ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለተማሪዎች ነገሮችን የመያዝ፣ የመፈተሽና የመመራመር ዕድል ይሰጧቸዋል::

8. **የማስታወስ ችሎታን ይዞ የማቆየት ብቃት** (Retentivity)

በድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጋዥነት በሚደረግ የመማር ሂደት የስሜት ሕዋሳትን ስለሚያነቃቁ የትምህርት ልምዶችን የማስታወስ ችሎታን ይዞ የማቆየት ብቃት ይኖራቸዋል::

9. **በማስተማር መርሖዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው** (Based on Maxims of Teaching)

ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም መምህሩ የማስተማር መርሆዎችን ማለትም እንደ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ እና በተግባር መማር የሚሉትን ዓይነት እንዲከተል ያስችሉታል::

10. **በመስህብነታቸው ምክንያት ትኩረት እንዲሰጥ ያደርጋሉ** (Helpful in attracting attention)

በማናቸውም የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ትኩረት፣ ዕውነተኛውና ተፈላጊው ጉዳይ ነው:: ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በክፍል ውስጥ መማር - ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የትምህርት አቀባበልና ትኩረት አሠጣጥ ላይ

ዘላቂነት ያለው ምቹ ዓውድ በመፍጠር የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱን ማራኪና ምቹ ከማድረጋቸውም በላይ የመምህሩን የሥራ ጫና ያቃልላሉ::

11. በመማር አዳዲስ ነገሮችን ለመረዳት ይጠቅማሉ (Helpful in fixing up new learning)

በመማር ረገድ ከትምህርት ዓላማ አኳያ በተማሪው አእምሮ ውስጥ አዳዲስ ዕውቀቶችና ክሂሎት ተቀርፀው ይጎለብታሉ:: ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መማሪያዎች የተለያዩ ተግባራትንና ልምዶችን በማቅረብና የተማሪውን ስሜትና ፍላጎት በማነሳሳት የተጠቀሰው የትምህርት ዓላማ ተግባራዊ እንዲሆን ይረዳሉ::

12. ጊዜንና ጉልበትን ይቆጥባሉ (Saving of Energy and Time)

በቀላሉ ሊገለፁ የማይችሉ ፅንሠ-ሃሳቦችና ክስተቶች በድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መማሪያዎች አማካኝነት በቀላሉ ሊገለፁ፣ ሊረዱ እና በተማሪው ዘንድ ሊዋሃዱ ይችላሉ:: በዚህም የተነሳ ከሚወስዱት አጭር ጊዜ አንፃር የተማሪውንም ሆነ የመምህሩን ጊዜ ይቆጥባሉ::

13. ነገሮችን እንዳሉ ያቀርባሉ (realism)

በድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መማሪያዎችን መጠቀም ነገሮች ባሉበት ሁኔታ ትዕይንተ ገጽታቸው እንዲታይና እንዲዳሰስ በማድረግ ለመማር ሁኔታ አስተዋጽኦ ያደረጋሉ:: ፊልሞችን በማየት፣ ዓውደ ርዕዮችን በማሳየት፣ ወዘተ. ምናልባት በንባብ ለመረዳት በሳምንታት የሚቆጠር ጊዜን ሊወስድ የሚችልን ነገር በጥቂት ሰዓታት ጊዜ ውስጥ መረዳት እንደሚቻል ጥናቶች ያረጋግጣሉ::

14. ግልፅነት (Vividness)

ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መማሪያዎች ለመማሪያ ድባብ ግልፅነትን ይፈጥራሉ:: ለምሳሌ የአንድ ታሪካዊ ወይም ሃይማኖታዊ ገጽታን የሚያሳይና በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀነባበረን ፊልም ስናይ ትክክለኛውን ሥዕላዊ ገጽታ በማየት እንማርበታለን::

15. ግለሰባዊ ልዩነቶችን ያጠባሉ (ያስታርቃሉ) (Meeting Individual Differences)

በተማሪዎች መካከል ሰፊ ግለሰባዊ ልዩነቶች ይኖራሉ:: አንዳንዶች ማዳመጥን ብቻ የሚመርጡ፣ ሌሎች ለዕይታ የቀረቡትን ነገሮች በማየት የሚረዱ፣ ሌሎች ደግሞ በተግባር እየሠሩ መማርን የሚመርጡ ሊሆኑ ይችላሉ:: በዓይነትና በመጠን የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም እነዚህን የተለያዩ የመማር ፍላጎትና ዝንባሌ ያላቸውን ተማሪዎች የትምህርት ፍላጎት በማሰባሰብ ያገናኛል::

16. ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንዲፈጠር ያበረታታሉ (Encouragement to Healthy Classroom Interaction)

ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባላቸው መጠነ ሰፊ አነቃቂነታቸው፣ አጓጊነታቸው፣ ተማሪዎችን በንቃት ማሳተፋቸው፣ በዕውነተኛ ነገሮች ወካይነታቸው፣ ወዘተ ለመማር - ማስተማሩ ዓላማ ግብ ሙምታት ጤናማ የሆነ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንዲፈጠር ዕገዛ ያደርጋሉ::

17. ትምህርትን በብዙሃን ስሌት ማሠራጨት (Spread of Education on a mass scale)

እንደ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ያሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በተለያየ አካባቢ በርቀት ላይ ለሚኖር ተማሪ ትምህርት በአንድ ጊዜ እንዲደርሰው ዕድል ይሰጣሉ::

18. ሳይንሳዊ ዕውነታዎችን ማስተዋወቅ (Promotion of Scientific Temper)

ተማሪዎች ስለአንድ ነገር እውነታን በቃል ከመስማት ፋንታ በሠርቶ ማሳያ ላይ የተቀመጡት ነገሮችንና ክስተቶችን በመመልከት እውነታው ሳይንሳዊ መሆኑን ይበልጥ ያረጋግጣሉ:: በዚህ ዓይነት ሁኔታም የአጠቃላይ የመማሪያ ክፍሉ ድባብ ለፈጠራ ተግባር የተመቻቸ እንዲሆን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ::

2.5.1. የትምህርት መርጃ መሣሪያን የማቅረብ (የማሳየት) መርሕ

ይህ መርሕ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ረገድ የሚከተሉትን ነጥቦች ያነበባርቃል Aggarwal (1996:155-156)፤

ሀ. መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማስተማሪያ መርጃነት ከማቅረባቸው በፊት መርጃ መሣሪያዎቹን በጥንቃቄ በአይን ህሊናቸው መቃኘትና ስለመርጃ መሣሪያዎቹ በቂ ግንዛቤ መጨበጥ ይኖርባቸዋል:: በሌላ አነጋገር አካላዊ ገጽታውንም ሆነ ምንነቱን በቅድሚያ ለራሳቸው መረዳት ይኖርባቸዋል::

ለ. በክፍል ውስጥ ለዕይታ (ለማስተማሪያ) የሚቀርቡትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የአፈታት፣ የአገጣጠም፣ የአሰራርና የአጠቃቀም ቴክኒኮችን መምህራን በቅድሚያ ማወቅና መፈተሽ ይኖርባቸዋል::

ሐ. በአጠቃቀም ሂደት ወቅት የትምህርት መርጃ መሣሪያው ጉዳት እንዳይደርስበት ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል::

መ. የክፍሉ ተማሪዎች በሙሉ መመልከት በሚችሉበት ሁኔታና በምልከታውም የሚፈለገውን ዕውቀትና ክሂሎት እንዲቀስሙበት ይችሉ ዘንድ የትምህርት መርጃ መሣሪያው በትክክል በሚታይ ቦታ ለዕይታ መቅረብ ይኖርበታል::

ሠ. በመርጃ መሣሪያው ላይ ሙሉ ትኩረት ለመስጠት ያመች ዘንድ በተቻለ መጠን ሐሳብን/ ትኩረትን የሚሰርቁ ነገሮችን ማስወገድ ያስፈልጋል::

ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች መርጃ መሣሪያዎቹን በአግባቡ ከተጠቀሙባቸው በኋላ በመርጃ መሣሪያዎቹ አጋዥነት ላከናወኑዋቸው የመማር ተግባራት በመምህራኑ አመቻችነት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት የመቻላቸው ብቃት ከአጠቃቀሙ መርሀ ጋር ተዳምሮ የሚታይ ነው:: እንደዚሁም የትምህርት መርጃ መሣሪያው ከዕለቱ ትምህርት ጋር የሚኖረው ተዛማጅነት፣ ተገቢነት እና የተማሪዎቹ አጠቃቀም ቴክኒክ ብቃት በትምህርቱ መጨረሻ ላይ መገምገም ይኖርበታል::

### 2.5.2. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሥነ ልቡናዊ ሁኔታ (The Psychology of Using Teaching Aids)

ከማንበብ በተጨማሪ ከሥዕሎች፣ ከፊልሞች፣ ከፊልም ስትሪፖች፣ ከመረጃ ሰጪ ግለሰቦች (resource persons)፣ ከመቅረፀ-ድምፆች፣ ከትምህርታዊ ጨዋታዎች (mockups)፣ ከቴሌቪዥን እና ከመሳሰሉት እውነተኞቹን የትምህርት ልምዶች ውክልና ማግኘት ይቻላል፡፡ በጣም ተጨባጭና አሳማኝ የትምህርት ልምድ ውክልና ወደ እውነተኛው ነገር በጣም የቀረበ በመሆኑ የመማሩን ሂደት ይበልጥ ውጤታማ ያደርገዋል፡፡ በርግጥ ተማሪው እውነተኛውን ነገር የወከለውን የትምህርት መርጃ መሣሪያ ውክልና አምኖ ካልተቀበለና በአጠቃቀም ላይም እንደ እውነተኛው ነገር አድርጎ ካላሰበው የመማሩ ነገር ከእውነተኛው ነገር ትምህርት ሕይወት ጋር የመነባበሩ ሁኔታ አጠያያቂ ሊሆን ይችላል፡፡

በትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ በሚከናወኑ የመማር ተግባራት ላይ የማስተማሪያ ሚዲያዎች የስሜት ሕዋሳትን በመቀስቀስ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከፍ እንደሚያደርጉ በተለያዩ አጋጣሚዎች በተደጋጋሚ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ በተግባቦታዊ ተግባራት ውስጥ የተለያዩ የስሜት ሕዋሳት እንደየሁኔታቸው መልዕክቶችን የመቀበል ደረጃቸው የላቀ ነው፡፡ እንደ Aggarwal (1996፣157) አገላለጽ፣ አንድ ተማሪ ከተሠጠው ትምህርት ውስጥ በስሜት ሕዋሳቱ አማካኝነት ምን ያህሉን ማስታወስ እንደሚችል Cubon (1969)ን በመጥቀስ እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፤

ከተሠጠው ትምህርት ውስጥ የማስታወስ ችሎታው ከመቶ ስሌት አንጻር ሲቀመጥ እንደሚከተለው ይቀርባል፤

- በመቅመስ 1 እጅ
- በመንካት 1.5 እጅ
- በማሽተት 3.5. እጅ
- በማዳመጥ 11 እጅ
- በማየት 83 እጅ ነው፡፡

እኚሁ ምሁር አያይዘውም የሰዎችን የማስታወስ ደረጃ እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

- ከሚያነቡት 10 ከመቶ
- ከሚያዳምጡት 20 ከመቶ

- ከሚያዩት 30 ከመቶ
- ከሚያዩትና ከሚሰሙት 50 ከመቶ
- ከሚናገሩት 30 ከመቶ
- እየሰሩ ከሚናገሩት 90 ከመቶ

የማስታወስ ችሎታ አላቸው::

ከዚህ አጠቃላይ መረጃ መረዳት የምንችለው አንድ ተማሪ በተለያዩ የስሜት ሕዋሳቱ አማካኝነት በመታገዝ ሲማር የማስታወስ ብቃቱ እያደገ የሚሄድ መሆኑንና በተለይም በእጁ ስለሠራው ነገር መግለጫ እያቀረበ ሲማር ትምህርቱን የማስታወስ ችሎታው እጅግ ከፍተኛ እንደሚሆን ነው::

### 2.5.3. በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮች

በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተፈላጊነት ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ቢመጣም በአጠቃቀሙ ላይ የሚታዩ መጠነኛ ችግሮች ይኖራሉ:: እነዚህንም Aggarwal (1996፣ 159-16) እንደሚከተለው ይዘረዝራቸዋል፤

#### 1. የመምህራኑ ግድየለሽነት (Apathy of Teachers)

ትምህርትን በቃል ብቻ ማስተማር አሰልቺ፣ ጊዜን አባካኝ እና ውጤታማ ያልሆነ መሆኑን መምህራን አምነው ሊቀበሉ ይገባል:: በመርጃ መሣሪያ አመራረጥ፣ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ረገድ መምህራን ግድየለሽነት ካጠቃቸው የመማሩ ሂደት ችግር ያጋጥመዋል::

#### 2. የተማሪዎች ግድ የለሽነት (Indifference of Students)

ታስቦበት በጥንቃቄ በተሠራ የትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠቀም የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል፤ በአንፃሩ ግን በግልጽ ለማይታወቅ ምክንያት (ያለበቂ ምክንያት) በሚዘጋጁ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም የመርጃ መሣሪያዎቹን ጠቀሜታና ተፈላጊነት ከማሳጣቱም በላይ ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ላይ የሚኖራቸውን እምነት በመቀነስ ግድየለሽ ያደርጋቸዋል::

3. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ፋይዳ ቢስ መሆን (Ineffectiveness of the aids)

በተገቢ ሁኔታ ያለመታቀድ፣ በመምህራኑ ችሎታ ማነስና ግድዬለሽነት የተነሳ በትክክል ያለመዘጋጀት፣ ትክክል ባልሆነ አቀራረብ፣ ተገቢ አተገባበር መንገድና በውይይት ያለመዳበር፣ አስፈላጊ የሆነ የአፈፃፀም ክትትል ያለመደረግ ምክንያቶች የተነሳ የተሟላ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ትግበራ ሊረጋገጥ አይችልም:: የሚዲያዎቹ በተግባር ያለመተርጎምም ፋይዳ ቢስነታቸውን ያመላክታል::

4. የገንዘብ እክሎች (Financial Hurdles)

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት ወይንም የተዘጋጀውን ለመግዛት፣ የሚያዘጋጁትን መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ለማሰልጠን አነስም በዛ ገንዘብ ያስፈልጋል:: በዚህ ረገድ ትምህርት ቤቶች የገንዘብ ዕጥረት ካለባቸው የተፈለገው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ላይሠራ ወይም ላይገዛ ይችላል፤ ሥልጠናዎችም ሊስተጓጎሉ ወይም በጭራሽ ላይካሄዱ ይችላሉ::

5. የኤሌክትሪክ ኃይል ያለመኖር

ብዙዎቹ ፕሮጀክተሮች፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ያለ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ሊሰጡ አይችሉም:: ኤሌክትሪክ ደግሞ በአብዛኞቹ የገጠር ትምህርት ቤቶች እንደልብ የማይዳረስበት ሁኔታ ይኖራል::

6. ለሥልጠና የሚያስፈልጉ ምቹ ሁኔታዎች ያለመኖር ወይም ዕጥረት

የማሠልጠኛ ኮሌጆች ወይም የሥልጠና ማዕከላት መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ረገድ ተገቢ ክሂሎት እንዲጨብጡ የማድረግ ሚና ይጫወታሉ:: እንደነዚህ ያሉ የማሰልጠኛ ኮሌጆችና የሥልጠና ማዕከላት በማይኖሩበት አካባቢ ባሉ ትምህርት ቤቶች የሚሰሩ መምህራንና ባለሙያዎች ሥልጠናዎችን የማግኘት አጋጣሚ አናሳ ይሆናል፤ በዚህም የተነሳ ሥልጠናዎችን ባለማግኘታቸው ምክንያት በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል::

## 7. ተማሪዎች ጉብኝት የሚያደርጉባቸው ማዕከላት ያለመኖር

በትምህርት ቤትና በክፍል ውስጥ ከሚቀርብላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በተጨማሪ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪም ጉብኝት የሚያደርጉባቸው ደረጃቸውን የጠበቁና የተደራጁ የፊልም ላይብራሪዎች፣ የድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ሙዚየም፣ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ዓውደ-ርዕዮች (exhibitions) እና የመሳሰሉት ጉዳዩ በሚመለከታቸው የትምህርት የበላይ አካላት መደራጀት ይኖርባቸዋል::

## 8. ትምህርት መስጫ ቋንቋን ያለመረዳት ችግር

ትምህርታዊ ፊልሞች የትምህርት በሬዲዮና በቴሌቪዥን ማሰራጫ ቋንቋዎች አቀራረብ ተማሪው አፍ ከፈታበት ቋንቋ የተለዩና የረቀቁ ከሆኑ ለግንዛቤ ችግር ይፈጥራሉ:: በመሆኑም በተለይ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለዚህ ዓይነቱ ችግር በጣም የተጋለጡ ናቸው::

## 9 በአካባቢ ቁሳቁስ የመጠቀም ፍላጎት ማነስ

በአካባቢ በሚታዩ ማሕበረሰባዊ፣ ሥነልቦናዊ እና ሥነትምህርታዊ ምክንያቶች የተነሳ በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የማዘጋጀት ፍላጎትና ትኩረት አናሳ ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ መርጃ መሣሪያዎቹ ከቆዳ ወይም ከሸክላ የሚሠሩ ቢሆኑ በአንዳንድ አካባቢ በሚታዩ ራስን ከፍ የማድረግና "የጨዋ ልጅ ወግ" ከቆዳ መሥራትን እንደፋቂነት፣ ከሸክላ መሥራትን ደግሞ እንደሸክላ ሠሪነት ወይም ፉጋነት አድርጎ የመቁጠር ሥነማሕበረሰባዊና ሥነልቡናዊ ችግር መፍጠር ሊከሰት ይችላል:: በሌላ በኩል ደግሞ ከአካባቢ ቁሳቁስ የሚሠሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እንደዝቅተኛ ነገርና ምንም ትምህርት እንደማይቀስምበት አድርጎ መመልከትና ትምህርት መርጃ መሣሪያ ሲባል በፋብሪካ ወይም በማምረቻ ድርጅት ብቻ ተመርቶና ተዘጋጅቶ የሚመጣ መሆን እንዳለበት ዓይነት የማሰብ ሥነ ትምህርታዊ ችግር ሊጠቀስ ይችላል::

10. ተገቢ የሆነ መርጃ መሣሪያ መምረጥ ያለመቻል ችግር

ለአንድ ትምህርት ዓላማ ማሳኪያና ለመማር-ማስተማር ክንውን ማቀላጠፊያ የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በንቃት መምረጥ ካልተቻለ የትምህርቱን ዓላማ ለማሳካትና የተማሪውን የትምህርት ፍላጎት ለመቀስቀስ ፈፅሞ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ያደርሳል::

ባጠቃላይ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀትና ለመጠቀም ስናስብ ከትምህርቱ ጎናዊና ተዋረዳዊ ዝምድና አኳያ የወደፊቱም እየታሰበ መሆን ይኖርበታል:: ለዛሬ ትምህርት የተጠቀምንበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለነገውና በተከታታይ ለሚቀርቡት ትምህርቶች መሠረት ጣይና አጎላማሽ ሊሆን ይገባል እንጂ ዛሬ አንድ መርጃ መሣሪያ ተጠቅመን ለነገውና ለሚቀጥሉት ተከታታይ ትምህርቶች እንደማያገለግል አድርገን የምንጥል ከሆነ መርጃ መሣሪያው በትምህርቶቹ ተከታታይነትና ተዛማጅነት ላይ የሚጫወተውን ሚና ያጣል ማለት ነው::

ይህንን ንዑስ ርዕስ ስናጠቃልል ይበልጥ ትኩረት ማድረግ ያለብን ለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ስኬትም ሆነ ውድቀት ተጠያቂው መምህሩ መሆኑን ነው:: Heinich et al. (1996:19)፣ "በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ውጤታማ አጠቃቀም የመምህሩ ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው::" በማለት ሐሳቡን ያጎለታል::

ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ጥያቄ መምህራን እያንዳንዱን የትምህርት መርጃ መሣሪያ እንደትምህርት ባለሙያ በተገቢ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ሙያዊ ስልት (ቴክኒክ) የማግኘታቸው ጉዳይ ነው:: የሚቀጥለው ክፍል መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተገቢ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ብቃት የሚያስታጥቃቸውን ሙያዊ ሥልጠና የሚመለከት ነው::

2.5.4. በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ የሚደረግ ሥልጠና

እንደ Newby et al. (1996:262) በቅድመ-ሥልጠናም ሆነ በሥራ ላይ ሥልጠና ወቅት ለመምህራን የሚሰጡት የሚዲያ ክሂሎት ማጎልበቻ ሥልጠናዎች ብቻቸውን መምህሩን የሚዲያ ባለሙያ አያደርጉትም፤ ነገር ግን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመማር ማስተማር

ተግባር አስፈላጊ እንደመሆናቸው መጠን መምህራኑ ቢያንስ እጅግ ቀላል የሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እንዲያዘጋጁዋቸውና እንዲጠቀሙባዋቸው ያስፈልጋል:: ለዚህ ጥረት ደግሞ ማንኛውም በሚዲያ ላይ የሚሰጥ ሥልጠና ፍላጎትን እና ትግበራን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል:: በተለይም በዐውደ ጥናቶች (work shops) እና በመምህራን ትምህርት ተቋማት የሚሠጡ የሚደያ ላይ ሥልጠናዎች ሠልጣኞቹ በተለያዩ መርጃ መሣሪያዎች አያያዝ፣ አሠራር፣ አመራረጥ፣ አመራረት፣ አጠቃቀም እና አገማገም ቀጥተኛ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ይጠበቃል:: በዚህ ረገድ የየትምህርት ዓይነት ሚዲያ ባለሙያዎች ቡድን ያካሄደውን ቤተሙከራና የተገኘውን ውጤት በተመለከተ Melvin and Dennis (1973)ን በመጥቀስ Betsate (2000:37) እንደሚያብራሩት ቡድኑ በኦውበርን ዩኒቨርሲቲ ከሁለት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ጥናቱን አካሄደ:: ዓላማውም ለሠልጣኝ መምህራን ውጤታማ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ማስተማሪያ ስትራቴጂን ለመለየት ነበር:: ሙከራው ያረጋገጠው ሠልጣኞቹ በገለፃና በውይይት ከሚሠጥ ትምህርት ይልቅ በዚህ ዕውነናዊና ተግባራዊ ልምምድ (Authentic Practical Experiences) ይበልጥ እንደሚሣተፉና በንቃት እንደሚከታተሉ ነው:: ሠልጣኞቹን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ጥናታዊ ጽሁፎችን (term papers) እንዲጽፉ፣ ፕሮጀክት ሥራዎችን ሠርተው ዘገባ እንዲጽፉ፣ እውነተኞቹን የመማሪያ ክፍሎች እንዲመለከቱና የትምህርት መርጃ ማዕከላትን እንዲጎበኙ፣ ብጤ ማስተማር ልምምድ እንዲያደርጉ ወይም በሕፃናት መማሪያ ክፍል ገብተው የማስተማር ልምምድ እንዲያደርጉ ሁሉ በተደረጉት ሙከራዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም የመሥራት ጠቃሚነቱ ተረጋግጧል::

Newby et al. (1996፣263) ፣ በሚዲያ ሥልጠና ወቅት ሠልጣኝ መምህራን በእጃቸው እየተለማመዱ ቢሠለጥኑ ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ በማለት ከላይ የቀረበውን ሐሳብ ይጋራሉ:: በመቀጠልም “ሰዎች ብስክሌት አነዳድን ከገለፃዊ ትምህርት ወይንም መጽሐፍ በማንበብ ብቻ እንደማይማሩ ሁሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አዘገጃጀትና አጠቃቀምንም በገለፃና ከመጽሐፍ በማንበብ ብቻ ተግባራዊ ማድረግ አይችሉም::” በማለት ይገልጻሉ::

ነገር ግን ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ በሚዲያ ላይ የሚሰጡ ሥልጠናዎች የተወሰኑ ድክመቶች እንደሚታዩባቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ከዚህ ጋር በተያያዘ Legat (1979፣37) እንደዘገበው በርካታ ቁጥር ያላቸው ሠልጣኞች ከማሠልጠኛ ተቋማት የሚወጡት በማንኛውም መምህራን

በየመማሪያ ክፍሎች የሚሠሩትን ተራና ቀላል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የማዘጋጀት ዕውቀትና ክሂሎት እንኳ ሳይጨብጡ ነው። ለምሳሌ ያህል Legat ከጀማሪ መምህራን ጋር ካደረገው ቃለምልልስ ያገኘው ውጤት፣ ጀማሪ መምህራኑ በጠመኔ ሠሌዳ ላይ እንኳ በደንብ መፃፍ የማይችሉ መሆናቸውን፣ እንደዚሁም በገለፃ ወቅት ድምፃቸውን እንዴት ማውጣት እንዳለባቸው ለተወሰኑ የመጀመሪያ ሳምንታት ችግር እንደገጠማቸው ነው። Tucker (1979፣21) እንደዚሁ ያደረገውን ተመሳሳይ ምልከታ ሲዘግብ፣ በብዙ የአሜሪካን የትምህርት ኮሌጆች ከሚሠጡ የአንድ ወቅት ሥልጣናዎች መካከል በሚዲያ ሥልጠና ላይ ተማሪ-መምህራኑ የሚያጠፉት ጊዜ እጅግ አነስተኛ መሆኑን ነው። በተመሳሳይ መልኩ Koskey (1974፣66) እንዲህ በማለት ይገልጻሉ "… ስለድምፃዊ ወዕይታዊ ኮርሶች ያየነውና የሰማነው፣ ኮርሶቹ ያለ ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያ የተሰጡ መሆናቸው ነው።"

Kosky (1974፣66) እንደሚገልፁት ይህንን ችግር ለመቅረፍ የሚቻለው አሠልጣኝ መምህራን ስለሚዲያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ኮርስ ለሠልጣኝ መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት ራሳቸው መርጃ መሣሪያዎቹን እየተጠቀሙና ሠልጣኞችም በተግባር እየተገለገሉ ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ማስደረግ ይኖርባቸዋል፤ አለበለዚያ ስለሚዲያ በደረቅ ዕውነታና በጥሬ መረጃ (raw data) ብቻ የሠልጣኞችን አዕምሮ መሙላት ለተጨባጭነትና ለምክንያታዊነት ምንም ዓይነት ፋይዳ አይኖርም። እንደዚሁም ደግም አሠልጣኝ መምህራንም ሆኑ ሠልጣኞች የሚዲያ አዘገጃጀትና አጠቃቀምን ኮርስ ከአዲሱ ተማሪ-ተኮር የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጋር በማቀናጀት መተግበር ይኖርባቸዋል። Ashby and Besse (1972፣3) ምክንያቱም በአንድ በኩል ሠልጣኝ መምህራን የሚዲያ ኮርሶችን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲከታተሉ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጠናቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ለወደፊት የማስተማር ሥራቸው ላይ ተግባራዊና ተማሪ አሳታፊ የሆነ፣ በመርጃ መሣሪያ የተደገፈ የመማር ማስተማር ክንውን እንዲያደርጉ ያዘጋጃቸዋል።

በሌላ ወገን በሥራ ላይ ያሉ መምህራን ከወቅታዊ የመርጃ መሣሪያ አጠቃቀምና የማስተማር ዘዴ ጋር እንዲተዋወቁ የሚያስችል የሥራ ላይ ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል Newby et al. (1996)። ከዚህም በተጨማሪ በቅድመ ሥራ ሥልጠና ወቅት በንድፈ-ሐሳብ ብቻ ገረፍ ገረፍ ተደርገው የታለፉትን የሚዲያ ኮርሶች በጥልቀት በተግባር እንዲከልሱ ያስችላቸዋል።

የሥራ ላይ ሥልጠና አተገባበርን በተመለከተ ከውጭ አማካሪዎችና አሠልጣኞች ይልቅ የአካባቢ ሚዲያ ባለሙያዎችና በዚህ ሙያ የተካኑ የትምህርት ቤት መምህራን ቢያሠለጥኑ ይመረጣል በማለት Newby et al. (1996፣263) ይመክራሉ:: ምክንያቱም እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የትምህርት ቤትንና የመማሪያ ክፍልን ተጨባጭ አውነታ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ የተሻሉ አሠልጣኞች ይሆናሉና:: I.C.D.R. (1888፣3) በተጨማሪ እንደሚገልፀው ልምድ ያላቸው መምህራንና የሚዲያ ባለሙያዎች በተለይ ለገጠር ትምህርት ቤቶች መምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ናቸው:: ምንም እንኳ መምህራን በሥራቸው ላይ እያሉ ለመሰልጠን የሥራ መደራረብና የጊዜ ዕጥረት ሊያጋጥማቸው ቢችልም፣ ትምህርት ቤቱና አሠልጣኞቹ ከመምህራኑ ጋር በጋራ በመሆን አመቺ የሆነ ጊዜ በመምረጥ የሥልጠና ጊዜ ሠሌዳ ሊያዘጋጁ ይችላሉ በማለት Newby (1996፣263) ጨምረው ይገልጻሉ::

## 2.6. የመማር-ማስተማርን ተግባር በማመቻቸት ረገድ የሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት ሚና

"የትምህርት መርጃ መሣሪያ ቅርንጫፍ ማዕከላት" የሚለው ስያሜ ከአገር አገር ይለያያል:: የዚህ ጥናት አቅራቢ በሐገራችን የሚባለውን ስያሜ ማለትም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ቅርንጫፍ ማዕከል ወይም ሚዲያ ማዕከል (Pedagogical center or media center) የሚለውን ስያሜ በመጠቀም ስለሚናው ለማብራራት ይሞክራል:: በሃገራችን ይህ ስያሜ ስለመሠጠቱም (Amare and Tasew, 1996፣13) ያረጋግጣሉ:: ቅርንጫፍ የተባለበትም ምክንያት በተለያዩ የትምህርት አስተዳደር አካላት ደረጃ በደረጃ የሚዲያ ማዕከላት እንዳሉና የዚህ ጽሑፍ ትኩረቱ በታችኛው በትምህርት ቤት ደረጃ በሚገኘው የሚዲያ ማዕከል በመሆኑ ነው::

የትምህርት መርጃ መሣሪያ ማዕከላት ሰፊ ይዘት ያላቸው የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚመረቱበት፣ የሚደራጁበት እና የሚሰራጩበት ተቋም ነው:: Kieffer and Cochran (1962፣233)፣ Ashby and Besse (1972፣33) እና Heinich et al. (1996፣18) በአሁኑ ጊዜ የሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት በየትምህርት ቤቱ ተመሥርተዋል:: ምክንያቱም በመማር - ማስተማር ሂደት ፍፁማዊ የሆነ ዕድገትና መሻሻል ሊመጣ የሚችለው ከዚህ ዓይነት አደረጃጀት ከሚገኝ አገልግሎትና ዕገዛ ነውና Tucker (1979፣127)::

የትምህርት ቤት ሚዲያ ማዕከላት አመሠራረት ታሪካዊ ዳራን ስንመለከት እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ ውስጥ በምዕራባውያን ሐገራት እንደተጀመረ Newby et al. (1996፣325) ይገልጻሉ:: ከነዚህ ዓመታት በፊት የነበረው አሰራር በትምህርት ቤቶች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች የሚፈለጉና በጋራ የሚጠቀሙባቸው መርጃ መሣሪያዎች የሚቀመጡት በየቤተ መጻሕፍቱ ሲሆን የየትምህርት ዓይነቱ መርጃ መሣሪያዎች ደግሞ በቋም ሳጥኖች ወይም በመምህራን ቢሮዎች ውስጥ እንደነበር እኚሁ ምሁር አክለው ይገልጻሉ:: የእነዚህ የተለያየ ዓይነት መርጃ መሣሪያዎች መብዛትና በዚህ መልክ መከማቸት በአደረጃጀት፣ በመሣሪያ አያያዝና ጥንቃቄ፣ በንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም ረገድ ራሱን የቻለ ችግር ሆኖ በመታየቱ እነዚህን በዓይነትና በመጠን እጅግ በርካታ የሆኑትን መርጃ መሣሪያዎች በአንድ በተለየ ቦታ በስልት ማደራጀት፣ ማስተዳደር እና በምክንያት መጠቀም እንዲቻል ማድረግ አስፈለገ::

ወደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ ከ I.C.D.R. (1980፣5) በተገኘው መረጃ መሠረት በኢትዮጵያ የሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከል በትምህርት ቤት ደረጃ የተቋቋመው እ.ኤ.አ. ከ 1977 ዓ.ም በኋላ ነበር:: ይህም የተከናወነው ከ106 የአውራጃ ወይም የዲስትሪክት ሚዲያ ማዕከላት አመሰራረት በኋላ ሲሆን እነዚሁ የአውራጃ ሚዲያ ማዕከላት በበኩላቸው ደግሞ የትምህርት ቤት ሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላትን አቋቋሙ:: እ.ኤ.አ በ1984ዓ.ም. በትምህርት ሚኒስቴር ከቀረበው ሪፖርት መረዳት እንደሚቻለው በመላው ኢትዮጵያ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች 5422 የትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማዕከላት መቋቋሚቸውን Amare and Tassew (1996፣19) ይገልጻሉ::

### 2.6.1. በሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት የሚሠጡ አገልገሎቶች

የሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት ተቀዳሚ ሚና ደንበኞች (መምህራንና ተማሪዎች) እና በመርጃዎች ወይም በሚዲያ መካከል የሚኖረውን መስተጋብራዊ ግንኙነት ማመቻቸትና ማስተባበር ነው:: በመሆኑም ሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት በባሕሪያቸው አገልግሎት ሰጭ ማዕከላት ናቸው:: ማዕከላቱ ከሚዲያ ጋር የተያያዙ አገልገሎቶችን ስለሚሰጡ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ተግባር መልካም ያደርጉታል Kieffer and Cochran (1962፣229)::

በአሁኑ ሰዓት ብዙዎች የሚዲያ ባለሙያዎች የሚስማሙባቸው የሚዲያ ማዕከላት አገልግሎት ዋና ዋና ምድቦች (Categories) የሚከተሉት ናቸው (Tucker, 1979፣18-19፣ Kieffer and Cochran 1962: 233-238)።

1. **የመርጃ መሣሪያዎች ለመዳና አገልግሎት መስጫ ክፍል** (Resource Acquisition and Provision Services)

ይህ ክፍል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከል ውስጥ የማመቻቸት፣ የማደራጀት፣ የአያያዝና የአጠቃቀም ልምምድ አገልግሎት የሚሰጥበት ነው:: በማዕከሉ የተሟላ አገልግሎት ለደንበኞች ለመስጠት ይቻል ዘንድ ንብረቶቹ በጥንቃቄና በሥርዓት መደራጀትና መቀመጥ ይኖርባቸዋል::

2. **የማጣቀሻ ምንጮች አገልግሎት መስጫ ክፍል** (References Services)

በዚህ ክፍል የሚሰጠው አገልግሎት ሚዲያ-ነክ የሆኑ ማጣቀሻ መጻሕፍትንና ንብረትን ለግል ጥናትም ይሁን ለመማር ማስተማር ተግባራት በማዕከል ውስጥም ሆነ ከማዕከሉ ውጪ የሚገኙበትን ቦታ መጠቆም፣ ማሳየት፣ መረጃ መስጠትና የመሳሰሉትን ያካትታል::

3. **የምርት አገልግሎት መስጫ ክፍል** (Production Services)

በዚህ ምድብ ሥር የሚከተሉት ዓይነት አገልግሎቶች ይሰጣሉ::

- ለመምህራን እና/ወይም ለተማሪዎች እንደ የሥራ መሣሪያዎች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ እና የጽሕፈት መሣሪያዎችን የመሳሰሉ ንብረቶችን በማቅረብ ቀለል ያሉ መርጃ መሣሪያዎች እንዲሠሩ (እንዲመረቱ) ማስቻል፤

- የራሳቸውን መርጃ መሣሪያዎች ለማዘጋጀት ለሚፈልጉ መምህራንና ተማሪዎች ሙያዊ ምክር እና የቴክኒክ አገልግሎት መስጠት፤

- እንዲዘጋጁ በመምህራንና በሚዲያ ባልደረቦች የተጠቆሙትን መርጃ መሣሪያዎች ማዘጋጀት (ማምረት)፤

4. ከሚዲያ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የሥራ ላይ ሥልጠናዎች አገልግሎት መስጫ ክፍል (Media- related In-service Training Services)

Kieffer and Cochran (1962: 237) እንደሚጠቁሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ ለመምረጥ፣ ለማዘጋጀት፣ ለመጠቀምና ለመገምገም ይቻል ዘንድ ለመምህራን ዕውቀትና ክሂሎት ማዳበሪያ የሚሆን የሥራ ላይ ሥልጠና የመስጠቱ ጉዳይ ወደ ኋላ የማይባል ነው:: በመሆኑም ይህን አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል በሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከሉ መኖር አለበት::

5. የምክር አገልግሎት መስጫ ክፍል (Consulting Services)

ከሚዲያ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ ለመምህራንና ለተማሪዎች የምክር አገልግሎት መስጠት የሚዲያ ባልደረቦች ኃላፊነት ነው:: የሚሠጠው የምክር አገልገሎት የሚከተሉትን ነጥቦች በሙሉ ወይም በከፊል ሊያጠቃልል ይችላል:: የሚፈጠሩትን ችግሮች ለይቶ ማወቅን፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አመራረጥ፣ የሚገኙበትን፣ አዘገጃጀትን፣ አጠቃቀምን፣ እና አገማገምን ከውጤታማነታቸው ጋር በማያያዝ የማንዛቤ ማስጨበጫ የምክር አገልግሎት መስጠት (Kieffer and Cochran, 1962: 237) እንደዚሁም ሚዲያ ማዕከል በሥርዓተ-ትምህርት ማሻሻያ ነጥቦች ዙሪያ የትምህርት ቤት ሥርዓተ-ትምህርት ኮሚቴን በማማከር ወሳኝ ሚና ይጫወታል::

ወደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ Amare and Tassew (1996:14) እንደሚያመለክቱት፣ በኢትዮጵያ ሚዲያ ማዕከላት ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት በላይ እጅግ የሰፋ አገልግሎት ይሠጡ ነበር::

ለምሳሌ ያህል:-

- መምህራንን ጥናትና ምርምር እንዲያደርጉ በማበረታታት፣
- ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶችንና ትውፊቶችን ሰብስቦ በማስቀመጥ፣
- ከአካባቢ ክሂሎት ማሰልጠኛ ማዕከላት ጋር ትብብር መፍጠር ወዘተ ናቸው::

ለማጠቃለል የትምህርት ቤት ሚዲያ ማዕከላት በትምህርት ቤቱ የውስጥ የትምህርት ዕቅድና መርሐግብር የማሳካት አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል:: ይህም ማለት በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ለሁሉም የክፍል ደረጃዎች የሚሆኑና የሚመጥኑ የትምህርት ሚዲያ አገልግሎት መስጠት ይኖርባቸዋል ማለት ነው:: ዘርዘር ባለ መልኩም የሚዲያ ማዕከላት ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ርዕሶችና ንዑስ ርዕሶች ዓላማዎች ግብ መምቻ የሚሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መያዝ፣ ማደራጀትና አገልገሎት መስጠት ይኖርባቸዋል::

2.6.2. የሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት የሚያስፈልጓቸው መሠረታዊ ነገሮች (Basic Requirements)

የትምህርት ቤት ሚዲያ ማዕከላት ጥራት ያላቸውን አገልገሎቶች መስጠት እንዲችሉ Tucker (1979:28) እንደሚነግሩን ከሁሉም በፊት ሚዲያ ማዕከሉ የመማር ማስተማሩ ዕድገት አስፈላጊ መሆኑና ትርጉም ያለው አገልግሎት ሰጪ የሆነ የትምህርት ቤቱ አንዱ ወሳኝ አካል መሆኑ ግንዛቤና ተቀባይነት ማግኘት አለበት:: በዚህ ነጥብ ላይ Ashby and Besse (1972:33) ጨምረው እንደሚገልጹት ሚዲያ ማዕከሉ እንደለውጥ መሣሪያና ለትምህርት ቤቱ አጠቃላይ የትምህርት መርሐገብሮች ወሳኝ መሆኑ በአጋሮችና በትምህርት ቤት አስተዳደር ጭምር መታመን ይኖርበታል::

በትምህርት ቤት ደረጃ የሚዲያ ዕጣ ፈንታ ማለትም ውድቀቱም ሆነ ዕድገቱ ባጠቃላይ በትምህርት ቤቱ አስተዳደር ትኩረት መስጠት /አለመስጠት ላይ የተመሠረተ ነው Tucker (1979):: ምክንያቱም ሚዲያ ማዕከሉን በንብረትም ሆነ በገንዘብ እንዲሁም በሰው ኃይል የማደራጀት ኃላፊነትና ዕድሉ ያለው በትምህርት ቤቱ አስተዳደር እጅ ነውና::

ፋይናንስ- Betsate (2000:44) Fred and Ellington (1984)ን ጠቅሰው እንዳብራሩት ሚዲያ ማዕከላት ጥራት ያለውን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ለጥገና፣ ለውብትና ጥንካሬ መጨመሪያ፣ ወዘተ. የሚሆን ዓመታዊ በጀት ከትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ዓመታዊ በጀት ተሸንሽኖ ሊመድብላቸው ይገባል:: ምክንያቱም ቅርንጫፍ ማዕከላቱ የትምህርት ቤቱ አስፈላጊ አካላት በመሆናቸው ነው::

ወደ አገራችን ሚዲያ ማዕከላት ስንመጣ ቀድሞ በ1970ዎቹ ገደማ በነበረው የአውራጃና የትምህርት ቤት ማዕከላት መዋቅር፣ ለአውራጃ ሚዲያ ማዕከል ብር 3000.00፣ ለትምህርት

ቤት ቅርንጫፍ ማዕከል ደግሞ ብር 1000.00 ዓመታዊ በጀት ይመደብ እንደነበርና በአሁኑ ሰዓት እስከነመኖራቸውም የተዘነጉ መሆናቸውን Amare and Tassew (1996:17) ከትምህርት ሚኒስቴር ያገኙትን መረጃ በመጥቀስ ይገልጻሉ::

ትምህርት ቤቶች ባላቸው ውስን ሀብትና ገንዘብ የውስጥ የፋይንስ ችግራቸውን ብቻቸውን እንዲፈቱ ማድረጉ ፍትሃዊ ያለመሆኑንና በየደረጃው የተቀመጡ የትምህርት ሚኒስቴር አካላትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዚህ ረገድ የትምህርት ቤቶችን ሚዲያ ማዕከላት የመርዳት ሚና መጫወት እንዳለባቸው Ashby and (Besse, 1972:6) ያስገነዝባሉ::

**ቦታና ተመቻችቶዎች** (Space and Facilities)

በተጨባጭ ከሚታየው ተሞክሮ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኞቹ የትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማዕከላት የሚሰጣቸው ቦታ (የሚገኙበት) ከውስብስብ ህንፃዎች መካከል በሚገኝ አንድ የማይረባና የማይመች ጠባብ ክፍል ውስጥ እንደሚሆን Fred and Ellington (1984) በመጥቀስ Betsate (2000:45) ይገልጻሉ:: ነገር ግን የትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማዕከላት ከፍ ሲል በተጠቀሰው መሠረት ከሚሰጡት አገልግሎትና እንደገናም የንብረቶቹ ማኖሪያ ከመሆናቸው አኳያ በጣም ሰፊና ምቹ የሆነ ክፍል ሊሰጣቸው እንደሚገባ Tucker (1979:104) በአፅንኦት ይገልጻሉ::

የሚዲያ አገልግሎት ዓይነት መብዛት በሚሰጡት የትምህርት አይነቶች እና የክፍል ደረጃዎች እንዲሁም በየትምህርት አይነቶቹ ምዕራፎችና ክፍለ-ትምህርቶች መጠን ያህል የበዛ ስለሆነ፣ ቅርንጫፍ ማዕከሉ ለሚዲያ ዝግጅትና ጥገና ሰፊ ቦታ፣ ገንዘብና በቂ የሰው ኃይል በብዛት እንደሚያስፈልገው አይጠረጠርም:: ነገር ግን ከሚታዩት ተጨባጭ ዕውነታዎች መረዳት እንደሚቻለው ለትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማዕከላት ሰፊ ቦታ፣ ገንዘብና የሰው ሃይል ሲመደብ አይታይም (Tucker 1979:74):: ከዚህ በመነሳት ለአንድ በጣም ደሃ ለተባለ የገጠር ትምህርት ቤት መኖር የሚገባውን ዝቅተኛ የቅርንጫፍ ማዕከል ክፍል መጠን ከTucker እና ከUNESCO ያገኙትን መረጃ በመጥቀስ Betsate (2000:45) እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፤

1. ለግልና ለቡድን ጥናት የሚሆን ክፍል እና የተመቻቸ ሁኔታ፣
2. ለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (የታተሙ እና ያልታተሙ) ማከማቻና ማሰራጫ የሚሆን ክፍል እና የተመቻቸ ሁኔታ፣

3. ማምረቻና ሠርቶ ማሳያ ክፍል እና የተመቻቸ ሁኔታ፣

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት በዚህ እጅግ አነስተኛና ቅድሚያ መሰጠት ባለበት የትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማዕከል አደረጃጀት ውስጥ ዋና ዋና ሥራዎች የሚታዩበት ክፍል (display room) ያልተካተተ መሆኑን ነው:: ይህ ማለት ግን አስፈላጊነቱን በመዘንጋት አይደለም::

ከዚህም በተጨማሪ የትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማዕከላት ተጠቃሚዎቹ (መምህራንና ተማሪዎች) ደስ እያላቸው ሁልጊዜ እንዲጎበኙት ንፅህናውና ውበቱ ሳቢ፣ የባለሙያዎቹ አቀባበልና አስተናጋጅ ማራኪ ሊሆን እንደሚገባ Kieffer and Cochran (1962:233)፣ Tucker (1979:30) እና Ashby and Besse, (1972:109) በአፅንኦት ያሳስባሉ::

ባለሙያ (Staff)- የማንኛውም ሚዲያ ማዕከል ሥራ ስኬት፣ ሥራውን በሚመራውና በውስጡም አብሮ ሙያዊ ግልጋሎት በሚሰጥ ሰው (ባለሙያ) እንደሚወሰን Kieffer and Cochran (1962:231) ይገልጻሉ:: እዚህ ላይ አብሮ መነሳት ያለበትም ጉዳይ የባለሙያ ብዛት እና የሠለጠነበት ሙያም ጭምር ነው:: Tucker (1979:17) እንደሚሉት፣ ለአንድ ሚዲያ ማዕከል የመጨረሻው (ዝቅተኛው) አስፈላጊ የባለሙያ ብዛት ሊወስን ይገባል:: Betsate (2000:46) እንደሚሉት፣ አንድ ሚዲያ ማዕከል ሊኖረው የሚገባው የሰው ኃይል አስተባባሪ እና እንደ ሥነ አፃፃፍ ጥበብ (graphic arts)ሙያ፣ በፎቶግራፍ ሙያ፣ በቅርፃ ቅርፅ ሙያ፣ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ሙያ የተለየ ብቃት ያላቸውን ቴክኒሻኖች ባቀፈ የሰው ኃይል መሟላት እንዳለበት Judith (1973:39) እና Fred and Ellington (1984:128)ን በመጥቀስ ይገልጻሉ:: ቀደም ሲል በዚህ ክፍል እንደተገለፀው ከሚዲያ ማዕከል ባለሙያዎች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የማዘጋጀት፣ የማሳየት፣ ማጣቀሻ የማቅረብ፣ የማምረት፣ ሥራ ላይ ሥልጠና ለትምህርት ቤቱ ልዩ ልዩ መምህራን የመስጠት ኃላፊነት ይጠበቃል:: ስለሆነም ይህን ሁሉ ኃላፊነት ይወጡ ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ልዩ ልዩ የሙያ ዘርፎች ከሌሎቹ መምህራን ደንበኞቻቸው ከፍ ባለ ደረጃ በየሙያው የሠለጠኑና ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች ሊኖሩ ይገባል:: ለአንድ ሚዲያ ማዕከል አስተባባሪነት ተፈጥሯዊ ችሎታ፣ ፍላጎት እና ልምድ በቻ በቂ ነው የሚባል የተሳሳተ ግምት ይኖራል:: ለሥራው ግን ከፍ ብለው በተጠቀሱትና በመሳሰሉት ሙያዎች የሠለጠነ የሰው ኃይል እንደሚያስፈልግ የማይታበል ሃቅ ነው:: Kieffer and Cochran (1962:232) እንደሚገልፁት፣ የሚዲያ ማዕከል አስተባባሪ በመጀመሪያ ደረጃ

የመምህርነት ሙያ ሰርቲፊኬት ሊኖረው ይገባል፣ በተጨማሪም የሚዲያ አመራረጥ፣ አዘገጃጀት፣ አጠቃቀምና አገማገም በሚመለከት ሰፊ ሙያዊ ሥልጠና ማገኘት ይኖርበታል:: በተመሳሳይ ሁኔታ የሚዲያ ማዕከል አስተባባሪ በተለይ በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርቶች ውስጥ ሚዲያን በሚመለከት በቂ ችሎታና ዕውቀት ሊኖረው ይገባል:: ከዚህ ተቃራኒ በሆነ ደረጃ የበርካታ ትናንሽ ትምህርት ቤቶች ቅርንጫፍ ማዕከል አስተባባሪዎች ውስን ቴክኒካዊ ገለፃ በመስጠት እና በዘፈቀደ ተመርጠው እንደሚሰየሙ (Kieffer and Cochran, 1962:233) ይገልጻሉ::

ወደ አገራችን ሁኔታ ስንመጣ Amare and Tassew (1996:21) የመጀመሪያ የዕድገት ዘገባ በማለት MOE (1982) ያቀረበውን መረጃ ዋቢ በማድረግ እንደሚገልፁት ከ1979 እስከ 1980 እ.ኤ.አ. ባሉት ሁለት ዓመታት 4,680 የትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማዕከላት አስተባባሪዎች ተዛማጅ ሥልጠና አግኝተዋል::

በመጨረሻም በዚህ ነጥብ ዙሪያ በቂ ጥናት ያደረጉት ምሁራን ያቀረቡትን ባለ ሦስት ነጥብ የመፍትሄ ሃሳብ ባጭሩ ለማስቀመጥ እንሞክራለን::

1. ለሥርዓታዊና ምክንያታዊ የሚዲያ አጠቃቀም የሚረዳ በደንብ የተረቀቀ ሚዲያ ፖሊሲ በትምህርት ቤት፣ በአካባቢና በብሄራዊ ደረጃ መውጣት ይኖርበታል:: የሚዲያ ፖሊሲውም ፍልስፍናውንና ዓላማዎችን፣ የተጠቃሚዎችን አገልግሎት፣ ስትራቴጂዎችን፣ ደረጃዎችን እና አካሄዶችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል::

2. የትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማዕከላት ተግባር በአንድ አስተባባሪ ብቻውን መወጣት ስለማይችል የተለያዩ ባለሙያዎችን በትምህርት ቤት አቅም ደረጃ ያካተተ መሆን ይኖርበታል:: ከዚህም በተጨማሪ የሁሉም አጋር ድርጅቶች (መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑና የሚመለከታቸው) ተሳትፎ ለትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማዕከል ዕድገትና መሻሻል ብሎም ተገቢ አገልግሎት መስጠት በጣም ወሳኝ ነው::

3. የአንድ ትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማዕከል ወይም የማዕከሉ አስተባባሪ ወይም ኮሚቴ ብቻቸውን ሠርተው የተፈለገውን ለውጥ ሊያመጡ ወይንም የተሟላ አገልግሎት ሊያበረክቱ አይችሉም:: በመሆኑም በአንድ ወረዳ አካባቢ ትምህርት ቤቶች መካከል

በክላስተር የታቀፉ የትምህርት ቤቶች ሕብረት ሊኖር ይገባል፤ ይህም ወደ ላይ በማደግ በክልል እና በብሔራዊ ደረጃ የተዋቀረ የሚዲያ አገልግሎት ሰጭ ማዕከላት ሊኖር ይገባል (Ashby and Besse እና Newby et al. (1996:146) (kieffer and Cochran 1962"229) Tucker 1979:110)።

## 2.7. የሐገርኛ ጽሑፎች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ጥናቶች ለማየት ባደረገው ፍተሻ፣ ሦስት የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎችን አግኝቷል። እነዚህም:- አንደኛው በጌታቸው ለገሰ (1992) "በአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት በማሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋጽኦ" በሚል ርዕስ የተጠና ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ Betsate Terefe (2000) "Application of Instructional Materials in the Primary Schools of the SNNPR" በሚል ርዕስ የተሠራ ጥናት ነው፤ ሦስተኛው ደግሞ በAbebe Zewdie (1997) "Selection and Use of Instructional Media by Pre Service and In Service Elementary School Teachers - The Case of Region 13." በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። በጌታቸው ለገሰ የቀረበው ጥናት ከትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አንዱ ስለሆነው ሬዲዮ ላይ ብቻ የሚያተኩር ሲሆን፣ እሱም በአዲስ አበባ ከተማ ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈውን ብቻ የሚመለከት ነው። ይኸኛው ጥናት ግን የድምፃዊ፣ የዕይታዊና የድምፃዊ ወዕይታዊ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አካትቶ የሚመለከት ሲሆን በዓላማው፣ ጥናቱ በሚካሄድበት አካባቢ፣ በትምህርት እርከንና በክፍል ደረጃም ይለያል።

በBetsate የተደረገው ጥናት ደግሞ በትምህርት ፋኩልቲ የካሪኩለምና እንስትራክሽን ዲፓርትመንት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ጥናቱ የሚያተኩረውም በአካባቢ ሳይንስ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አተገባበር ላይ ነው። ይህም ቢሆን ከዚህኛው ጥናት በዓላማው፣ በትምህርት ዓይነትነቱ፣ በክፍል ደረጃውና በጥናት አካባቢው ይለያል። ሦስተኛውም ቢሆን እንደዚሁ ከትምህርት ፋኩሊቲ የካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ዲፓርትመንት ጋር የተያያዘ ጥናት ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረውም ቅድመ ሥልጠና በወሰዱ መምህራን እና በሥራ ላይ ሥልጠና በወሰዱ መምህራን መካከል የሚካሄድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቃቀም ንጽጽር ላይ ነው። ይህም እንደ ቀደሙት ሁለቱ ሁሉ ከዚህኛው ጥናት በዓላማው፣ በትምህርት ዓይነትነቱ እና በጥናት አካባቢው ይለያል።

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

ቀደም ሲል በተደጋጋሚ ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በቦንጋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች አጠቃቀም እና የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም መፈተሽ ሲሆን፣ ለዚህም አመቺ ይሆናሉ ተብለው የተመረጡት ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ክፍል የሆነው ገላጭ የምርምር ዘዴ እና መጠናዊ (Quantitative) የምርምር ዘዴ ናቸው::

## 3.1. የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች

ለዚህ ጥናት ሦስት ዓይነት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች በዋናነትና በደጋፊነት በሥራ ላይ ውለዋል:: በዚህም መሠረት ለጥናቱ በዋነኛነት መረጃ የተሰበሰበው በምልከታ (observation) ነው:: የጥናቱ ዋነኛ የመረጃ ማሰባሰቢያ ምንጭ የሆነውን ምልከታ ለማጠናከርም የጽሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ተጨማሪ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች ሆነዋል::

### 3.1.1. ምልከታ

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያ ምልከታ ነው:: በመሆኑም ስለ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ጥናቱ በተካሄደባቸው አምስቱም ትምህርት ቤቶች በአመቺነት በተመረጡ የ3ኛ እና የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ክፍለ ጊዜያት ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ በአጥኚው ተደርጓል:: እንደዚሁም ደግሞ የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶችን ሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት አሠራርና አደረጃጀት ተከታታይ ምልከታ በአጥኚው ተካሂዷል፡፡ የምልከታዎቹ መከታተያ ቅጾቹም የተዘጋጁት በመስኩ የተደረገውን ሥራ (Day, 1990) መሠረት በማድረግ ነው፡፡

### 3.1.2. የጽሑፍ መጠይቅ

የጥናቱን ዋነኛ የመረጃ ማሰባሰቢያ ምንጭ ለማጠናከር ሁለት የጽሑፍ መጠይቆች ተዘጋጅተው ለጥናቱ አማካሪ አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል:: መጠይቆቹ የተዘጋጁትም (ያለው 2006)ን መሠረት በማድረግ ነው:: ከዚያም ለጥናቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል አማርኛ መምህራንና ለሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት አስተባባሪዎች ተሰራጭተው የሚፈለጉት መረጃዎች በደጋፊነት ተሰብስበዋል:: በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ጥያቄ ዝግና ልቅ አማራጮች እንዲኖሩት ተደርጓል::

### 3.1.3. ቃለመጠይቅ

እንደ ጽሑፍ መጠይቁ ሁሉ ቃለመጠይቁም የጥናቱ ደጋፊ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያ ነው:: በዚህም መሠረት አንድ ቃለመጠይቅ በ(ያለው፣ 2006) ሞዴልነት ተዘጋጅቶ በጥናቱ አማካሪ ከተረጋገጠ በኋላ ጥናቱ የተካሄድባቸው የአምስቱ ትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራን ተጠይቀዋል:: ከቃለመጠይቁም የተገኘው መረጃ ለዋናው መረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያ (ምልከታ) በደጋፊነት አገልግሏል።

## 3.2. ናሙና አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የወረዳ (የከተማ አስተዳደር)፣ የትምህርት ቤት፣ የሳይክል (የዕርከን)፣ የክፍል ደረጃና የመምህራን ናሙና አመራረጥ ዘዴዎች በዝርዝር ተገልጸዋል።

### 3.2.1. የወረዳ /ከተማ አስተዳደር/ ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ሥር ከሚገኙት ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች መካከል የካፋ ዞን ዋና ከተማ የሆነው የቦንጋ ከተማ አስተዳደር በአመቺ የናሙና አመራረጥ ስልት ሊመረጥ ችሏል:: ምክንያቱም የዚህ ጥናት አቅራቢ በሥራ ምክንያት ከአሥር ዓመታት በላይ በከተማው የኖረ በመሆኑና ያለብዙ ችግር በቀላሉ መረጃዎችን ለማግኘት (ለመሰብሰብ) እንደሚያስችለው ስላመነበት ነው።

### 3.2.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በቦንጋ ከተማ አስተዳደር ውስጥ አምስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይገኛል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ በመሆኑ ካሉት አምስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚያስተምሩትን አራት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ማለትም ግራዝማች ጳውሎስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ባርታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ሸታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ባንዲራ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙናነት የተመረጡ ሲሆን፣ ከከተማው ድንበር በጊምቦ ወረዳ ክልል ውስጥ የሚገኘው የካያ ኬላ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትም በአመቺ ናሙናነት አምስተኛው የዚህ ጥናት ናሙና ትምህርት ቤት በመሆን ሊመረጥ ችሏል፡፡ ከዚህ በተረፈ አማርኛን በአፍ መፍቻነት የሚያስተምሩትም ሆነ ሌሎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለዚህ ጥናት በናሙናነት አልተመረጡም፡፡

### 3.2.3 የእርከን ናሙና አመራረጥ

ቋንቋን በመማር - ማስተማር ሂደት በተለይ ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ሚና ጉልቶ የሚታየው በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ እርከን ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ እንግዳ እንደመሆናቸው መጠን ቋንቋውን ከዚህ ቀደም በማዳመጥም ሆነ በመናገር ደረጃ ምንም የማያውቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከየትኛውም እርከን በላይ በዚህ በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ላይ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የማዘጋጀቱና የመጠቀሙ ሁኔታ እጅግ  የሰፋ ይሆናል፡፡ ለዚህም ሲባል የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ለዚህ ጥናት በናሙናነት ሊመረጥ በቅቷል፡፡

### 3.2.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ከጥናቱ ርዕስና ከጥናቱ ዓላማ አኳያ ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን በተራ ቁጥር 3.2.2 ሥር በተዘረዘሩት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ውስጥ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ላይ የሚገኙት አሥር መምህራን ለዚህ ጥናት በአመቺ በናሙናነት ሊመረጡ በቅተዋል፡፡



ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

### 3.2.5. የትምህርት ቤት ሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች ናሙና አመራረጥ

እንደመምህራኑ ናሙና አመራረጥ ሁሉ፣ ከጥናቱ ርዕስና ከጥናቱ ዓላማ አኳያ በጥናቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ሚዲያ ማዕከላት ውስጥ በአስተባባሪነት በማገልገል ላይ የሚገኙት አምስት አስተባባሪዎች በአመቺ ናሙናነት ተመርጠዋል።

## 3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት በናሙናነት በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍሎች እና በየሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላቱ የተካሄዱትንና የተመዘገቡትን የምልከታ ውጤቶች፣ በደጋፊነት ከተሰበሰቡት የጽሑፍ መጠይቅና የቃለ መጠይቅ ውጤቶች ጋር በማገናዘብ፣ እንደዚሁም በአዲሱ የሦስተኛ እና የአራተኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ የተጠቆሙትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመምህራኑ ከተዘጋጁት የሴሚስተር እቅድ ጋር በማስተያየት ከክለሳ ድርሳን ከተገኙ ንድፈ ሐሳቦችና መሥፈርቶች አንፃር በዓይነታዊ (Qualitative) ትንተና ዘዴ ዘርፍ በሆነው በገላጭ ትንተና ዘዴ እና በመጠናዊ (Quantitative) ትንተና ዘዴ ተተንትኗል።

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ

ከጥናቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል:: ከፍ ሲል በምዕራፍ ሦስት በተጠቀሱት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡትን እነዚህን መረጃዎች እንደሚከተለው በሦስት ክፍሎች በመመደብ ለመተንተን ተሞክሯል፤

- የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎችና የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት፤
- የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም፣ እና
- የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ብቃት የሚወስኑ ተላውጦዎች፣

የሚሉት ሲሆኑ በእያንዳንዳቸው ዙሪያም በመረጃ የተደገፉ ዝርዝር ጥናታዊ ትንታኔዎች ቀርበዋል::

## 4.1. የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎችና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት

ይህን ርዕስ በሦስት ደረጃ ከፍለን በመተንተን እያንዳንዳቸውን በተናጠል እንመለከታለን፤

### 4.1.1. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት የተደረገ ዕቅድ

አንድ መምህር በሴሚስተር መጀመሪያ ላይ ትምህርቱን በሚያቅድበት ጊዜ እሱና ተማሪዎቹ እንዴትና በምን ዓይነት ሁኔታ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀትና መጠቀም እንዳለባቸው፣ ወጪም የሚያስፈልግ ከሆነ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግ፣ ተሠርቶ የሚያልቅበት ጊዜ፣ ለሥራው የባለሙያ እገዛ የሚያስፈልግም ከሆነ አስቀድሞ በማሰብ መርጃ መሣሪያው በተያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ደርሶ ለመማር- ማስተማር ተግባር እንዲውል በቅድሚያ ከሴሚስተር የትምህርት ዕቅድ ውስጥ አስገብቶ አብሮ ማቀድ እንደሚኖርበት ቀደም ሲል ተገልጿል:: ዕቅዱን በተሟላ መልኩ ለማከናወን ደግሞ ወቅታዊ የትምህርት መሣሪያዎች ተሟልተው መገኘት የግድ አስፈላጊ ነው:: ወቅታዊ የትምህርት መሣሪያዎች (ለትምህርት ዘመኑ ለማስተማሪያነት የተዘጋጁ መርሐ ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪ መጽሐፍ)

በሌሉበት ወይም አንዳቸው እንኳ በተጓደለበት ሁኔታ የሴሚስተሩን ትምህርት ማቀድ የማይቻል፣ ቢሞከርም እጅግ አስቸጋሪ እና ያልተሟላ ነው የሚሆነው::

ከዚህ አኳያ በጥናቱ ታላሚ የሆኑት ትምህርት ቤቶች ያላቸውን የትምህርት መሣሪያዎች ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ ቀጥሎ ቀርቧል::

ሠንጠረዥ 3፣ አዳዲስ የትምህርት መሣሪያዎች ያላቸው መምህራን፤

| የትምህርት መሣሪያዎች ዓይነት | የ3ኛ ክፍል መምህራን | | | | የ4ኛ ክፍል መምህራን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ያላቸው | | የሌላቸው | | ያላቸው | | የሌላቸው | |
| | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| መርሐ ትምህርት | - | 0% | 5 | 100% | - | 0% | 5 | 100% |
| የመምህሩ መምሪያ | - | 0% | 5 | 100% | - | 0% | 5 | 100% |
| የተማሪው መጽሐፍ | - | 0% | 5 | 100% | - | 0% | 5 | 100% |

መግለጫው እንደሚያሳየው በጥናቱ ታላሚ የሆኑት አምስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የ3ኛ እና የ4ኛ ክፍል አሥር የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን በሙሉ /100% / ወቅታዊ (አዳዲስ) የትምህርት መሣሪያዎች የሌሏቸው መሆኑን ነው::

ሠንጠረዥ 4፣ አዳዲስ የትምህርት መሣሪያዎች ባለመኖራቸው ምክንያት መምህራን የተጠቀሙባቸው አማራጮች፤

| ጠቅላላ የመምህራን ብዛት | የትምህርት መሣሪያ ዓይነቶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አሮጌ መርሐ ትምህርት | | አሮጌ የመምህሩ መምሪያ | | አሮጌ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ | |
| | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 10 | - | 0% | 1 | 10% | 9 | 90% |

አዳዲስ የትምህርት መሣሪያዎች ባለመኖራቸው ምክንያት መምህራን የሴሚስተር ዕቅዳቸውን ለማዘጋጀትም ሆነ ለዕለት ተዕለት ትምህርት ለመዘጋጀት የተጠቀሙባቸው አማራጮችን ስንመለከት ደግሞ ዘጠኙ መምህራን በአሮጌ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ሲጠቀሙ አንዱ መምህር ብቻ በአሮጌ የመምህሩ መምሪያ ተገልግሏል:: ይህ ማለት በአሮጌ የተማሪ መጽሐፍ የተጠቀሙት ዘጠኙ መምህራን አሮጌ መርሐ ትምህርትም ሆነ አሮጌ የመምህሩ መምሪያ

የሌላቸው፣ እንደዚሁም በመምህሩ መምሪያ ብቻ የተጠቀመው አንዱ መምህርም አሮጌ መርሐ ትምህርትም ሆነ አሮጌ የተማሪ መጽሐፍ ያላገኘ ሲሆን ባጠቃላይ መምህራኑ የተጠቀሙበት አሮጌ የተማሪ መጽሐፍና አሮጌ የመምህር መምሪያ ለእያንዳንዳቸው ብቸኛ አማራጭ ነው ማለት ነው::

በዚህም የተነሳ በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና ባጠቃላይም በትምህርት ቤቶቹ የአማርኛ ቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት ላይ የተፈጠረውን ክፍተት ለማነፃፀር የሚረዳን መረጃ ቀጥሎ በቀረቡት ተከታታይ ሠንጠረዦች ተመልክቷል::

መግለጫዎቹ በ1996 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ አሁን በሥራ ላይ ካለው የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ ለሁለተኛ ሲሚስተር ትምህርት የተጠቆሙት የ3ኛ እና የ4ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር እና በተጓዳኝ ደግሞ ያለወቅታዊ /አዲስ/ መርሐ ትምህርት መምህራኑ በእጃቸው ባገኙት አሮጌ የተማሪ መማሪያና የመምህሩ መምሪያ /ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መሠረት/ በመጠቀም ባዘጋጁት የሴሚስተር ዕቅድ ላይ ያቀረቡትን መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር ደረጃ በደረጃ የሚያሳዩ ናቸው::

ሠንጠረዥ 5፣ በ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ የተጠቆሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር /ሁለተኛ ሴሚስተር/

| የቋንቋ ትምህርት ክፍል ዘርፎች | የትምህርት ይዘት | የተጠቆሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|
| ንባብ | ጽሑፍን ማንባብ | - ሞዴል የግጥምና የስድ ንባብ ጽሑፎች<br>- በጉልህ የተጻፈ የዓረፍተ ነገር ሰሌዳ ወይም ፍላሽ ካርድ<br>- ለልዩ ልዩ ጉዳዮች አፈጻጸም የተዘጋጁ መመሪያዎች<br>- ሞዴል የክፍል ቤተ መጻሕፍት<br>- ሞዴል መዝገበ ቃላት<br>- የማውጫ ናሙና |
| ንግግርና ጽሕፈት | ተጠየቃዊ አስተሳሰብ | - የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን የሚያሳዩ ቃላትና ሥዕሎች<br>- መንስዔና ውጤት አመልካች ዓረፍተ ነገሮች |

| የቋንቋ ትምህርት ክፍል | የትምህርት ይዘት | የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|
| ጽሕፈት | - ከልዩ ልዩ ጽሑፎችና ንግግሮች ማስታወሻ አወሳሰድ<br>- ዓረፍተ ነገሮችን አገጣጠም አንቀጽ መጻፍ<br>- የደብዳቤ አጻጻፍ /የሰላምታ ደብዳቤ/<br>- ውጥን ሃሳብን መጨረስ | - ናሙና ማስታወሻ<br>- ሞዴል አጫጭር አንቀጾች<br>- የተጻፈ ደብዳቤ ናሙና<br>- ተጀምረው ያላለቁ ዓረፍተ ነገሮች ከተለያዩ መቋጫ ሐሳቦቻቸው ጋር የሚያሳይ ሰሌዳ |
| | አያያዦች | - ምሳሌ የሚሆኑ የተመረጡ አያያዦች |
| ንግግርና ማዳመጥ | ልዩ ልዩ ተጠየቃዊ የንግግር ሥርዓት መግለጫዎች<br>- ውይይት<br>- ክርክር<br>- ጭውውት | - የክርክር ሥርዓት<br>- የውይይት ሥርዓት<br>- የጭውውት መመሪያ |
| ንግግርና ማዳመጥ | - አንድን ሐሳብ በራስ አባባል /ፖራፍሬዝ/ ማቅረብ | - ናሙና ጽሑፍ<br>- ናሙና ንግግር |
| ሥነ-ጽሑፍ | ሥነ-ቃል<br>- ተረት<br>- ዕንቆቅልሽ<br>- ግጥም | - ከሥነ ቃሎች ጋር የሚሄዱ የፈጠራ ሥዕሎች<br>- ግልፅ የሆኑ አጫጭር ግጥሞች |

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደሚታየው በአዲሱ የ3ኛ ክፍል የሁለተኛ ሴሚስተር የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ 21 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በአጋዥነት እንዲያገለግሉ ተጠቁመዋል:: በአንጻሩ ደግሞ ቀጥሎ በቀረበው የመምህራን የሴሚስተር የትምህርት ዕቅድ ውስጥ ስድስት ያህል መርጃ መሣሪያዎች ብቻ በአጋዥነት እንዲያገለግሉ ተደርገው ቀርበዋል:: እነዚህም ቢሆኑ በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ ከተጠቀሙት ጋር የይዘትም ሆነ የቅርፅ ተመሳስሎ የላቸውም::

ሠንጠረዥ 6፣ በ2000 ዓ.ም ለ2ኛ ሴሚስተር ለ3ኛ ክፍል በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር/ከታላሚ ትምህርት ቤቶች መካከል የአንዱ በናሙናነት የተወሰደ/፤

| የትምህርት ርዕስ | የትምህርት ይዘት | የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|
| ድምፆች | ዲቃላ ድምፆች | የፊደል ገበታ የቃላት ካርዶች |
| ቁጥሮች | የአማርኛና የዐረብኛ ቁጥሮች ንፅፅር | - |
| | የቀለም ዓይነቶች | የቀለም ዓይነቶችን የሚያሳይ ሥዕል |
| ዓረፍተ ነገር | የተጓደሉ ዓረፍተ ነገሮችን አሟልቶ መጻፍና ማንበብ | ፍላሽ ካርድ |
| ሥርዓተ ነጥቦች | | - ሻሽ ቦርድ የቃላት ካርዶች<br>- ሥርዓተ ነጥቦች |
| ቃላት | ቃላትን እንደ አገልግሎታቸው መመደብ | የቃላት ካርዶች |

ከዚህ በታች ደግሞ በ4ኛ ክፍል ሁለተኛ ሴሚስተር መርሐ ትምህርት እና በክፍሉ ሁለተኛ ሴሚስተር የመምህራን ዕቅድ ላይ የተጠቀሙት መርጃ መሣሪያዎች ንፅፅር በተመሳሳይ ሁኔታ ቀርቧል::

ሠንጠረዥ 7፣ በ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር፤

| የቋንቋ ትምህርት ክፍል ዘርፎች | የትምህርት ይዘት | የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|
| ንባብ/ማዳመጥና መናገር | ልዩ ልዩ መመሪያዎች | - የተለያዩ መመሪያዎችን የሚያሳዩ ሠንጠረዦች<br>- የማስጠንቀቂያ፣ የማገጃ፣ የማሳወቂያ ምልክቶች /ለምሳሌ የመንገድ ሥነ ሥርዓት ምልክቶች፣ የጤና አጠባበቅ ቻርቶች...<br>- የማሳወቂያ ምልክቶች /የምግብ ቤት፣ የትምህርት ቤት፣ የሃይማኖት.../ |
| ንባብ | ከልዩ ልዩ መግለጫዎች የመረጃ ሐሳቦችን ማግኘት | - ቅርጻ ቅርጽ<br>- ሥዕሎች ፎግራፎች የተለያዩ የግርጌ መግለጫዎች ያሉባቸው ሥዕሎች ፎቶ<br>- ግራፎች<br>- ሠንጠረዦች<br>- ካርታዎች |

| የቋንቋ ትምህርት ክፍል ዘርፎች | የትምህርት ይዘት | የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|
| ንግግርና ጽሕፈት | ሐሳብን በራስ አባባል መግለፅ /ፓራፍሬዝ/ | - በካሴት የተቀረጹ ንግግሮች<br>- የተመረጡ ሞዴል ጽሑፎች |
| ማዳመጥና ንግግር | - ጭውውት<br>- ውይይት<br>- ክርክር | - በካሴት የተቀረጹ ጭውውቶች<br>- ጭውውትን የሚያሳዩ ሥዕላዊ መግለጫዎች<br>- ውይይትን የሚያሳዩ ሞዴል ሥዕሎች ወይም ፎቶ ግራፎች<br>- ክርክር የሚያሳዩ ሥዕላዊ መግለጫዎች<br>- ሞዴል የክርክር ጽሑፎች |
| ንግግርና ጽሕፈት | ተጠየቃዊ አስተሳሰብ<br>- ማወዳደር<br>- የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን በተለያዩ ነገሮች አሠራር መግለጽ<br>- መንስዔና ውጤት<br>- መደምደሚያ፣ ውሳኔ ሐሳብ ላይ መድረስ<br>- በሀቅና በግል አስተያየት መካከል ያለ ልዩነትን ማብራራት | - የሁለት ነገሮችን ልዩነትና ተመሳሳይነት የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ቻርቶች<br>- ተከታታይ ድርጊቶችንና ጊዜያትን የሚያሳዩ ሥዕሎች ፖስተሮች ሠንጠረዦች<br>- ፖስተሮች /ለምሳሌ ስለበሽታ አመጣጥና ስለሚያስከትለው ሁኔታ የተባለ/<br>- መደምደሚያ ወይም ውሳኔ ሐሳብ ላይ መድረስን የሚያመለክቱ ሞዴል ዓረፍተ ነገሮችና ሐሳቦች<br>- ሞዴል የግል አስተያየትና ሀቅን የሚያመለክቱ ዓረፍተ ነገሮች |
| ሥነጽሑፍ | ሥነቃል<br>- የጨዋታ ግጥሞች<br>- ተረቶች | - በምሳሌነት የሚያገለግሉ ተረቶች እንቆቅልሾች<br>- ከሥነ ቃሎቹ ጋር አብረው የሚሄዱ ደጋፊ ሥዕሎች |
| ንባብና ማዳመጥ | ማስታወሻ መያዝ | - የማስታወሻ አወሳሰድ ሞዴል |
| ጽሕፈት | ደብዳቤዎች መጻፍ<br>- የሰላምታ<br>- የማመልከቻ<br>- የሥራ<br>የመረጃ ጽሑፎች አጠቃቀም<br>የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም | - አድራሻዎች የተጻፉባቸው ፖስታዎች<br>- የሥራ ደብዳቤ ናሙና<br>- ጋዜጣ<br>- መጽሔት<br>- ማውጫ ያላቸው መጻሕፍት<br>- መዝገበ ቃላት |
| ጽሕፈት | - ዘገባ<br>- የግል የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ<br>- ጽሑፍን ማረም | - በጽሑፍ የቀረቡ ናሙና ዘገባዎች<br>- ናሙና የሕይወት ታሪክ ጽሑፍ<br>- ያልታረሙና የታረሙ ዓረፍተ ነገሮች የተጻፉበት ወረቀት |

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደሚታየው በአዲሱ የ4ኛ ክፍል የሁለተኛ ሴሚስተር መርሐ ትምህርት ውስጥ 31 ዓይነት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በአጋዥነት እንዲያገለግሉ ተጠቁመዋል:: በአንፃሩ ደግሞ ቀጥሎ በቀረበው የመምህራን የትምህርት ዕቅድ ውስጥ ሁለት መርጃ መሣሪያዎች ብቻ በአጋዥነት እንዲያገለግሉ ተደርገው ተጠቁመዋል:: በእርግጥ በመምህራኑ በተዘጋጀው የሴሚስተር ዕቅድ ላይ የተመለከቱትን የትምህርት ይዘቶች ስንመለከት ሁሉም በመርጃ መሣሪያ መደገፍ የነበረባቸው ሲሆኑ በዝግጅት ማነስ ያለመርጃ መሣሪያ ታቅደዋል:: እነዚህም ቢሆኑ በመርሐ ትምህርት ውስጥ ከተጠቆሙት ጋር ያላቸው የይዘትም የሆነ የቅርፅ ተመሳስሎ እጅግ ውስን ነው::

ሠንጠረዥ 8፣ በ2000 ዓ.ም ለ2ኛ ሴሚስተር ለ4ኛ ክፍል በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር/ከታላሚ ትምህርት ቤቶች መካከል የአንዱ በናሙናነት የተወሰደ/፤

| የቋንቋ ትምህርት ክፍል ዘርፎች | የትምህርት ይዘት | የተጠቆሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|
| ሥርዓተ ነጥቦች | ሁለት ነጥብ፣ ጥያቄ ምልክት አራት ነጥብ፣ ነጠላ ሠረዝ | - |
| ሆሄያትን ለመቅረጽ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ምልክቶች | | - |
| መስመር ጠብቆ አጻጻፍ መመሪያ | | አምስቱ መሰረታዊ ምልክቶች ____ ( ) 0 |
| የወረዳዎች ዋና ከተማ | | የደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ካርታ |
| ቃላትን ደጋግሞ በቃል መፃፍ | | - |
| ከሆሄያት ቃላትን መመሥረት | | - |
| በቃላት ውስጥ ያሉ ሆሄያት ቦታ በመቀያየር የተለያዩ ቃላት መመሥረት | | - |
| - የጭውውት መመሪያ<br>- የክርክር መመሪያ<br>- የውይይት መመሪያ | | - |
| - ዓምደ- ቃላት | | - |

ባጠቃላይ መግለጫዎቹ የሚያመለክቱት ለሁለቱም ክፍሎች በተዘጋጁት አዳዲሶቹ መርሐ ትምህርቶች ውስጥ በተዘረዘሩት የትምህርት ይዘቶችና ለይዘቶቹ መማሪያ በተጠቆሙት የቋንቋ

ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እና በመምህራኑ ያለመርሐ ትምህርት በተዘጋጁት የሴሚስተር ዕቅዶች ላይ በተጠቆሙት ይዘቶችና የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል የታየው የመጣጣም ሁኔታ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ነው:: እንዲህም ሆኖ በመምህራኑ በታቀዱት የሴሚስተር ዕቅዶች መሠረት የሚመረጡት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከየት ይገኛሉ? የሚለው ደግሞ ቀጥሎ የተነሳው ጥያቄ ነው::

### 4.1.2. በዕቅዱ መሠረት የሚመረጡት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መገኛ

የትምህርት መርጃ መሣሪያ መገኛ ምንጮች በዋነኛነት ሁለት እንደሆኑና እነዚህም በፋብሪካ ተመርተው የሚቀርቡ እና ከአካባቢ ቁሳቁስ በትምህርት ቤት ማሕበረሰብ የሚዘጋጁ እንደሆኑ ከአሁን በፊት አይተናል:: በዚህም መሠረት በጥናቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በአጋዥነት እንዲያገለግሉ ታቅደው የተዘጋጁት ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከየት ከየት እንደተገኙ ከዚህ በመከተል ቀርቧል::

በታላሚ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ምልከታ መከታተያ ቅጽ በተራ ቁጥር 7 ላይ በቀረበው ጥያቄ መሠረት ለ3ኛ እና ለ4ኛ ክፍሎች አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር፣ የተለያዩ ሥዕሎች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሽክርክሪቶች፣ ሞዴሎችና ቻርቶች ሲሆኑ የተዘጋጁትም በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች በመምህራንና በማዕከላቱ አስተባባሪዎች ነው:: ምንም እንኳ በአካባቢው ከሚገኘው የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በዕጩ መምህራን የተዘጋጁ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ኮሌጁ በስጦታ የሰጣቸው ቢሆንም፣ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጋዥነት የሚሰጡት አገልግሎት በትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ከተዘጋጁት የማይሻሉና ከአካባቢ ቁሳቁስ የተዘጋጁ እንደሆኑ ከጽሑፍ መጠይቁ ለመረዳት ተችሏል::

### 4.1.3. በትምህርት ቤቶች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ሁኔታ

በትምህርት ቤቶች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትን በተመለከተ ከታላሚ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን፣ ከሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች እና በሚዲያ ማዕከላቱ ተዘጋጅተው ከተቀመጡት መርጃ መሣሪያዎች ሁኔታ አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል:: ባጠቃላይ የመርጃ መሣሪያዎቹ ምንጮች የሚያተኩሩት መምህራኑ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት በግላቸው ባደረጉት ጥረት፣ እንዲዘጋጅላቸው ለሚዲያ ማዕከላቱ ባቀረቡአቸው ጥያቄዎች፣ እንደዚሁም ደግሞ ተማሪዎቻቸው

የሚማሩባቸውን ወይም የተማሩባቸውን የትምህርት ይዘቶች የሚያጠናክሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እንዲያዘጋጁ መምህሮቻቸው ባደረጉት የግፊት እና የማበረታታት ሁኔታ ላይ ነው::

ሠንጠረዥ 9፣ በመምህራን የተመረቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፤

| መላሾች | ብዛት | በመምህራን የተዘጋጁ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከ8 በላይ | | 5-8 | | 1-4 | | ምንም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| መምህራን | 10 | 7 | 70% | 1 | 10% | 2 | 20% | - | 0% |

ከላይ በቀረበው መግለጫ መሠረት ለመምህራኑ በጽሑፍ ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ የተገኘው መረጃ ከአሥሩ መምህራን መካከል ሰባቱ ከስምንት በላይ መርጃ መሣሪያዎች በተያዘው ዓመት ውስጥ እንዳዘጋጁ፣ አንድ መምህር ከአምስት እስከ ስምንት መርጃ መሣሪያዎች እንዳዘጋጀ እና ሁለቱ መምህራን ደግሞ ከአንድ እስከ አራት እንዳዘጋጁ ያመለክታል::

የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትን በተመለከተ ለትምህርት ቤቶቹ ርዕሰ መምህራን፣ "መምህራን የትምህርት ሚዲያ ማዕከላትን ዓላማና ጠቀሜታ ዓውቀውና አምነው ዘወትር እንዲጠቀሙባቸው ግፊት ያደርጋሉ? የመምህራኑ አመለካከትና አቋም ምንድን ነው?" ተብሎ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ ስናይ ከአምስቱ ርዕሰ መምህራን ሁለቱ፣ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው መምህራን እንዳሉ ሁሉ የዚያኑ ያህል ምንም ፍላጎት የሌላቸው ይኖራሉ ሲሉ፣ ሌሎች ሁለቱ ርዕሰ መምህራን ደግሞ የማዕከል ተሳትፎ በውጤት-ተኮር ዕቅድ ውስጥ እንዲካተት በመደረጉና ከዚያ አንፃር ግምገማ ስለሚደረግ ለመምህሩ እንደግዴታው የሚቆጠርበት ነው በማለት መልሰዋል:: ሌላኛው አንድ ርዕሰ መምህር ደግሞ የመምህራኑ ቁጥር አነስተኛ መሆኑን፣ በሳምንት 30 ክፍለ ጊዜያት ስለሚያስተምሩ ጊዜ ባይኖራቸውም ጥረት ያደርጋሉ በማለት መልስ ሰጥተዋል::

በሌላ በኩል በሚዲያ ማዕከላት ምልከታ ወቅት በዚህ ጥናት አቅራቢ የተስተዋለው ነገር በማዕከላቱ ውስጥ ያሉት /የታዩት/ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት ዝቅተኛ መሆኑንና መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ የማይጣጣሙ መሆናቸው ነው::

የመምህራኑ ምላሽና ከርዕሰ መምህራኑ የተገኙት መረጃዎች ከማዕከላቱ ምልከታዎች ከታዩት ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ሲነፃፀር፣ መምህራኑ በትምህርት ዘመኑ አዘጋጀን የሚሏቸው መርጃ መሣሪያዎች ብዛት እና በማዕከላቱ የታዩት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት ያለመመጣጠን ጉዳይ የመምህራኑን ምላሽ ትክክለኛነት አጠያያቂ ያደርገዋል::

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንዲዘጋጁላቸው ለማዕከላት አስተባባሪዎች ጥያቄ የሚያቀርቡት መምህራን ምን ያህል እንደሆኑና ጥያቄዎቹን የተቀበሉ የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎችን ብዛት ቀጥሎ ከቀረበው መግለጫ እንመለከታለን::

ሠንጠረዥ 10፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያ እንዲዘጋጅ ከመምህራን ቀርበው በሚዲያ ማዕከል የተመዘገቡ ትዕዛዞች መጠን፤

| መላሾች | ብዛት | ጥያቄ ያቀረቡ መምህራን ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አብዛኞቹ | | ግማሽ ያህሉ | | ጥቂቶች | | ማንም የለም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች | 5 | - | - | 1 | 20% | 2 | 40% | 2 | 40% |

መግለጫው እንደሚያስረዳን በትምህርት ዘመኑ ልዩ ልዩ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንዲዘጋጅላቸው ለማዕከላቱ አስተባባሪዎች በመምህራን ለቀረበ ጥያቄ በአምስቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ አምስት የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች መካከል አንዱ ግማሽ ያህል መምህራን ጥያቄ አቅርበዋል ብሏል:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 20% መሆኑ ነው:: ሁለቱ የማዕከላት አስተባባሪዎች ደግሞ በጣም ጥቂት መምህራን የይዘጋጅልን ጥያቄ አቅርበዋል ብለው መልስዋል:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 40% ይሆናል:: ሌሎች ሁለቱ ደግሞ ምንም የይዘጋጅልኝ ጥያቄ አላቀረቡም በማለት መልስ ሰጥተዋል:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 40% መሆኑ ነው:: ከመግለጫው አጠቃላይ ሁኔታ መገንዘብ የሚቻለው ዓቅደው ወይም አስበውበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ እንዲዘጋጅላቸው ለሚዲያ ማዕከላት ትዕዛዝ የሚያቀርቡ መምህራን ቁጥር በጣም ጥቂት መሆኑንና በአብዛኞቹ መምህራን ዘንድ የዚህ ዓይነት ጥያቄ /ትዕዛዝ/ ማቅረብ እንብዛም ያልተለመደ መሆኑን ነው::

#### 4.1.4. በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ሂደት የተማሪዎች ተሳትፎ

ተማሪዎች በአስተማሪዎቻቸው ወይም በሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች የተዘጋጁትን አሊያም በቀጥታ ከፋብሪካ ተመርተው የቀረቡትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጠብቀው ብቻ እንዲጠቀሙ አይመከርም:: አቅማቸውና ችሎታቸው በፈቀደ መጠን ደረጃቸውን የጠበቀ የትምህርት መርጃ መሣሪያ እንዲያዘጋጁ ያስፈልጋል:: ከዚህም አኳያ በመምህራኑ የተደረጉት ጥረቶች ምን ያህል እንደሆኑ ቀጥሎ ከቀረበው መረጃ እንረዳለን::

ሠንጠረዥ 11፣ ተማሪዎች በመርጃ መሣሪያዎች ዝግጅት እንዲሳተፉ በመምህራን በኩል የተደረገ ጥረት፤

| መላሾች | ብዛት | የመምህራኑ ጥረት መጠን | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ ጥረት | | ዝቅተኛ ጥረት | | ምንም ጥረት | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| መምህራን | 10 | - | - | 4 | 40% | 6 | 60% |

ከመረጃው እንደምንገነዘበው በዚህም በኩል የተደረገው ጥረት ዝቅተኛ /40%/ መሆኑንና ብዙዎቹ መምህራን /60%/ ተማሪዎቻቸው በመርጃ መሣሪያ ዝግጅት እንዲሣተፉ ምንም ዓይነት ጥረት ያላደረጉ መሆኑን ነው::

### 4.2. የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም፤

መምህራን በዕለት ተዕለት የማስተማር ተግባራቸው ወቅት የሁሉንም ተማሪ ፍላጎትና ስሜት የሚያሟሉ፣ ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በክፍል ውስጥ ዘወትር ይጠቀሙ /አይጠቀሙ እንደሆነ ለመናገር በተወሰነ የሁለትና የሦስት ክፍለ ጊዜያት የክፍል ውስጥ ምልከታ ብቻ የተሟላ መረጃ ተገኝቷል ለማለት አያስደፍርም:: ምክንያቱም በዓመቱ ወይም በሴሚስተሩ ውስጥ ከሚኖሩት ክፍለ ጊዜያት ቢያንስ 30% ያህል ጊዜ ምልከታ መካሄድ እንዳለበት ጥናቶች ያመለክታሉ::

ሆኖም ግን የመምህራኑን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ ተጨባጭ መረጃ ለማግኘት ከክፍል ምልከታ የተሻለ አማራጭ ባለመኖሩ አጥኚው ባለው ውስን ጊዜ በተቻለው መጠን በአምስቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ ታላሚ የ3ኛ እና የ4ኛ ክፍሎችን አማርኛ መምህራን ሲያስተምሩ በክፍል ውስጥ በመገኘት እያንዳንዳቸውን ለሦስት ሦስት

ክፍለ ጊዜያት ለመመልከት ችሏል:: ከዚህም በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሰውን የመረጃ ተአማኒነት ሥጋት ለመቀነስ እንዲረዳ በማሰብ የመምህራንን የሴሚስተርና የዕለት የትምህርት ዕቅድ በመመልከት በሴሚስተሩ ዕቅድ ላይ የተጠቀሱት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ጋር መጣጣም አለመጣጣማቸውን ለማገናዘብ ሞክሯል::

ከላይ እንደተገለጸው በአጠቃላይ ምልከታ የተደረገባቸው ሠላሳ ክፍለ ጊዜያት ናቸው:: ይኸውም ለ3ኛ ክፍል አምስት ምድቦች (Sections) አሥራ አምስት ክፍለ ጊዜያት ምልከታ ሲደረግ፣ ለ4ኛ ክፍል አምስት ምድቦችም እንደዚሁ አሥራ አምስት ክፍለ ጊዜያት ምልከታ ተካሂዷል:: በዚህም መሠረት ምልከታ ከተካሄደባቸው ሠላሳ ክፍለ ጊዜያት መካከል መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለምን ያህል ጊዜ ተጠቅመውባቸዋል የሚለውን ጥያቄ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ውስጥ ለማሳየት ይሞከራል::

ሠንጠረዥ 12፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ ከተካሄደባቸው ሠላሳ ክፍለ ጊዜያት መካከል መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት ብዛት፤

| ምልከታ የተካሄደበት ክፍሎች ደረጃ | ምልከታ የተካሄደባቸው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜያት ብዛት | መምህራን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት ብዛት | % | መምህራን መርጃ መሣሪያዎች ያልተጠቀሙባቸው ክፍል ጊዜያት ብዛት | % |
|---|---|---|---|---|---|
| 3ኛ | 15 | 4 | 26.67% | 11 | 73.3% |
| 4ኛ | 15 | 3 | 20% | 12 | 80% |

ከላይ የቀረበው መረጃ የሚያሳየው በአምስቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች በ3ኛ ክፍል አምስት ምድቦች በተደረገው የአሥራ አምስት የምልከታ ክፍለ ጊዜያት 26.67% ያህሉ ብቻ በመርጃ መሣሪያ የተደገፈ ትምህርት ሲሰጥ 73.3% ያህሉ ግን ያለመርጃ መሣሪያ ድጋፍ የሚሰጥ መሆኑን፣ በ4ኛ ክፍልም እንደዚሁ በተደረገው ተመሳሳይ የምልከታ ክፍለ ጊዜያት 20% ብቻ በመርጃ መሣሪያ በተደገፈ ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን ቀሪው 80% ግን ያለመርጃ መሣሪያ በቃል ብቻ የሚሰጥ ትምህርት እንደሆነ ነው:: በምልከታው ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ጥራትና መጠን በተመለከተ በየክፍል ውስጥ መከታተያ ቅጽ

በተራ ቁጥር 17 እና 18 ሥር በቀረቡት ጥያቄዎች መሠረት እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል::

ሠንጠረዥ 13፣ በምልከታ ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጥራት፣

| የክፍል ደረጃ | አገልግሎት ላይ የዋሉ መርጃ መሣሪያዎ ብዛት | የጥራት ደረጃ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ጥሩ | በጣም ጥሩ | ጥሩ | በቂ | አነስተኛ |
| 3ኛ | 4 | - | - | 1 | 1 | 2 |
| 4ኛ | 3 | - | - | 1 | 1 | 1 |

መግለጫው የሚያስገነዝበው በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች መምህራን የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የጥራት ደረጃ ባብዛኛው አነስተኛ እንደሆነና የተወሰኑት ብቻ በ"ጥሩ" እና በ"በቂ" ደረጃ ላይ መገኘታቸውን ነው::

በዚህ ጥናት ውስጥ በተራ ቁጥር 2.3.2. ላይ Aggarwal (1996:157) የጥሩ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባሕሪያት ብለው ካስቀመጡዋቸው አሥር ነጥቦች መካከል አንዱ፣ "ጥሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በክፍል ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ በሚታይ ሁኔታ ሰፋና ተለቅ ባለ መጠን መዘጋጀት ይኖርባቸዋል::" የሚል ነው ገጽ -- ይመልከቱ/ በዚህም መሠረት የዚህ ጥናት አቅራቢ በክፍል ምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉትን የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን /ስፋታቸውንና ጎልተው የመታየታቸውን ሁኔታ/ ደረጃ በማዘጋጀት በሚከተለው ሠንጠረዥ ለማሳየት ሞክሯል:: የመጠን ደረጃውም "እጅግ በጣም ሰፊና ጉልህ" ፣ "በጣም ሰፊና ጉልህ"፣ "በቂ" እና "አነስተኛ" በሚሉት ገላጭ ቃላት እንዲለካ ተደርጓል::

ሠንጠረዥ 14፣ በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን /ስፋትና ጥበት/፤

| የክፍል ደረጃ | በአገልግሎት ላይ የዋሉ መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | በአገልግሎት ላይ የዋሉ መርጃ መሣሪያዎች መጠን | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ሰፊና ትልህ | በጣም ሰፊና ትልህ | በቂ | አነስተኛ |
| 3ኛ | 4 | - | 1 | 2 | 1 |
| 4ኛ | 3 | - | 1 | 2 | - |

መግለጫው የሚያሳየው በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በመማር - ማስተማር ሂደት ወቅት መምህራን የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠን /ስፋትና ጥበት/ ደረጃ ሲሆን፣የመርጃ መሣሪያዎቹ መጠንም በየክፍል ደረጃው ሲታይ በጣም ሰፊና ትልህ የሆኑ አንድ አንድ ብቻ ሲሆኑ፣ ከዚያ በታች በቂ የሚባሉት ደግሞ በየክፍል ደረጃው ሁለት ሁለት ብቻ ናቸው:: እንደዚሁም አነስተኛ መጠን ያለው የትምህርት መርጃ መሳሪያ በ3ኛ ክፍል ላይ አንድ ብቻ መሆኑን ሠንጠረዡ ያሳያል::

ባጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሁለት ተከታታይ ሠንጠረዦች ለመረዳት እንደሚቻለው አብዛኞቹ መምህራን በክፍል ውስጥ ለማስተማሪያነት የሚጠቀሙባቸው መርጃ መሣሪያዎች በጥራትም ሆነ በመጠን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሆኑ ነው:: የመርጃ መሣሪያዎቹ ጥራት መጓደል ተነሳስኦት ከማሳጣቱም በላይ በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ፍላጎት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል:: እንደዚሁም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን፣ ማለትም ስፋት ያለመኖርና ትልህ ሆኖ ያለመታየት በተለይ ከመርጃ መሣሪያዎች ርቀው ከኋላ ለሚቀመጡ ተማሪዎች በግልፅ ስለማይታይ በመርጃ መሣሪያው አጋዥነት ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ሊያዛባባቸው ይችላል::

## 4.2.1. በአገልግሎት ላይ የዋሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት

የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች የተጠቀሙባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዕለቱ ሊሰጥ የታቀደውን ረቂቅ የትምህርት ይዘት ተጨባጭና ግልፅ ከማድረግ አኳያ ምን ያህል ተገቢነት እንዳላቸው በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት ለመቃኘት ተሞክሯል:: የተገቢነት ደረጃውም "እጅግ በጣም ጥሩ"፣

"በጣም ጥሩ"፣ "ጥሩ"፣ "በቂ" እና "አነስተኛ" በሚሉት ገላጭ ቃላት እንዲለካ ተደርጓል:: በዚህም መሠረት በክፍል ውስጥ መከታተያ ቅፅ ተራ ቁጥር 12 ከቀረበው ጥያቄ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው ተተንትኗል::

ሠንጠረዥ 15፣ በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ተገቢነት፤

| የክፍል ደረጃ | [redacted]አገልግሎት ላይ የዋለ መርጃ መሣሪያ ብዛት | በአገልግሎት ላይ የዋሉ መረጃ መሣሪያዎች ተገቢነት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ጥሩ | በጣም ጥሩ | ጥሩ | በቂ | አነስተኛ |
| 3ኛ | 4 | - | 3 | - | 1 | - |
| 4ኛ | 3 | - | 1 | 1 | 1 | |

አብዛኞቹ መምህራን እጅግ ውስን በሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አልፎ አልፎ ቢጠቀሙም፣ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ከማሳካት አኳያ የተደረገው የአመራረጥና የአጠቃቀም ብቃት የትምህርት ሚዲያዎችን ተገቢነት የሚያንፀባርቅ ነው:: በአንፃሩ ተገቢ ያልሆነ አመራረጥና አጠቃቀም የጥቂት መምህራን የቅድመ ዝግጅት ብቃት ማነስን ያንፀባርቃል::

የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ በጥቅሉ ይኸን ያህል ካነሳን በክፍል ምልከታ ወቅት እና ከመምህራን የሴሚስተር ዕቅድ መረጃዎች በመነሳት ለመማር-ማስተማር ሂደት በአጋዥነት በአገልግሎት ላይ የዋሉትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዓይነት ከፋፍለን ለማየት ሞክረናል::

### 4.2.2. የመምህራ ተኣማኒ በሆኑ የትምህርት መሣሪያዎች (Real objects) የመጠቀም ልምድ

እውነተኞቹን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም ቶሎ ሊረሱ የሚችሉትን ረቂቅ የሆኑ አስተሳሰቦችን፣ የነገሮችን እንቅስቃሴ፣ የነገሮችን ስፋት፣ ጥልቀት፣ ክብደት፣ ጠረን፣ ጣዕም፣ ስሜት፣ ቀለም፣ ጊዜ እና የመሳሰሉት ለግንዛቤ አስቸጋሪ የሚሆኑትን ነገሮች በግልፅና በተጨባጭ ከማስረዳት አኳያ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው Bowen (1982:1) ይገልፃሉ:: ከተቻለ አዲስና ወጥ በሆነ ተኣማኒ የሆኑ የትምህርት ልምድን ተጠቅም ማስተማር ሌሎች ወካይ

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ከመጠቀም ይልቅ የተሻለ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ላይ ተመልክቷል::

በዚህም መሠረት የክፍል ውስጥ ምልከታ በተካሄደበት ወቅት የተስተዋሉትንና የተመዘገቡትን ተኣማኒ የሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እና በመምህራኑ ከተዘጋጁት የ2000 ዓ.ም ሁለተኛ ሴሚስተር የ3ኛ እና 4ኛ ክፍል የአማርኛ ትምህርት ዕቅድ መካከል የአንዱ ትምህርት ቤት ተወስዶ ከየርዕሶቹ አንፃር የተጠቆሙትን ተኣማኒ የሆኑትን ብዛት ለመቃኘት ተሞክሯል::

ሠንጠረዥ 16፣ በክፍል ምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት ከዓይነት አንጻር ሲታይ፤

| የክፍል ደረጃ | በአገልግሎት ላይ የዋለ የመርጃ መሣሪያዎች ብዛት | በአገልግሎት ላይ የዋሉ መርጃ መሣሪያዎች ዓይነትና ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ተኣማኒ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ብዛት | ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት |
| 3ኛ | 4 | 1 | 3 | - |
| 4ኛ | 3 | 1 | 2 | - |

ከመረጃው መገንዘብ የሚቻለው በክፍል ምልከታው ወቅት ለ3ኛ ክፍል የመማር ማስተማር ሂደት መምህራኑ ከተጠቀሙባቸው 4 የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል አንዱ ተኣማኒ የትምህርት መሣሪያ ሲሆን፣ ለ4ኛ ክፍል ከቀረቡት 3 የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደዚሁ አንዱ በተኣማኒ የትምህርት መሣሪያ ላይ የተመሠረተ ነው:: እነዚህንም በዝርዝር ስናይ ለ3ኛ ክፍል የቀረበው ከአምስቱ ትምህርት ቤቶች በአንደኛው ላይ በተካሄደ የክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት የትምህርቱ ርዕስ ክርክር ስለነበር ክርክሩን እንዲያቀርቡ የተደረጉት ተማሪዎችን እንደ ዕውነተኛ የትምህርት መርጃ በመቁጠር ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በውይይት የትምህርት ርዕስ ላይ ትምህርት በተሰጠበት ሌላ ትምህርት ቤት የውይይቱ መሪዎችና ተካፋዮች የሆኑትን ተማሪዎች እንደ ዕውነተኛ የትምህርት መርጃ መሣሪያ በመቁጠር የተቀመረ ስሌት ነው::

ሠንጠረዥ 17፣ በ2000 ዓ.ም. ሁለተኛ ሴሚስተር ከታላሚ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ከተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዕቅዶች ውስጥ የተጠቆሙት የትምህርት ሚዲያ ብዛት በዓይነት፤

| የክፍል ደረጃ | በአገልግሎት ላይ የዋለ መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | ሲሠሩ የታቀዱ መርጃ መሣሪያዎች ዓይነት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ተአማኒ የሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ብዛት | ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት |
| 3ኛ | 6 | - | 6 | - |
| 4ኛ | 2 | - | 2 | - |

ከዚህ በላይ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው በተያዘው የትምህርት ዘመን ሁለተኛ ሴሚስተር፣ ከታላሚ ትምህርት ቤቶች በአንደኛው ለሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ከታቀዱት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል ዕውነተኛ ነገርን የሚጠቁም አንድም የትምህርት መርጃ መሣሪያ ያለመኖሩን ነው::

### 4.2.3. የመምህራን በዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ልምድ

ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በሁሉም የትምህርት እርከኖች ለሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች የሚያገለግሉ ቢሆኑም በተለይም ለመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል የቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን አቅልሎና ተጨባጭ አድርጎ በማቅረብ ሂደት ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው (Harmer 2001:14):: መምህራን ከየትኛውም የትምህርት መርጃ መሣሪያ ዓይነት ይልቅ በዕይታዊ መርጃ መሣሪያ በመታገዝ ማስተማር ይቀላቸዋል፤ ያዘወትራሉም:: በተለይም ሥዕሎች፣ ቻርቶች፣ ፍላሽ ካርዶች ሰሌዳዎች እና የመሳሰሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በቀላሉ ሊዘጋጁና ሊቀርቡ ይችላሉ::

በዚህም መሠረት ከዚህ በላይ በተከታታይ ከቀረቡት ሠንጠረዦች መካከል በሠንጠረዥ 16 ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በክፍል ምልከታ ወቅት ለ3ኛ ክፍል በአገልግሎት ላይ ከዋሉት አራት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል ሦስቱ ዕይታዊ የትምህርት መሣሪያዎች መሆናቸውን ነው:: እንደዚሁም ለ4ኛ ክፍል በአገልግሎት ላይ የዋሉት ሦስት ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ናቸው:: በተመሳሳይ ሁኔታ በሠንጠረዥ 17 ከተጠናቀረው መረጃ እንደምንገነዘበው በተያዘው የትምህርት ዘመን ከታላሚ ትምህርት ቤቶች

በአንደኛው የታቀዱት ስድስት የ3ኛ ክፍል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ እንደዚሁም ሁለት የ4ኛ ክፍል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በሙሉ ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል::

### 4.2.4. የመምህራን በድምፃዊ እና በድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ልምድ

ድምፃዊ እና ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም መምህሩ የማስተማር መርሖዎችን ማለትም፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ፣ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ እና በተግባር መማር የሚሉትን ዓይነት እንዲከተል ከማስቻላቸውም በተጨማሪ በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የትምህርት አቀባበልና ትኩረት አሰጣጥ ላይ ዘላቂነት ያለው ምቹ ዓውድ በመፍጠር የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱን ማራኪና ምቹ ከማድረጋቸውም በላይ የመምህሩን የሥራ ጫና ያቃልላሉ Heinich et al. (196:22)፣ Aggarwal (1996:154)::

በዚህም መሠረት በቦንጋ ከተማ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች በሚሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት በተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታም ሆነ በመምህራኑ በተዘጋጁ የ2000 ዓ.ም. ሁለተኛ ሴሚስተር በሁለቱም ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዕቅዶች ውስጥ አንድም ድምፃዊ እና የድምፃዊ ወዕይታዊ የቋንቋ መርጃ መሣሪያ አልተጠቀሰም፤ ሲጠቀሙም አልታየም:: በርግጥ እዚህ ላይ መካድ የሌለበት ነገር ሬዲዮ ያላቸው ትምህርት ቤቶች ማለትም ባርታ እና ባንዲራ ትምህርት ቤቶች የትምህርት በሬዲዮ ሥርጭት አገልግሎት በመጠቀም ያስተምሩበታል:: ሌሎች ሦስቱ ትምህርት ቤቶች /ግራዝማች ጳውሎስ፣ ሽታ እና ካያ ኬላ/ ሬዲዮ ስለሌላቸው የትምህርት በሬዲዮ ሥርጭት አገልግሎት ተጠቃሚ አይደሉም:: ይህንንም ይበልጥ ለማረጋገጥ ስለድምፃዊ እና ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መኖር /አለመኖርን በሚመለከት ለርዕሠ መምህራን ለቀረበላቸው የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ርዕሰ መምህራኑ የሰጡትን መልስ እንመልከት::

ሠንጠረዥ 18፣ ድምፃዊ እና ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያን በሚመለከት ከርዕሠ መምህራን የተገኘ መረጃ፤

| ጥያቄ ተራ.ቁጥር | ጥያቄዎች | የትምህርት ቤቶቹ ርዕሰ መምህራን | የተሰጡት መልሶች |
|---|---|---|---|
| 22 | በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሬዲዮ አለ? ምን ያህል? ካለስ ይሠራል? | ግራዝማች ጳውሎስ | - ሬዲዮ የለንም:: |
| | | ባርታ | - አንድ ሬዲዮ አለን ይሠራል:: |
| | | ሸታ | - ነበረን ተሰርቆብናል:: |
| | | ባንዲራ | - ሬዲዮ ካሴት አለን ለሬዲዮም ያገለግላል:: |
| | | ካያኪላ | - ሬዲዮ ካሴት ነው ያለን፣ የሚሠራውም በካሴት ብቻ ነው:: |
| 23 | በትምህርት ቤቱ ውስጥ ቴሌቪዥን አለ? ካለስ ይሠራል? | ግራዝማች ጳውሎስ ባርታ እና ሸታ | አለን በዲሽ የሚሠራ ነው:: |
| | | ባንዲራ እና ካያኪላ | የለንም:: |

ከርዕሠ መምህራኑ መልስ መረዳት እንደሚቻለው ሬዲዮና ቴሌቪዥን ያላቸው ትምህርት ቤቶች ባላቸው መሣሪያ በመጠቀም ተጨባጭና ማራኪ ትምህርት ማስተማር ሲችሉ በዕቅዳቸው ውስጥም ሆነ በመማሪያ ክፍሎቻቸው ሲጠቀሙ አልታየም:: ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም ከማያስችሉ ችግሮች አንደኛው የኤሌክትሪክ ኃይል ያለመኖር እንደሆነ ቢታወቅም፣ እነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚገኙበት ከተማ የሃያ አራት ሰዓት የመብራት አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ነው:: ትምህርት ቤቶቹም የኤሌክትሪክ መስመር የተዘረጋላቸው መሆኑን አጥኚው በምልከታው ወቅት አረጋግጧል:: እነዚህ በሬዲዮ ካሴትና በቴሌቪዥን የመጠቀም ሰፊ ዕድል ያላቸው ትምህርት ቤቶች በአጋጣሚው ባለመጠቀም ከሌሎች ሬዲዮም ሆነ ቴሌቪዥን ከሌላቸው ትምህርት ቤቶች እኩል ተጠቃሚ ያለመሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል::

### 4.2.5. የመምህራን በሕትመት ውጤቶች የመጠቀም ልምድ

የሕትመት ውጤቶች ሲባል መርሐ ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪ መጽሐፍ እንደዚሁም ለልዩ ልዩ የቋንቋ ትምህርት ክሂሎት ማዳበሪያ የሚያገለግሉ ተጨማሪ የንባብና የመልመጃ መጻሕፍትንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል:: ከዚህ አንጻር የቦንጋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን በሕትመት ውጤቶች የመጠቀም ልምዳቸው ሲታይ መምህራን በአብዛኛው የሚጠቀሙባቸው አሮጌ /አንዳንዶቹ የሕትመት ዘመናቸው በግልፅ የማይታወቅ/ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ እንደሆነ በምልከታ ወቅት

በተደረገው ቅኝት ለማረጋገጥ ተችሏል:: ከዚህም በተጨማሪ ለርዕሠ መምህራን ከቀረበው ቃለመጠይቅ የተገኙትን ምላሾች መመልከት ይቻላል::

ሠንጠረዥ 19፣ የማስተማሪያ መጻሕፍት ዕጥረትን በሚመለከት የርዕሠ መምህራን ምላሽ፤

| ጥያቄ ተራ ቁጥር | ጥያቄ | የትምህርት ቤቶቹ ርዕሰ መምህራን | የተሰጡት መልሶች |
|---|---|---|---|
| 32 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ መጻሕፍት እጥረት አለ? | ግራዝማች ጳውሎስ | - የ3ኛ ክፍል መጠነኛ ዕጥረት አለብን::<br>- የ4ኛ ክፍል ያለችን አንድ መጽሐፍ የተቀዳደደች በመሆኑ ሙሉ ገጽ እንኳ የላትም:: |
| | | ባርታ | - በጣም ዕጥረት አለ በጣም በቆየ ሕትመት ነው የሚያስተምሩበት:: |
| | | ሽታ | ዕጥረት ብቻ ሳይሆን ፈፅሞ የለንም ማለት ይቻላል:: |
| | | ባንዲራ | - ዕጥረት በከፍተኛ ደረጃ አለ:: |
| | | ካያኪላ | በተለይ 4ኛ ክፍል ያለን አንድ የመምህሩ መምሪያ ብቻ ነች:: |

ከመግለጫው መረዳት እንደሚቻለው በሁሉም ትምህርት ቤቶች የመማሪያ መጻሕፍት ዕጥረት በመኖሩ የተነሳ መምህራኑ እንደልባቸው በሕትመት ውጤቶች መጠቀም አልቻሉም፤ ተማሪዎቻቸውንም ማለማመድ አልቻሉም:: በተለይም የ4ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ፈፅም ያለመኖር የአምስቱም ትምህርት ቤቶች የጋራ ችግር ነው:: የዚህ ጥናት አቅራቢ በምልከታው ወቅት በተለይ በሽታ ትምህርት ቤት ሦስት የ3ኛ ክፍል መምህራን አንድ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለሦስት እየተቀባበሉ ተራ በተራ ሲያስተምሩ ለማየት ችሏል:: እንደዚህ ዓይነት የጎላ የመጻሕፍት ዕጥረት በትምህርት ቤቶቹ እየታየ የተማሪ መጽሐፍ ጥመርታ ምን ያህል ነው ተብሎ ለርዕሠ መምህራኑ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁሉም የመለሱት ምንም በሌለበት ስለጥመረታ መናገር አንችልም ነው: ከዚህም ሌላ በአምስቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የ3ኛ እና የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሌሎች የሕትመት ውጤቶች በመታገዝ ሲያስተምሩ አልታዩም:: በሴሚስተር ዕቅዳቸውም ውስጥ የተካተተ ተጨማሪ የማስተማሪያ የሕትመት ውጤት የለም::

በሌላም በኩል በትምህርት ቤቶቹ አስተዳደርም ሆነ በመምህራን እነዚህን ዕጥረት ያለባቸውን የትምህርት መሣሪያዎች በግዥም ሆነ በሌላ መንገድ ለማግኘት ወይም ደግሞ ያሉትንም ቢሆን በፎቶ ኮፒ አባዝቶ በመጠረዝ ለማዳረስ የተደረገ ጥረት የለም::

### 4.2.6. የመምህራን በተለያዩ ሠሌዳዎች የመጠቀም ልምድ

መማሪያ ክፍሎች በተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መሟላትና መዋብ እንደሚኖርባቸው ይታመናል:: እነዚህም መርጃ መሣሪያዎች የተለያዩ ሠሌዳዎችን ያካትታሉ:: በ Aggarwal (1996:161) እንደተጠቀሰው አንድ መማሪያ ክፍል ከጠመኔ ሠሌዳ በተጨማሪ ሊኖሩት የሚገባው የሠሌዳዎች ዓይነት የተለያዩ ትምህርታዊ ማስታወቂያዎች የሚለጠፉበት የማስታወቂያ ሠሌዳ፣ የተለያዩ ፍላሽ ካርዶች፣ ሥዕሎች ፎቶ ግራፎች ወዘተ የሚሰቀሉበት ከወፍራም ሱፍ ጨርቅ የተሰራ ሠሌዳ እና ወይም ሻሽ ሠሌዳ ብረት-ነክ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚጣበቁበት መግነጢዊ ሠሌዳ ይገኙበታል:: ምልከታ በተካሄደባቸው የመማሪያ ክፍሎች በተደረገው ቅኝት ከጠመኔ ሠሌዳ በስተቀር ከላይ የተጠቀሱት ሠሌዳዎች ፈጽሞ የለም::

ከዚህም በተጨማሪ ርዕሠ መምህራን ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እንዳረጋገጡት፣ ከጥቁር ሠሌዳዎች በስተቀር ሌሎች ሠሌዳዎች በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ እንደሌሉ ነው:: እንደዚሁም ስለ ጠመኔ ሠሌዳ ዕጥረት መኖር/ አለመኖር ለቀረበላቸው ጥያቄ የአራት ትምህርት ቤት ርዕሠ መምህራን የጥቁር ሠሌዳ ዕጥረት መኖሩን ሲገልጹ የአንዱ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ብቻ ባላቸው ክፍሎች ልክ ጠመኔ ሠሌዳዎች ስላሉአቸው የጎላ የዕጥረት ችግር እንደሌለባቸው ገልጸዋል:: ዕጥረት አለብን ካሉት ርዕሰ መምህራን አንዱ እንዲያውም ያሉን የጠመኔ ሠሌዳዎች የተላለጡ እና ሲጻፍባቸው ጠመኔ የማይቀበሉና መጠናቸውም አነስተኛ በመሆኑ እየጠገንን ነው የምንጠቀመው በማለት ገልጸዋል::

መምህራኑ የረጅም ዘመን የመምህርነት ልምደ ያላቸው በመሆኑ የጠመኔ ሠሌዳ አጠቃቀም ልምድ አልጎደለባቸውም:: አጥኚው እንዳስተዋለው የቸገራቸው ነገር የጠመኔ ሠሌዳዎቹ መጠን ማነስና ማርጀት ነው:: በሌላ በኩል ግን በየመማሪያ ክፍሉ ግድግዳ ላይ እንደነገሩ ተመስቃቅለው የተሰቀሉትንና በየግድግዳው ጥግ ወለል ላይ የተጣሉትን ልዩ ልዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን፣ የተለያዩ ሠሌዳዎችን በማዘጋጀት በሥርዓት መስቃቀልና መለጣጠፍ

ከመምህራኑ የሚጠበቅ ተግባር ነው:: በርግጥ እንደመግነጢሳዊ ሠሌዳ ዓይነት በፋብሪካ የሚመረት ሠሌዳ ማግኘት ከመምህራንም ሆነ ከትምህርት ቤቱ ዓቅም በላይ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን በቀላሉ በሚዲያ ማዕከላትና በመምህራን ዓቅም ሊሰሩ የሚችሉትን እንደ ሻሸ ሠሌዳ እና ማስታወቂያ ሠሌዳ ያሉትን በማዘጋጀት እነዚህ የተመሰቃቀሉትንና የወዳደቁትን መርጃ መሣሪያዎች እንደሚታዩ አድርጎ በዓይነትና በሥርዓት ማኖር ይቻል ነበር:: ይህም የክፍሉን ውበት ከመጠበቁም በላይ የተማሪዎችን ስሜት በማነቃቃትና ፍላጎታቸውን በመቀስቀስ ረገድ ጥሩ ሚና ይኖረው ነበር:: ነገር ግን ከዚህ አኳያ የመምህራኑ በሠሌዳዎች የመጠቀም ልምድ ዝቅተኛ መሆኑ በጥናቱ ወቅት ተረጋግጧል::

## 4.3. የመምህራንን የመርጃ መሣሪያ አዘጋጃጀትና አጠቃቀም ብቃት የሚወስኑ ተላውጦዎች (Variables)

በዚህ ክፍል በጥናቱ የተካተቱት ታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ምን እንደሚመስልና የመርጃ መሣሪያዎቹ የብቃት ደረጃም በምን በምን መልክ ሊገለጽ እንደሚችል በዝርዝር ቀርቧል:: በዚህም ዙሪያ የተሰበሰቡት መረጃዎች በሁለት ተከፍለው ተብራርተዋል:: እነዚህም በግለሰባዊ ተላውጦዎች ዙሪያ እና በተቋማዊ /በትምህርት ቤት ደረጃ/ ባሉ ተላውጦዎች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው::

### 4.3.1. ግለሰባዊ ተላውጦዎች

#### *ሀ. የመምህራን የሚዲያ ቅድመ ሥልጠና*

ለሚዲያ-ነክ ተግባራዊ ድርጊቶች እድገትም ሆነ ውድቀት ዕውቀትና ብቃት በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው:: የሚዲያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ብቃትም የሚጎለብተው ለመምህራን በሚሰጡ ቅድመ ሥራ ሥልጠናና የሥራ ላይ ሥልጠናዎች አማካኝነት እንደዚሁም ባገኙት ሥልጠና መሠረት በሥራ ላይ በሚያደርጉት ተግባራዊ ልምምድ ነው::

የሚቀጥለው መረጃ የመምህራንና የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎችን የትምህርት ደረጃ የሚመለከት ነው::

ሠንጠረዥ 20፣ የመምህራንና የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች የትምህርት ደረጃ፤

| መላሾች | ብዛት | የትምህርት ደረጃ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 12ኛ ክፍል የጨረሰ | | 12+TTI | | 1ኛ ዓመት ኮሌጅ | | ዲፕሎማ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| መምህራን | 10 | - | - | 7 | 70% | - | - | 3 | 30% |
| የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች | 5 | - | - | 2 | 40% | - | - | 3 | 60% |

ከዚህ በላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ ውስጥ ሁለት ነገሮችን መገንዘብ እንችላለን:: የመጀመሪያው ሁሉም መምህራን የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም /TTI / ምሩቃን መሆናቸውን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከእነዚሁ መካከል በክረምት ኮርስ እና በርቀት ትምህርት የተወሰኑት በተለያየ የትምህርት ዓይነት ዲፕሎማ ያገኙ መሆናቸውን ነው::

ከሚቀጥለው ሠንጠረዥ የመምህራኑን የሚዲያ ሥልጠና በሚመለከት በቂ መረጃ ማግኘት ይቻላል::

ሠንጠረዥ 21፣ የመምህራንና የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች መደበኛ የሚዲያ ሥልጠና ሁኔታ፤

| መላሾች | ብዛት | በሚዲያ ላይ የተሰጡ ኮርሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የወሰዱ | | ያልወሰዱ | | ኮርስ ስለመኖሩም የማያውቁ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| መምህራን | 10 | - | - | 10 | 100% | - | - |
| የሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች | 5 | 2 | 40% | 3 | 60% | - | - |

በሠንጠረዡ ውስጥ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አሥሩም የጥናቱ ታላሚ መምህራን በሙሉ በመደበኛ የመምህርነት ሥልጠናቸው ወቅት የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን የሚመለከት ትምህርት ራሱን የቻለ አንድ ኮርስ ሆኖ እንዳልተማሩ ገልጸዋል:: ከሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች መካከል ደግሞ በተቋም ደረጃ ከሌሎች የሥነ ዘዴ ኮርሶች ጋር በተጨማሪነት መማራቸውን የገለጹት ሁለት /40%/ ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ሦስቱ /60%/ ግን

ምንም ዓይነት የመርጃ መሣሪያን የሚመለከት ሥልጠና በተቋምም ሆነ በኮሌጅ ደረጃ አለመውሰዳቸውን ገልጸዋል::

## ለ. የመምህራን የሚዲያ የሥራ ላይ ሥልጠና

የሚዲያ ሥልጠና በመደበኛ የመምህርት ሥልጠና ወቅት ቢሰጥም ወይም ባይሰጥም እንኳ መምህራን ተመርቀው ወደ ሥራ ዓለም ከተሰማሩ በኋላ የተሃድሶ ወይም የማጠናከሪያ ሥልጠናዎችን በሥራ ላይ ሆነው ማግኘት ይኖርባቸዋል:: ይህም ዓይነት የሥራ ላይ ሥልጠና ሚዲያ-ነክ ብቃታቸውንና ክሂሎታቸውን ያጠናክርላቸዋል:: ይህን በሚመለከት መምህራኑ ያገኙት የሥራ ላይ ሥልጠና ስለመኖሩ ከሚቀጥለው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል::

ሠንጠረዥ 22፣ ከትምህርት መርጃ መሣሪያ ጋር በተያያዘ ለመምህራን የተሰጠ የሥራ ላይ ሥልጠና፤

| መላሾች | ብዛት | ሥልጠና የወሰዱበት ዙር ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከአንድ ጊዜ በላይ የተካፈሉ | | አንድ ጊዜ ብቻ የተካፈሉ | | ምንም ያልተካፈሉ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| መምህራን | 10 | 1 | 10% | 1 | 10% | 8 | 80% |

ከዚህ በላይ እንደመለከተው ከአሥሩ የጥናቱ ታላሚ መምህራን መካከል ስምንቱ /80%/ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አዘገጃጀትን በሚመለከት ምንም ዓይነት የሥራ ላይ ሥልጠና አልወሰድንም ብለው ሲመልሱ አንዱ /10%/ ከአንድ ጊዜ በላይ ሚዲያ ነክ የሥራ ላይ ሥልጠና መውሰዱን፣ ሌላኛው አንድ /10%/ ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ ሥልጠና ማግኘቱን ገልጿል::

## ሐ. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀትና ለመጠቀም የመምህራኑ ፍላጎት እና ተነሳሽነት

የመምህራን የቅድመ ሥልጠናም ሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ማግኘት በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ረገድ ምን እንደሚያዘጋጁና እንዴት እንደሚያዘጋጁ ዕውቀቱና ክሂሎቱ ስላላቸው የሥራ ፍላጎትና የተነሳሽነት ስሜት ይፈጥርላቸዋል:: ከዚህም በላይ በሚያዘጋጁት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም የሚያስተምሩት ትምህርት በተማሪዎቻቸው ላይ

የሚፈጥረውን የትምህርት አቀባበል ለውጥና ዕድገት ሲመለከቱ ሁሌም የማዘጋጀትና የመጠቀም ፍላጎትና ተነሳሽነት ያድርባቸዋል:: በአንፃሩ ግን ቅድመ ሥልጠናም ሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ያልወሰዱ መምህራን ስለሚዲያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ምንም ዓይነት ዕውቀትና ክሂሎት ስለማይኖራቸው ለሚዲያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ለሚኖራቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት ዝቅተኛነት አስተዋጽኦ ያደርጋል::

ቀደም ሲል በሠንጠረዥ 21 እና በሠንጠረዥ 22 ላይ በተገለፀው መሠረት የጥናቱ ታላሚ መምህራን በሙሉ /100%/ በመደበኛ የመምህርነት ሥልጠናቸው ወቅት የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን የሚመለከት ራሱን የቻለ አንድ ኮርስ ሆኖ እንዳልተማሩ እና 80% ያህሉ ደግሞ እንደዚሁ ምንም ዓይነት ሚዲያ ነክ የሥራ ላይ ሥልጠና ያልወሰዱ መሆናቸው ተረጋግጧል:: ይህም አብዛኞቹ ታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በማዘጋጀትም ሆነ በመጠቀም ረገድ የሚኖራቸውን ፍላጎትና ተነሳሽነት የደበዘዘ እንዲሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል::

እንደዚሁም መምህራኑ ካለባቸው የክፍለ ጊዜ ብዛት ጫና የተነሳ በሚዲያ ማዕከላቱ ተገኝተው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት ያለመቻልም እንደ አንድ ምክንያት ሊቆጠር ይችላል:: ለዚህም ከመምህራኑ ከራሳቸው የተገኘውን ይበልጥ ግልፅና ቀጥተኛ የሆነ መረጃ ቀጥሎ እንመለከታለን::

ሠንጠረዥ 23፣ ሳምንታዊ የመምህራን የክፍለ ጊዜ ጫና፤

| መላሾች | ብዛት | የክፍለ ጊዜያት ብዛት በሳምንት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከ10 በታች | | 11-15 | | 16-20 | | 21-25 | | 26-30 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| መምህራን | 10 | - | - | - | - | - | - | 3 | 30% | 7 | 70% |

ከአጠቃላይ መላሾች መካከል ሦስቱ /30%/ ከ21-25 ክፍለ ጊዜያት በሳምንት የሚያስተምሩ ሲሆኑ፣ ሰባቱ /70%/ ግን በሳምንት ከ26-30 ክፍለ ጊዜያት የሚያስተምሩ ናቸው:: ከዚህም ሌላ ከመምህራኑ ጋር ከተደረገው ውይይት አጥኚው እንደተረዳው እነዚህ በሳምንት እስከ 30 ክፍለ ጊዜያት የሚያስተምሩ መምህራን የአሐዳዊ (Self-contained) መምህራንና ምንም ረዳት መምህር ያልተመደባላቸው ናቸው:: በመሆኑም በመምህራኑ ላይ የሚታየው የክፍለ ጊዜ ብዛት

ጫና የመምህራኑን የትምህርት መርጃ መሣሪያ ዝግጅት ተሳትፎ ዝቅ ሊያደርግ ይችላል፤ የዝግጅት ተሳትፎ ማነስም ለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ማነስ አስተዋጽኦ ይኖረዋል::

### 4.3.2. ተቋማዊ ተላውጦዎች

በሥርዓት የተደራጀ የሚዲያ ማዕከል መኖርና ከማዕከሉም ተገቢ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አገልግሎት ማግኘት የመማር- ማስተማሩን ተግባር እንደሚያቀላጥፈው የታወቀ ነው:: ይህን በሚመለከት ለሚነሡት ዝርዝር ትንታኔዎች ማለትም በጥናቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ስለመኖራቸው፣ ማዕከላቱ ለሥራ ክፍት ስለሚሆኑበት ሰዓት፣ ስለማዕከላቱ ክፍሎች ሁኔታ እና በማዕከላቱ የተመደቡ ባለሙያዎች የክፍለ ጊዜ ጫና ባጠቃላይም ስለማዕከላቱ አደረጃጀት ከዚህ ቀጥሎ ከቀረበው ሠንጠረዥ በቂ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል ይታመናል::

ሠንጠረዥ 24፣ የትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ያሉበት ደረጃ፤

| | | | የማዕከላቱ ተግባራዊነት (functionality) | | | | | | | | | የሥራ ሰዓት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የቦታ ሁኔታ | | | | | | | | | |
| | | | | | | የተለያዩ ክፍሎች | | | | | | | | | |
| ትምህርት ቤት | የአስተባባሪ ብዛት | የክፍለ ጊዜያት ብዛት | የሚሠራ | በሁለቱም ፈረቃ | በአንድ ፈረቃ | አንድ ክፍል ብቻ | ቢሮ | ቤተ መጻሕፍት | ማሳያ ክፍል | መሥሪያ ክፍል | ግምጃ ቤት | ሁልጊዜ ክፍት | አብዛኛውን ጊዜ | ሁልጊዜ ዝግ | አበዛኛውን ጊዜ ዝግ |
| ግራዝማች ጳውሎስ | 1 | 20 | ✓ | X | ✓ | ✓ | X | X | X | X | X | X | X | X | ✓ |
| ባርታ | 1 | 20 | ✓ | X | ✓ | ✓ | X | X | X | X | X | X | X | X | ✓ |
| ሽታ | 2 | 20 | ✓ | ✓ | | ✓ | X | X | X | X | X | X | X | X | ✓ |
| ባንዲራ | 1 | 30 | ✓ | X | ✓ | ✓ | X | X | X | X | X | X | X | X | ✓ |
| ካያኪላ | 2 | 30 | ✓ | ✓ | | ✓ | X | X | X | X | X | X | X | X | ✓ |

የምልክቶች መፍቻ፤

✓ = አዎንታዊ መልሶችን ያመለክታል::

X = አሉታዊ መልሶችን ያመለክታል::

## ሀ. የሚዲያ ማዕከላት መኖርን በተመለከተ

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ እንደታየው በአምስቱም የጥናቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የትምህርት ቤት ሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት አሉ:: የዚህ ጥናት አቅራቢ በየትምህርት ቤቶቹ ሚዲያ ማዕከላት በመገኘት ባደረገው ምልከታ በተረዳው መሠረት የማዕከላቱ ክፍሎች አሠራር ለሚዲያ ማዕከል በሚያመች መልኩ ታስቦባቸው የተዘጋጁ ሳይሆኑ፣ ልክ በመማሪያ ክፍል አሠራር ሁኔታ በግምት ሰባት ሜትር በስምንት ሜትር በሚሆን ስፋት የተሠሩት አንዳንድ ክፍል ብቻ ናቸው:: ከእነዚህ ከአምስቱ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት የሦስቱ ማለትም የሽታ፣ የባንዲራና የካያኬላ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ክፍሎች ወለል አፈር ሲሆን፣ ቤቶቹም የተሠሩት ከእንጨት፣ ከጭቃና ከቆርቆሮ ክዳን ነው:: የሌሎች ሁለቱ ማለትም የግራዝማች ጳውሎስ እና የባርታ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ወለሎቻቸው ሲሚንቶ ሲሆን የግራዝማች ጳውሎስ ብቻ ግድግዳው ብሎኬት ነው::

## ለ. የሚዲያ ማዕከላቱን የሥራ ሰዓት በተመለከተ

እዚህ ላይ የሥራ ሰዓት ሲባል በሁለት መልክ ሊታይ ይችላል:: አንደኛው ማዕከላቱ በሁለቱም ፈረቃዎች /ጧትና ከሰዓት በኋላ/ ክፍት በመሆን ለተጠቃሚዎቻቸው የተሟላ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በሁለትም ይሁን በአንድ ፈረቃ፣ ማዕከላቱ ከአንደኛ ክፍለ ጊዜ ጀምሮ እስከ መጨረሻ ድረስ ሙሉ ጊዜያቸውን ክፍት ሆነው ለተጠቃሚዎቻቸው አገልግሎት እየሰጡ እንደሆነ የሚመለከት ነው:: ከዚህ አኳያ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑትን ሚዲያ ማዕከላት የሥራ ሰዓት ሁኔታ ከሠንጠረዡ ስንመለከት የግራዝማች ጳውሎስ፣ የባርታ እና የባንዲራ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት በአንድ ፈረቃ ብቻ የሚሠሩ ሲሆኑ፣ የሽታ እና የካያኬላ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ግን በሁለቱም ፈረቃዎች የሚሠሩ ናቸው:: የዚህም ምክንያቱ በአንድ ፈረቃ ብቻ የሚሠሩት ሦስቱ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት አንዳንድ አስተባባሪ ብቻ ያላቸው ሲሆኑ፣ በሁለቱም ፈረቃ የሚሠሩት ሁለቱ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ግን ረዳት አስተባባሪዎች ስላሏቸው ነው:: በመሆኑም በአንድ ፈረቃ ብቻ የሚሠሩት የሦስቱ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ተጠቃሚዎቻቸውን ማስተናገድ የሚችሉት በአንድ ፈረቃ ብቻ በመሆኑ ተጠቃሚዎቹ በተቃራኒው ፈረቃ አገልግሎት አያገኙም::

የአሰተባባሪዎቹን የሳምንት የማስተማር ክፍለ ጊዜያት ጫና ስንመለከት የግራዝማች ጳውሎስ፣ የባርታና የሽታ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች በሳምንት ሃያ ሃያ ክፍለ ጊዜያት፣ በቀን በአማካይ አራት አራት ክፍለ ጊዜያት ሲኖራቸው የባንዲራና የካያኬላ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት አስተባባሪዎች ደግሞ በሳምንት ሠላሳ ሠላሳ ክፍለ ጊዜያት፣ በቀን በአማካይ አምስት አምስት ክፍለ ጊዜያት ይኖራቸዋል:: ከዚህ የምንገነዘበው አንድ የሚደያ ማዕከል አስተባባሪ በሚያስተምርበት ፈረቃ በቀን ከአራት እስከ አምስት ክፍለ ጊዜ ያህል ለማስተማር ወደ ክፍል በመግባቱ ምክንያት ማዕከሉ ዝግ ስለሚሆን አገልግሎት አይሰጥም:: በሌላ አነጋገር በአንድ ፈረቃ ከሚኖሩ ስድስት ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ማዕከላቱ ክፍት ሆነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ለአንድ ወይም ለሁለት ክፍለ ጊዜያት /ከ40-80 ደቂቃ/ ብቻ ይሆናል::

ሐ. ቦታን በተመለከተ

የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የአምስቱንም ሚዲያ ማዕከላት ክፍሎች ሁኔታ ሲታይ፣ ሁሉም በግምት ሰባት ሜትር በስምንት ሜትር የሆነ የመማሪያ ክፍል ዓይነት አሠራር ያላቸው አንዳንድ ክፍል እንደሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል:: ከዚህ ባለፈ ሁሉም በሚዲያ ማዕከል ክፍሎች አደረጃጀት አግባብ መሠረት የሠራተኞች ቢሮ፣ ንባብ ቤት፣ የማሳያ ክፍል፣ የመሥሪያ ክፍል፣ ግምጃ ቤት፣ ወዘተ. የሚባሉ ክፍሎች የሏቸውም::

መ. በጀትን በተመለከተ

ሚዲያ ማዕከላት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀትም ሆነ በግዥ ለማቅረብ እነሰም በዛም ገንዘብ /በጀት/ ያስፈልጋቸዋል:: ይህን በሚመለከት የጥናቱ ተተኳሪ ለሆኑት ማዕከላት አስተባባሪዎች በቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ውስጥ ሁሉም የሰጡት መልስ በየዓመቱ ለሚዲያ ማዕከላቱ የሚያስፈልገውን በጀት ዓቅደው ቢያቀርቡም፣ የትምህርት ቤቶቹ አስተዳደሮች ግን የተወሰነ የጽሕፈት መሣሪያና መሰል ነገሮችን ብቻ በዓይነት ገዝተው እንደሚያቀርቡላቸው እንጂ፣ በዕቅዱ መሠረት የተፈለገውን ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ በሙሉ /በበቂ ደረጃ/ ማግኘት እንደማይችሉ ገልጸዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ለትምህርት ቤቶቹ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ኃላፊዎቹ የሰጡት ምላሽ፣ ማዕከላቱ በደንቡ መሠረት ዓቅደው ቢያቀርቡም፣ ትምህርት ቤቶቹ ካለባቸው የበጀት ውሱንነት የተነሳ ከሌሎች ፕሮግራሞች ጋር በማጣጣም

የተማሪ ድጎማ በጀት ተብሎ ከመንግሥት ከሚፈስላቸው ውስን በጀት ላይ በማብቃቃት የተወሰኑ የጽሕፈት መሣሪያዎችንና መሰል ነገሮችን በዓይነት ገዝተው እንደሚያቀርቡላቸው ገልጸዋል::

ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ የምንረዳው የሚዲያ ማዕከላቱ አደረጃጀት እና የበጀት አመዳደብ ሁኔታ የሚዲያ ማዕከላቱን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ብቃትን ሊወስኑ የሚችሉ ተቋማዊ /በትምህርት ቤት በኩል የሚታዩ/ ተላውጦዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው::

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና አስተያየት

በዚህ ክፍል በጥናቱ የመረጃ ውጤት ትንተናን እና ማብራሪያን መሠረት በማድረግ የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት ተሰጥቷል::

## 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚያስተምሩ የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች አጠቃቀም እና የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ለማረጋገጥ የተካሄደ ነው:: ስለዚህም በናሙናነት በቦንጋ ከተማ የሚገኙ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ተመርጠው የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች አጠቃቀም እና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ደረጃቸው ምን ያህል እንደሆነ ለማሰስ ተሞክሯል::

መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማቀድም ሆነ ለማዘጋጀት በቅድሚያ ሦስቱን የትምህርት መሣሪያዎች ማለትም መርሐ ትምህርትን፣ የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መጽሐፍ ማግኘት ይኖርባቸዋል:: በጥናቱ በተካተቱት ትምህርት ቤቶች ግን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ መሣሪያዎች አንዳቸውም እንደሌሉ ተረጋግጧል:: በዚህም የተነሳ የሴሚስተርንም ሆነ የእለት ትምህርት እቅድ ለመንደፍና በአኳያውም ተገቢ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አዘጋጅቶ ለመጠቀም አዳጋች እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል::

ትምህርት ቤቶች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የሚያገኙባቸው መንገዶች በርካታ ናቸው:: ከነዚህም በግዥና በስጦታ የሚገኙ መርጃ መሣሪያዎች ይጠቀሳሉ:: ከዚህ አኳያ በጥናቱ የተካተቱት ትምህርት ቤቶች በግዥም ሆነ በስጦታ የሚያገኙት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ብዛት አነስተኛ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል::

መምህራን ተገቢ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ማዘጋጀት የሚያስችላቸውን ቅድመ ሥራ ሥልጠና እና የሥራ ላይ ሥልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል:: ከዚህም ሌላ መምህራኑ ባላቸው ውስን ችሎታም ቢሆን በሚዲያ ማዕከል ተገኝተው ለመሥራት በቂ ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል:: ከዚህ አንፃር በጥናቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን በቂ የሆነ የቅድመ ሥራ ሥልጠናም ሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ባለማግኘታቸው፣

እንደዚሁም በሳምንት ከ25-30 ክፍለ ጊዜያት የሚሠሩ በመሆናቸው የተነሳ የማዕከል ተሳትፎአቸው ዝቅተኛ ነው:: ከዚህም ሌላ ተማሪዎች በመርጃ መሣሪያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ረገድ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በመምህራን በኩል የተደረገው ጥረት አነስተኛ ነው::

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መምረጥ፣ ማቀድና ማዘጋጀት ብቻውን በቂ አይደለም:: ዋናው ነገር የተዘጋጁትን ወይም የተመረጡትን መርጃ መሣሪያዎች በክፍል ውስጥ በመማር-ማስተማር ተግባር ማዋል ነው:: ከዚህ አንፃር በክፍል ውስጥ በተደረጉት ምልከታዎች እንደተስተዋለው ከ73.3% እስከ 80% ያህል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያስተምሩት ያለትምህርት መርጃ መሣሪያ በቃል ብቻ ነው::

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሳቢነት እንዲኖራቸው በጥራት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል:: በጉልህ እንዲታዩም መጠናቸው ተለቅ ማለት ይኖርበታል:: ከዚህ አንፃር በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተዘጋጁትም ሆነ በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የጥራትና የመጠን ደረጃ ዝቅተኛ ነው::

በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዓይነት ተለይተው ሲታዩ አብዛኞቹ እንደ ሥዕልና ፍላሽ ካርድ ያሉ ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብቻ ናቸው:: ሌሎች እንደ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ያሉ ድምፃዊና ድምፃዊ ወዕይታዊ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በአገልግሎት ላይ ሲውሉ አልታዩም::

የክፍል ምልከታ በተካሄደባቸው አሥር የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በእያንዳንዳቸው የሚገኘው የጠመኔ ሠሌዳ ብቻ ነው:: ሌሎች እንደ ሻሸ ሠሌዳ፣ ማስታወቂያ ሠሌዳ፣ ከሱፍ ጨርቅ የተሠራ ሠሌዳ ያሉ በቀላሉ በሚዲያ ማዕከል ደረጃ የሚሠሩ ሠሌዳዎች በየክፍሉ ባለመኖራቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በሥርዓት ለመስቀልና ለመለጠፍ አልተቻለም::

በጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት ውስጥ የሚሠሩ አስተባባሪዎች "ካሉት መምህራን ይሻላሉ" በሚል በመምህራን ጉባዔ የተመረጡ እንጂ የሚዲያ ማዕከል አስተባበሪነት ሙያ ሥልጠና የወሰዱ አይደሉም:: ከዚህም ሌላ በሚዲያ ማዕከላቱ ሊኖር የሚገባ በተለያየ ሙያ የሠለጠነ የሰው ኃይል ፈጽሞ የለም:: የሚዲያ ማዕከላቱ የክፍሎች አደረጃጀት ሲታይ ደግሞ እንደቢሮ፣ የማሳያ ክፍል፣ የመሥሪያ ክፍል፣ ንባብ ቤት እና ግምጃ ቤት ያሉ የተለያዩ ክፍሎች የሏቸውም:: በዚህ መልኩም የተደራጁ አይደሉም::

የትምህርት ቤት ሚዲያ ማዕከላት ሁል ጊዜ ክፍት በመሆን ለተጠቃሚዎቻቸው ተገቢ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ አንፃር የጥናቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች ሚዲያ ማዕከላት አብዛኛውን ጊዜ ዝግ ናቸው። ክፍት የሚሆኑት በቀን ቢበዛ ከአርባ እስከ ስማኒያ ደቂቃ ብቻ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የአስተባባሪዎቹ ጊዜ በማስተማር ሥራ መያዙ ነው።

## 5.2. አስተያየት

የጥናቱ አቅራቢ በዚህ ጥናት ማጠቃለያ ላይ ለቀረቡት ችግሮች መፍትሔ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት የሚከተሉትን አስተያየቶች ይሠነዝራል፤

ሀ. የትምህርት ቤቶች አስተዳደሮችና ሌሎች የትምህርት የበላይ አካላት አዳዲስ የትምህርት መሣሪያዎች /መርሐ ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪ መጽሐፍ/ በተቻለ መጠን በየወቅቱ ለትምህርት ቤቶች እንዲደርሱ ቢያደርጉ፤

ለ. መምህራንና የሚዲያ ማዕከል አስተባባሪዎች የትምህርት መርጃ መሣሪያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም በሚመለከት ተከታታይነት ያለው የሥራ ላይ ሥልጠና ቢሰጣቸው፤

ሐ. መምህራን፣ ተማሪዎቻቸው አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው መሆኑን ተገንዝበው፣ እያንዳንዱን የትምህርት ይዘት ተገቢና ጥራት ባለው የትምህርት መርጃ መሣሪያ በማስደገፍና በመታገዝ ቢያስተምሯቸው፤

መ. መምህራን በቂ ዝግጅት አድርገው ተማሪዎቻቸውን በተገቢ ሁኔታ እንዲያስተምሩ የሚዲያ ማዕከል አስተባባሪዎችም በማዕከላቱ ሁልጊዜ ተገኝተው አገልግሎት እንዲሰጡ የክፍለ ጊዜ ጫና ቢቀነስላቸው፤

ሠ. መምህራን በትምህርት ቤቶቻቸው በሚገኙት በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በመጠቀም አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ የሆነባቸውን ተማሪዎቻቸውን የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎት ማጎልበቻ ትምህርት ማስተማር ቢያስተምሩ፤ ትምህርት ቤቶችም ለዚህ ተግባር ሁኔታዎችን ቢያመቻቹ፤

ረ. መማሪያ ክፍሎች ከጠመኔ ሠሌዳ ሌላ በትምህርት ቤት ዓቅም ሊሠሩ በሚችሉ ሌሎች ሠሌዳዎች ቢሟሉ፤ በዚህም ሁኔታ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በሠሌዳዎቹ ላይ በመለጠፍና በመስቀል በሥርዓት ማደራጀት ቢቻል፤

ሰ. ሚዲያ ማዕከላቱ የዓመት እቅዳቸውን በተገቢ ሁኔታ ይወጡ ዘንድ በግላቸው በቂ በጀት ቢመደብላቸው፤



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ዋቢ ጽሑፎች


ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት፣ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት (1996) "የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ከ1ኛ -4ኛ ክፍሎች" (ያልታተመ)::

ትምህርት ሚኒስቴር (1984) <u>የትምህርት ፖሊሲና አተገባበሩ::</u> አዲስ አበባ፤ ትመማማድ::

ጌታቸው ለገሠ (1992) "በአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት በማሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋጽኦ::" ያልታተመ የአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ የኒቨርሲቲ::

ያለው እንዳወቀ 2006 <u>የምርምር መሠረታዊ መርሖዎችና አተገባበር</u>:: አዲስ አበባ:: አልፋ አሳታሚዎች::

Abebe Zewdie (1997) "Selection and Use of Instructional Media by Pre Service and in Service Elementary School Teachers- The Case of Region 13." Unpublished M.A. Thesis. Addis Ababa University.

Aggarwal, J.C. (1996) <u>Principles, Methods and Techniques of Teaching.</u> New Delhi: Vikas Publishing House Pvt.Ltd.

Amare Asgedom and Tasseq Zewdie (1996) <u>Sevey of Pedagogical Centers in Primary Schools of Addis Ababa.</u> Addis Ababa: Region 14 Education Bureau.

Amare Asgedom (1999) "Availability and use of Instructional Materials in Tigray." IER Flambeau 7(1):53-66.

Asby, Eric and Ralph M. Besse (1972) (ed) <u>The Fourth Revolution- Instructional Technology in Higher Education.</u> New York: Mcgraw- Hill co.

Bestate Terefe (2000) "Application of Instructional Materials in the Primary Schools of the SNNPR." Unpublished M.A. Thesis. Addis Ababa University.

Bowen, Betty Morgan (1982) <u>Look Here! Visual Aids in Language Teaching.</u> Hong Kong: Macmillan Publishers Ltd.

Day, Richard R. (1990) "Teacher Observation in Second Language Education." In J.C. Richards and D.Nunan (eds) Second Language Teacher Education. Cambridge: Cambridge University Press.

Department of Foreign Languages and Literature, AAU (1995) Skills Development methodology- Part-1. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Flanigan, Michael C. and Boon, Robert S. (1977) Using Media in the Language Arts. Itsca: FE. Peacock Publishing INC.

Harrison, Raymond H. & Gowin, Lawerence E. (1958) The Elementary Teacher in Action. San Fransisco: Wadsworth Publishing Company Inc.

Harmer, J. (2001) The Principles of English Language Teaching. London: Pearson Educational Limited.

Heinich, Rovert et al. (1996) Instructional media and Technologies for Learning. (5th ed). New jersey: Prentice- Hall.

I.C.D.R. (1989) Source Book on the Preparation of Low Cost Teaching Materials for Primary and Junior Geography. Addis Ababa: M.O.E. and Goethe Institute.

Kieffer, R.E. and leew, Cochran (1962) Manual of Audio-Visual Techniques. New Jersey: Prentice Hall Inc.

Koskey, B.Eugene (1974) "Its About Time we Practice what we Teach!" In Selecting Media for Instruction: Readings from AV instruction 66-70.

Newby, Timothy J. et al. (1996) Instructional Technology fro Teaching and Learning. Newjersey: Prentice Hall.

Nkuuhe, Johnson (1995) "Instructional Media." In Matiru, Barbara and Others (eds) Teach Your Best: A Hand Book for University Lecturers. Nirobi: Integrated System Ltd.

Nunan, D. (1998) Language Teaching Methodology. Edinberrurgh: Pearson Education Ltd.

Quist, Dawn (2000) Primary Teaching Methods. Oxford: Macmillan Publishers Limited.

Tucker, Richard N. (1979) The Organization and Management of Educational Technology. London: Croom Helm.

Wookock, V. (nd) What is Teaching Aid? Retrieved Mar. 16, 2008, From http://www.silentmational.com/referencematerial,htm.

Wright, Andrew (1989) Pictures for Language Learning. London: Longman.

Wright, Andrew and Haleem, Sofia (1994) Visuals for Language Classroom. London: Longman.

# አባሪዎች

# አባሪ 1

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድኅረ ምረቃ መርሐግብር

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅጽ፤

## (Classroom Observation Check List)

### ክፍል በአንድ:- አጠቃላይ መግለጫ

1. ሀ. የትምህርት ቤቱ ስም፣______________

ለ.የክፍል ደረጃ፣____________________

ሐ. ክፍለ ጊዜው፣____________________

መ. ምልከታው የተካሄደበት ቀን፣ ___________

### ክፍል ሁለት፣ ዝርዝር መረጃዎች፤

2. የሴሚስተር የትምህርት ዕቅድ ሀ. ተዘጋጅቷል ለ. አልተዘጋጀም
3. በሴሚስተር የትምህርት ዕቅድ ውስጥ መረጃ መሣሪያዎች

ሀ. ተጠቅሰዋል ለ. አልተጠቀሱም

4. የዕለቱ የትምህርት ዕቅድ ሀ. ተዘጋጅቷል ለ. አልተዘጋጅም
5. የዕለቱ የትምህርት ርዕስ____________________
6. በዕለት የትምህርት ዕቅድ ውስጥ መረጃ መሣሪያዎች

ሀ. ተጠቅሰዋል ለ. አልተጠቀሱም

7. ለዕለቱ ትምህርት ተዘጋጅተው የቀረቡ መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር

ሀ.____________________

ለ. ____________________

ሐ. ____________________

መ. ____________________

ሠ. ____________________

8. በዕለት ትምህርት ዕቅድ ውስጥ የተጠቀሰው የትምህርት መርጃ መሣሪያ በሴሚስተር ዕቅድ ላይ ከሰፈረው ጋር ሀ. ተመሳሳይ ነው ለ. ተመሳሳይ አይደለም
9. የዕለቱ ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ.____________________

ለ. ____________________

ሐ. ____________________

መ. ____________________

10. የሴሚስተሩም ሆነ የዕለቱ የትምህርት ዕቅድ የተዘጋጀው
   ሀ. መርሐ ትምህርቱን ተከትሎ ነው::
   ለ. በመምህሩ መምሪያ እና በተማሪው መጽሐፍ ብቻ ነው::
   ሐ. በተማሪው መጽሐፍ ብቻ ነው::
   ሐ. መምህሩ ከነበራቸው ልምድ በመነሳት ያለምንም ትምህርት መሣሪያ ነው ያዘጋጁት::
11. ተዘጋጅተው የቀረቡት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የዕለቱን ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች ከማሳካት አካያ ያላቸው ተገቢነት:-
   ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው::
   ለ. በጣም ጥሩ ነው::
   ሐ. ጥሩ ነው::
   መ. በቂ ነው::
   ሠ. አነስተኛ ነው::
12. መርጃ መሣሪያዎቹ የተገኙት:-
   ሀ. ተገዝተው ነው::
   ለ. በአካባቢው ከሚገኙት ቁሳቁሶች ተዘጋጅተው ነው::
   ሐ. በስጦታ መልክ ነው::
12.1. ተገዝተው የቀረቡ ከሆነ ማን ገዛቸው?____________________
12.2. ከአካባቢ ቁሳቁስ ተዘጋጅተው ከሆነ በማን ተዘጋጁ?
   ሀ. በመምሩ
   ለ. በተማሪው
   ሐ. በማዕከሉ ባለሙያ
12.3. በስጦታ መልክ የተገኙ ከሆነ ከማን ?____________________
13. መርሐ ትምህርቱ፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መጽሐፍ በመምህሩ እጅ ይገኛሉ::
   ሀ. ሦስቱም አሉ::
   ለ. የተማሪው መማሪያ ብቻ ነው ያላቸው::
   ሐ. የመምህሩ መምሪያ ብቻ ነው ያላቸው::
   መ. የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መጽሐፍ ብቻ ነው ያላቸው::
   ሠ. መርሐ ትምህርቱ ብቻ ነው ያላቸው::
   ረ. ሦስቱም የላቸውም::
14. የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ:-
   ሀ. በእያንዳንዱ ተማሪ እጅ ይገኛል
   ለ. አንድ መጽሐፍ ለሁለት ተማሪ::
   ሐ አንድ መጽሐፍ ለሦስት ተማሪ::

መ. አንድ መጽሐፍ ለአራት እና ከዚያ በላይ ተማሪ::

ሠ. መጽሐፍ በፍፁም የላቸውም::

15. የመማሪያ መጽሐፉ አዘገጃጀት በሥዕላዊ መግለጫ የመደገፉ ሁኔታ:-

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው::

ለ. በጣም ጥሩ ነው::

ሐ. ጥሩ ነው::

መ. በቂ ነው::

ሠ. አነስተኛ ነው::

16. ለዕለቱ የቀረቡት ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጥራት:-

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው::

ለ. በጣም ጥሩ ነው::

ሐ. ጥሩ ነው::

መ. በቂ ነው::

ሠ. አነስተኛ ነው::

17. ለዕለቱ የቀረቡት ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን:-

ሀ. እጅግ በጣም ሰፊና ጉልህ ነው::

ለ. በጣም ሰፊና ጉልህ ነው::

ሐ. በቂ ነው::

መ. አነስተኛ ነው::

18. በመማሪያ ክፍሉ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አደረጃጀትን በተመለከተ

18.1 በትምህርት ዓይነት ማህደር

ሀ. ተደራጅተዋል:: ለ. አልተደራጁም::

18.2 በምዕራፍ ማህደር:-

ሀ. ተደራጅተዋል ለ. አልተደራጁም

18.3 በቋንቋ ክሂሎች መማሪያ ማህደር:-

ሀ. ተደራጅተዋል ለ. አልተደራጁም

18.4 በርዕስ ማህደር:-

ሀ. ተደራጅተዋል ለ. አልተደራጁም

18.5 በባህላዊ መረጃ (Cultural Information) :-

ሀ. ተደራጅተዋል ለ. አልተደራጁም

19. በክፍል ውስጥ የሚገኙ ሠሌዳዎችን ዝርዝር በተመለከተ:-

19.1 ጠመኔ ሠሌዳ (Chalk board):- ሀ. አለ ለ. የለም

19.2 ነጭ ሠሌዳ:- ሀ. አለ ለ. የለም

19.3 ሻሸ ሠሌዳ ሀ. አለ ለ. የለም

19.4 መግነጢሳዊ ሠሌዳ (magnetic board) ሀ. አለ ለ. የለም

19.5 ከወፍራም ሱፍ ጨርቅ የተሠራ ሠሌዳ (Flannel Board)

ሀ. አለ ለ. የለም

19.6 የማስታወቂያ ሠሌዳ ሀ. አለ ለ. የለም

20. የመምህሩ በሠሌዳው /በሠሌዳዎቹ/ የመጠቀም ብቃት፣

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው::

ለ. በጣም ጥሩ ነው::

ሐ. ጥሩ ነው::

መ. በቂ ነው::

ሠ. አነስተኛ ነው::

21. ተማሪዎች በመርጃ መሣሪያዎቹ በመጠቀም የሚያሳዩት የትምህርት ተሳትፎ:-

ሀ. እጅግ የላቀ ነው::

ለ. በጣም የላቀ ነው::

ሐ. ጥሩ ነው::

መ. በቂ ነው::

ሠ. አነስተኛ ነው::

22. በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ማራኪነት:-

ሀ. ሁሉም ተማሪዎች የደስታ መንፈስ ይታይባቸዋል::

ለ. አብዛኞቹ ተማሪዎች የደስታ መንፈስ ይታይባቸዋል::

ሐ. ግማሽ ያህሉ ቹ የደስታ መንፈስ ይታይባቸዋል::

መ. ጥቂቶች ብቻ የደስታ መንፈስ ይታይባቸዋል::

ሠ. ሁለም ተማሪዎች የደስታ መንፈስ አይታይባቸውም::

23. ተማሪዎች በዕለቱ በቀረቡት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ የተማሩትን ትምህርት በክፍለ ጊዜው መጨረሻ መምህሩ ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ:-

ሀ. እጅግ በጣም ፈጣን ነው::

ለ. በጣም ፈጣን ነው::

ሐ. ዝግተኛ ነው::

መ. በጣም ዝግተኛ ነው::

ሠ. ትምህርቱን የመረዳታቸው ሁኔታ ራሱ አጠራጣሪ ነው::

## አባሪ 2

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድኅረ ምረቃ መርሐግብር

## የትምህርት ቤት ሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከላት ምልከታ

## (Observation Check List)

1) ራሱን የቻለ የትምህርት ሚዲያ ማዕከል አለ ወይ?

ሀ. አለ ለ. የለም

2) ማዕከሉ በአሁኑ ጊዜ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?

ሀ. ሁልጊዜ ክፍት ነው።

ለ. አንዳንድ ጊዜ ክፍት ነው።

ሐ. ሁል ጊዜ ዝግ ነው።

መ. አንዳንድ ጊዜ ዝግ ነው።

ሠ. ሌላ ካለ ይገለጽ______________________________

3) በማዕከልነት የሚያገለግለው ክፍል መጠንና አካላዊ አቋም:-

ሀ. በጣም ሰፊ ነው።

ለ. ሰፊ ነው።

ሐ. ጠባብ ነው።

መ. በጣም ጠባብ ነው።

4) ለማዕከሉ የተመደበ አስተባባሪ መምህር/ቴክንሺያን/ አለ?

ሀ. አለ ለ. የለም

5) የማዕከሉ አቋምና አደረጃጀት

5.1 የጥሬ ዕቃ አቅርቦት

ሀ. በቂ ነው

ለ. በቂ አይደለም

ሐ. እንዲያውም የለም

5.2 የሥራ መሣሪያዎች

ሀ. የተለያዩ ዓይነቶች አሉ

ለ. አንድና ሁለት ዓይነት ብቻ

ሐ. ምንም የለም

6) በማዕከሉ ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሥርዓተ ትምህርት መሣሪያዎች አሉ

6.1. የ3ኛ ክፍል መርሐትምህርት

ሀ. አለ ለ. የለም

6.2 የ3ኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ

ሀ. አለ ለ. የለም

6.3 የ3ኛ የተማሪው መጽሐፍ

ሀ. አለ ለ. የለም

6.4 የ4ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት

ሀ. አለ ለ. የለም

6.5 የ4ኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ

ሀ. አለ ለ. የለም

6.6 የ4ኛ የተማሪው መጽሐፍ

ሀ. አለ ለ. የለም

7) ለ3ኛ 4ኛ ክፍሎች አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ መረጃ መሣሪያዎች አሉ?

ካለ ዓይነታቸው (Variety)

_______________________________________________

8) ለ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁት መርጃ መሣሪያዎች ስብጥር/ብዛት/ ከትምህርቱ ምዕራፎች አንፃር፣

ሀ. ከ10 በላይ ለሆኑ ምዕራፎች ለ. ከ5-10 ምዕራፎች

ሐ. ከ1-4 ምዕራፎች መ. ምንም የለም

9) ለ4ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁት መርጃ መሣሪያዎች ስብጥር /ብዛት/ ከትምህርት ምዕራፎች አንፃር፣

ሀ. ከ10 በላይ ለሆኑ ምዕራፎች ለ. ከ5-10 ምዕራፎች

ሐ. ከ1-4 ምዕራፎች መ. ምንም የለም

10) ማዕከሉ የተለየ የማሳያ ሥፍራ አለው? ሀ. አለው ለ. የለውም

11) የማሳያ ሥፍራው ሁኔታ ምን ይመስላል?

ሀ. በጣም በቂ ነው ለ. በቂ ነው ሐ. በቂ አይደለም መ. በጭራሽ በቂ አይደለም

12) ማዕከሉ የተለየ የማስቀመጫ ሥፍራ አለው? ሀ. አለው ለ. የለውም

13) የማስቀመጫ ሥፍራው ሁኔታ ምን ይመስላል?

ሀ. በጣም በቂ ነው ለ. በቂ ነው ሐ. በቂ አይደለም መ. በጭራሽ በቂ አይደለም

14) ማዕከሉ የመጻሕፍት መደርደሪያ:- ሀ. አለው ለ. የለውም

15) ማዕከሉ የመርጃ መሣሪያዎች መደርደሪያ /ማስቀመጫ/:- ሀ. አለው ለ. የለውም

16) የመርጃ መሣሪያዎች አደራደር በምን ዓይነት ነው?



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሀ. በክፍል ደረጃ አንፃር   ለ. በትምህርት ዓይነት አንፃር   ሐ. በሀ ና በለ

መ. ዝብርቅርቅ ነው   ሠ. ሌላ ካለ ይገለጽ

17) የቅርፃዊና የሌሎችም መሰል ሥዕላዊ መረጃዎች ማስቀመጫ ሳጥን (Cabinet):-

ሀ. አለው   ለ. የለም

18) የማንበቢያና የጥናት ሥፍራ ተለይቷል? ሀ. አዎ   ለ. አልተለየም

19) የማንበቢያና የጥናት ጠረጴዛዎች አሉ? ሀ. አዎ   ለ. የሉም

20) የማዕከሉ ሠራተኛ የሚጽፍበት ጠረጴዛና ወንበር አለ? ሀ. አለ   ለ. የለም

21) የመሥሪያ ሥፍራ ተለይቶለታል? ሀ. አዎ   ለ. የለም

22) የመሥሪያው ሥፍራ ስፋቱ ምን ያህል ነው?

ሀ. በጣም ሰፊ ነው   ለ. ሰፊ ነው   ሐ. ጠባብ ነው   መ. በጣም ጠባብ ነው

23) የመሥሪያ ሥፍራው ከማንበቢያና ጥናት ጠረጴዛው የራቀ ነው?

ሀ. አዎ   ለ. አይደለም

24) በማዕከሉ ውስጥ የሚገኙ መረጃ መሣሪያዎችን ዝርዝር በርዕስ፣ በዓይነት፣ ወዘተ. የሚያሳይ መዝገብ/ካርድ ካታሎግ/ አለ? ሀ. አዎ   ለ. የለም

25) የማዋሻ መዝገብ ተዘጋጅቷል? ሀ. አዎ   ለ. የለም

26) የማዋሻ መዝገብ አገልግሎት ይሰጣል? ሀ. አዎ   ለ. አይሰጥም

# አባሪ 3

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድኅረ ምረቃ መርሐግብር
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

**በቦንጋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ዕርከን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ**

ዓላማ፡- የቋንቋ ማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን በሚመለከት በመምህራንና በትምህርት ቤቶች በኩል በመሠራት ላይ የሚገኘውን ሥራ፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን፣ ያሉትንና የጎደሉትን ሁኔታዎች በተጨባጭ ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው።

ማሳሳቢያ፡-

- ስምዎን መጻፍ አያስፈልግዎትም።
- የጥናቱ ውጤት አስተማማኝ እንዲሆን በጣም ግልፅ ሆነው ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ እጠይቃለሁ።
- ግልፅ ሆነው የሚሰጡት ማንኛውም መረጃ ለጥናቱ ዓላማ ብቻ ከሚውል በስተቀር በሚስጥር እንደሚያዝ አረጋግጣለሁ።
- ጥያቄዎቹን አንድም ሳያስቀሩ በመመለስ የተሟላ መረጃ እንዲሰጡ አደራ እላለሁ።
- ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል በእርስዎ በኩል ትክክለኛ ነው ብለው ያመኑበትን መልስ የሚወክለውን ፊደል ይክበቡት።
- ለአንዳንድ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች የተለየ ሌላ መልስ ሲኖርዎትና እንዲሁም ምርጫ ለሌላቸው ክፍት ጥያቄዎች መልስዎን ለዚሁ በተዘጋጁት ክፍት ሥፍራዎች ላይ ይጻፉ።

ለትብብርዎ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን ከወዲሁ አቀርባለሁ።

## ክፍል አንድ፣ የግል ሁኔታ መግለጫ፤

1. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት፣ ____________________
2. ፆታ፣ ሀ. ወንድ ለ. ሴት
3. የአገልግሎት ዘመን፣

   ሀ. ከ1-5 ዓመት ለ. ከ6-10 ዓመት

   ሐ ከ11-15 ዓመት መ. ከ16 ዓመት በላይ
4. የትምህርት ደረጃ:-

   ሀ. 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች/

   ለ. የምስክር ወረቀት/ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም

   ሐ. 12+1ኛ ዓመት የኮሌጅ ትምህርት መ. ዲኘሎማ

   ሠ ሌላ/ ይገለጽ__________
5. በኮሌጅ ደረጃ ሠልጥነው ከሆነ የሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት /ዐቢይ__________

   ንዑስ__________
6. የተመረቁበት ዓ.ም.____________________
7. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ

   ሀ. 3ኛ ለ. 4ኛ ሐ. 3ኛ ና 4ኛ መ. ሌላ ካለ ይገለፅ____________
8. በሳምንት ውስጥ ምን ያህል ክፍለ ጊዜያት ያስተምራሉ?

   ሀ. ከ10 በታች ለ. ከ11-15 ሐ. ከ16-19 መ. ከ20-24 ሠ. ከ25 በላይ

## ክፍል ሁለት፣ ዝርዝር መረጃዎች፤

9. ለሚያስተምሩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በአዲስ መልክ የተዘጋጀ መርሐ ትምህርት/ሲለበስ/ አለዎት?

   9.1. የ3ኛ ክፍል ሀ. አለኝ ለ. የለኝም

   9.2 የ4ኛ ክፍል- ሀ. አለኝ ለ. የለኝም
10. ለጥያቄ ቁጥር 9 መልስዎ «አለኝ» የሚል ከሆነ፣ መርሐትምህርቱን ከየት አገኙት?

    ሀ. ከዳይሬክተርዎ፤ ለ. ከንብረት ክፍል፤

    ሐ. በትምህርት ቤትዎ አብሮዎት ከሚሠራ ባልደረባዎ፤

    መ. ከትምህርት ክፍልዎ /ዲፓርትመንት/፤

    ሠ. ከትምህርት ቤትዎ ውጭ ካሉ ምንጮች በራስዎ ጥረት፤

    ረ. በሌላ መንገድ ወይም ከሌላ ምንጭ የተገኘ ከሆነ ይገለፅ____________
11. ለጥያቄ ቁጥር 9 መልስዎ «የለኝም» የሚል ከሆነ ዓመታዊ የትምህርት ዕቅድዎን ለማዘጋጀትና ለአጠቃላይ ለማስተማር ሥራዎ በመመሪያትና

በማመሳከሪያነት የሚገለገሉበት አማራጭ ምንድን ነው?/ ከአንድ በላይ መልስ መስጠት ይችላሉ/

ሀ. አዲሱን የመምህሩ መምሪያ

ለ. አዲሱን የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ

ሐ. የቀድሞ መርሐትምርት

መ. የቀድሞው የተማሪው መማሪያ

ሠ. የቀድሞው የመምህሩ መምሪያ

ረ. ከአእምሮዎ አፍልቀው

12. አዲስ የተዘጋጀው የመምህሩ መምሪያ አለዎት?

ሀ. አለኝ ለ. የለኝም

13. በመርሐትምህርቱ ወይም በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ከተጠቀሙት መርጃ መሣሪያዎች መካከል በቀላሉ ሊገኙ/ሊሠሩ/ የማይችሉት ምን ያህሉ ናቸው?

ሀ. በጣም ብዙዎቹ ሊገኙ አይችሉም ለ. ብዙዎቹ ሊገኙ አይችሉም

ሐ. ጥቂቶቹ ሊገኙ አይችሉም መ. ሁሉም ሊገኙ የሚችሉ ናቸው

ሠ. አዲሱን መርሐትምርህትና የመምህሩ መምሪያ አይቻቸው አላውቅም

14. ለሚያስተምሩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓይነት የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ በትምህርት ቤቱ አለ?

14.1 ለ3ኛ ክፍል ሀ. አለ ለ. የለም

14.2 ለ4ኛ ክፍል ሀ. አለ ለ. የለም

15. ለጥያቄ 14 መልስዎ «አለ» የሚል ከሆነ ለተማሪዎችዎ ምን ያህል ተዳርሷል?

ሀ ለእያንዳንዱ ተማሪ ደርሷል።

ለ. አንድ መጽሐፍ ለ2-3 ተማሪ ደርሷል።

ሐ. አንድ መጽሐፍ ለ4-5 ተማሪ ደርሷል።

መ. አንድ መጽሐፍ ለ6ና ከዚያ በላይ ተማሪ ደርሷል።

16. የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን የሚመለከት ትምህርት ራሱን የቻለ አንድ ኮርስ ሆኖ ተምረውታል?

ሀ. ተምሬያለሁ ለ. አልተማርኩም ሐ. ትምህርቱ ራሱ መኖሩን አላውቅም

17. በሥልጠናው ዘመን /ሥልጠና ወስደው ከሆነ/ ስለመርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም በቂ የሆነ ተግባራዊ ልምምድና ትምህርት ያገኙ ይመስልዎታል?

ሀ. ይመስለኛል። ለ. አይመስለኝም። ሐ. አስተያየት ለመስጠት ይከብደኛል።

18. ለጥያቄ 17 መልስዎ «ይመስለኛል» የሚል ከሆነ ኮርሱ የመርጃ መሣሪያዎችን አዘገጃጀትና አጠቃቀም በሚመለከት ላለብዎት ኃላፊነት በብቃት አዘጋጅቶኛል ብለው ያስባሉ?

ሀ. በከፍተኛ ደረጃ አዘጋጅቶኛል።  ለ. በመጠኑ አዘጋጅቶኛል።

ሐ. ምንም አላዘጋጀኝም።  መ. ሥልጠና አልወሰድኩም።

19. የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን የሚመለከት ትምህርት በኮርስ ደረጃ ተምረው ከሆነ ትምህርቱ ለማስተማር ሥራዎ የሚሰጠውን ጥቅም በሚገባ ያወቁት መቼ ነው?

ሀ. ትምህርቱን በምከታተልበት ወቅት።

ለ. ትምህርቱን ጨርሼ ወደ ሥራ ዓለም ከገባሁ ከተመለስኩ በኋላ።

ሐ. የተጠቀሰውን ትምህርት አልተማርኩም።  መ. ሌላ መልስ ካለ ይገለጽ_____

20. ስለማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች ትምህርት አግኝተው ከሆነ ትምህርቱን በእርጋታ ለመከታተል በወቅቱ በቂ ጊዜ አግኝተዋል?

ሀ. አግኝቻለሁ።  ለ. አላገኘሁም።

ሐ. ትምህርቱን አልተከታተልኩም።  መ. ሌላ መልስ ካለ ይገለጽ_____

21. ለጥያቄ 17 መልስዎ «አዎ» የሚል ከሆነ የመርጃ መሣሪያዎችን አመራረጥ አዘገጃጀትና አጠቃቀም የሚመለከት ጽሑፍ በተቀነባበረ መልኩ (Handout) በአሠልጣኝዎ ተሰጥቶዎታል?

ሀ. አዎ  ለ. የለም  ሐ. ሌላ መልስ ካለ ይገለጽ_____

22. ለጥያቄ 21 መልስዎ «አዎ» የሚል ከሆነ ጽሑፉ በሥራዎ ላይ ምን ያህል ጠቀመዎት?

ሀ እጅግ በጣም  ለ በጣም  ሐ. በመጠኑ  መ. ምንም አልጠቀመኝም

ሠ. ጽሑፉ ትዝ ብሎኝ አንብቤው አላውቅም

23. ለጥያቄ 17 መልስዎ «የለም» የሚል ከሆነ እንግዲያው ስለ መረጃ መሣሪያዎች ያለዎትን ዕውቀት ከየት አገኙት?

ሀ. ከመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም

ለ. በልዩ ልዩ አጋጣሚ ከግል ተሞክሮ

ሐ. ከአጭር የማስተዋወቂያ ስብሰባ እና/ ወይም ወርክሾፕ

መ. በትምህርት ቤትዎ ካለው የትምህርት ሚዲያ ማዕከል

ሠ. ሌላ ካለ ይገለጽ_____

24. በመርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ላይ ባተኮረ ወርክሾፕ ወይም ሲሚናር ተካፍለው ያውቃሉ?

ሀ. ከአንድ ጊዜ በላይ ተካፍያለሁ።  ለ. አንድ ጊዜ ተካፍያለሁ።

ሐ. በጭራሽ አልተካፈልኩም።

25. ለጥያቄ 24 መልስዎ አዎንታዊ ከሆነ ወርክሾፑ የተዘጋጀው በምን ደረጃ ነበር? /ከአንድ በላይ መልስ መስጠት ይቻላሉ/

ሀ. በትምህርት ቤት ደረጃ

ለ. በተቀራረቡ አካባቢዎች ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች በአንድ ላይ /በክላስተር ደረጃ/

ሐ. በወረዳ ደረጃ መ. በዞን ደረጃ ሠ. በክልል ደረጃ ረ. በአገር ዓቀፍ ደረጃ

26. መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት የሚያስፈልገው በቂ ዕውቀትና ችሎታ ያለዎት ይመስልዎታል?

ሀ. ከበቂ በላይ አለኝ ለ. በቂ አለኝ ሐ. በቂ የለኝም መ. ምንም ዕውቀት የለኝም

27. በትምህርት ቤትዎ የትምህርት ሚዲያ ማዕከል አለ?

ሀ. አለ ለ. የለም

28. ለጥያቄ 27 መልስዎ «አዎ» የሚል ከሆነ ማዕከሉ በአሁኑ ጊዜ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?

ሀ. ሁል ጊዜ ክፍት ነው:: ለ. አንዳንድ ጊዜ ክፍት ነው

ሐ. ሁልጊዜ ዝግ ነው:: መ. አንዳንድ ጊዜ ዝግ ነው::

ሠ. ሌላ ካለ ይገለጽ::______________________

29. ለጥያቄ 27 መልስዎ «አዎ» የሚል ከሆነ ለማዕከሉ የተመደበ አስተባባሪ መምህር (ቴክኒሽያን) አለ? ሀ. አዎ ለ. የለም

30. ልዩ ልዩ መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት መመሪያ የሚሠጥ ጽሑፍ/ማኑዋል/ ከሚመለከተው ማዕከል/ የትምህርት የጽሕፈት ቤት ተሰጥቶዎት ያውቃል?

ሀ. ከአንድ ጊዜ በላይ ተሰጥቶኛል:: ለ. አንድ ጊዜ ተሰጥቶኛል::

ሐ. በጭራሽ አልተሰጠኝም::

31. አንድ የተወሰነ የመርጃ መሣሪያን ለማዘጋጀት የሚረዳዎትን ዕውቀትና ችሎታ ከሚዲያ ማዕከሉ ሠራተኛ /መምህር/ ጠይቀው ያገኙበት ጊዜ አለ?

ሀ. በርካታ ጊዜ አግኝቼአለሁ ለ. አልፎ አልፎ አግኝቼአለሁ ሐ. በጭራሽ የለም

32. የመርጃ መሣሪያዎችን አዘገጃጀት በሚመለከት ሊሰጥዎት ከሚችለው ሙያዊ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ አኳያ በትምህርት ቤትዎ የትምህርት ሚዲያ ማዕከል ሠራተኛ ብቃት ምን ያህል ይተማመናሉ?

ሀ. ሙሉ እምነት አለኝ:: ለ. መጠነኛ እምነት አለኝ::

ሐ. ምንም እምነት የለኝም::

33. በእርስዎ አመለካከት የማስተማር-መማርን ተግባር ስኬታማ ለማድረግ የትምህርት ሚዲያ ማዕከላት የሚጫወቱት ሚና ምን ያህል ነው?

ሀ. በጣም ከፍተኛ ሚና ለ. ከፍተኛ ሚና ዝቅተኛ ሚና

መ. በጣም ዝቅተኛ ሚና ሠ. ምንም ሚና አይጫወቱም

34. ባሉበት ወረዳ የትምህርት ሚዲያ ማዕከል አለ?

ሀ. አለ ለ. የለም ሐ. መኖር/አለመኖሩን አላውቅም

35. በሚከተለው ዓረፍተ ነገር ምን ያህል ይስማማሉ? ትምህርት ቤትዎ በፋብሪካ የተሠሩ መርጃ መሣሪያዎችንና ተዛማጅ ቁሳቁሶችን ለመግዛ የሚሆን በጀት የለውም::

ሀ. በጣም እስማማለሁ:: ለ. እስማማለሁ::

ሐ. አልስማማም:: መ. በጣም አልስማማም::

36. ተማሪዎች በመርጃ መሣሪያዎች ታግዘው ሲማሩ የአቀባበልና የማስታወስ ችሎታቸው ከፍ ይላል ብለው ያምናሉ?

ሀ. በጣም አምናለሁ:: ለ. በመጠኑ አምናለሁ::

ሐ. አላምንም:: መ. በፍጹም አላምንም::

37. ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በአካባቢዎ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ምን ያህል መርጃ መሣሪያዎችን አዘጋጅተዋል?

ሀ. ከ8 በላይ ለ. ከ5-8 ሐ. ከ1-4 መ. ምንም አላዘጋጀሁም

38. ተማሪዎች መርጃ መሣሪያዎችን ለማሠራት እና/ወይም ከቤታቸው እንዲያመጡ ለማድረግ ምን ያህል ሞክረዋል?

ሀ. ለበርካታ ጊዜያት ለ. አልፎ አልፎ ሐ. በጭራሽ ሞክሬ አላውቅም

39. ከትምህርት ቤትዎ ውጪ ካሉ ምንጮች ልዩ ልዩ መርጃ መሣሪያዎችን በውሰትም ሆነ በስጦታ መልክ ለማግኘት ምን ያህል ጥረት እያደረጉ ነው?

ሀ. በጣም በርካታ ጥረት

ለ. መካከለኛ ጥረት

ሐ. አነስተኛ ጥረት

መ. ምንም ጥረት አላደረግሁም

40. የትምህርት ቤቱን የትምህርት ሚዲያ ማዕከል ዘወትር እንደትጠቁሙ በትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች ወይም በማዕከከሉ ተጠሪ በኩል ማሳሰቢያና ቅስቀሳ ተሰጥቶ ያውቃል?

ሀ. ብዙ ጊዜ ተሰጥቶአል:: ለ. አንዳንድ ጊዜ ተሰጥቶአል::

ሐ. ማሳሰቢያ ተሰጥቶ አያውቅም:: መ. እኔ ሰምቼ አላውቅም::

ሠ. ሌላ መልስ ካለዎት::..............................

41. በመምህራን መገምገሚያ ቅጽ ውስጥ የመርጃ መሣሪያን መጠቀም የሚመለከት ነጥብ መካተቱን ያውቃሉ? ሀ. አውቃለሁ ለ. አላውቅም

42. የዞኑ/የወረዳው ማዕከል የሚገኝበት አካባቢ ከርስዎ ትምህርት ቤት በግምት ምን ያህል ኪ.ሜ ይርቃል?

ከ20 በላይ ለ. ከ10-19 ሐ. ከ1-9

43. ከዚኑ ወይም ከወረዳው የትምህርት ሚዲያ ማዕከል ለሙያዎ የሚረዳ የአጭር ጊዜ ሥልጠና የምክር ወይም ሌላ ዓይነት አገልግሎት አግኝተው ያውቃሉ?

ሀ. አውቃለሁ ለ. አላውቅም

44. ለጥያቄ 44 መልስዎ «አውቃለሁ» የሚል ከሆነ መቼና እንዴት ሊያውቁ እንደቻሉ ይግለጹ።

---

45. ስለመርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም እንዲሁም ስለትምህርት ቤቱ ሚዲያ ማዕከል ሁኔታና ሌሎችም በዚህ መጠይቅ ውስጥ ያልተዳሰሱ አጠቃላይ ሐሳቦችና አስተያየቶች ካለዎት ቀጥሎ ባለው ክፍት ሥፍራ ላይ ይጻፉ።

---

# አባሪ 4

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## ድኅረ ምረቃ መርሐግብር
## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

**በቦንጋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ዕርከን ትምህርት ቤቶች ቅርንጫፍ የሚዲያ ማዕከላት ሠራተኞች/ቴክኒሽያኖች/ የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ**

ዓላማ:- የቋንቋ ማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን በሚመለከት በመምህራንና በትምህርት ቤቶች በኩል በመሠራት ላይ የሚገኘውን ሥራ፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን፣ ያሉትንና የጎደሉትን ሁኔታዎች በተጨባጭ ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው፡፡

ማሳሳቢያ:-

- ስምዎን መጻፍ አያስፈልግዎት፡፡
- የጥናቱ ውጤት አስተማማኝ እንዲሆን በጣም ግልዕ ሆነው ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ እጠይቃለሁ፡፡
- ግልዕ ሆነው የሚሰጡት ማንኛውም መረጃ ለጥናቱ ዓላማ ብቻ ከሚውል በስተቀር በሚስጥር እንደሚያዝ አረጋግጣለሁ፡፡
- ጥያቄዎቹን አንድም ሳያስቀሩ በመመለስ የተሟላ መረጃ እንዲሰጡ አደራ እላለሁ፡፡
- ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል በእርስዎ በኩል ትክክለኛ ነው ብለው ያመኑበትን መልስ የሚወክለውን ፊደል ይክበቡት፡፡
- ለአንዳንድ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች የተለየ ሌላ መልስ ሲኖርዎትና እንዲሁም ምርጫ ለሌላቸው ክፍት ጥያቄዎች መልስዎን ለዚሁ በተዘጋጁት ክፍት ሥፍራዎች ላይ ይጻፉ፡፡

ለትብብርዎ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን ከወዲሁ አቅርባለሁ፡፡

## ክፍል አንድ፣ የግል ሁኔታ መረጃዎች፤

1. የሚሠሩበት ትምህርት ቤት፣ ________________
2. ፆታ፣ ሀ. ወንድ ለ. ሴት
3. የአገልግሎት ዘመን፣

   ሀ. ከ1-5 ዓመት ለ. ከ6-10 ዓመት ሐ. ከ11-15 ዓመት መ. ከ16- ዓመት በላይ
4. የትምህርት ደረጃ፣

   ሀ. 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች/ ለ. የምስክር ወረቀት/ መምህራን ማስልጠኛ ተቋም

   ሐ. 12+ 1ኛ ዓመት ኮሌጅ መ. ዲፕሎማ ሠ. ሌላ ካለ ይገለጽ________
5. በኮሌጅ ደረጃ ሠልጥነው ከሆነ የሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት ዐቢይ ___ንዑስ___
6. የተመረቁበት ዓ.ም. ________________

## ክፍል ሁለት፣ አጠቃላይና ዝርዝር መረጃዎች፤

1. ለማዕከሉ የተመደበ አስተባባሪ መምህር /ቴክኒሽያን/ አለ? ____________
2. የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን በሚመለከት ትምህርት ወስደዋል?

   ሀ. በኮሌጅ ደረጃ ለ. በተቋም ደረጃ ሐ. ምንም አልወሰድኩም
3. ለማዕከል ቴክኒሽያንነት የሚያበቃ ልዩ ሥልጠና አግኝተዋል?

   ሀ.አግኝቻለሁ ለ. አላገኘሁም
4. ሥልጠናውን አግኝተው ከሆነ የሠለጠኑት በምን ሙያ ነው?

   ሀ. በእንጨት ሥራ ለ. በብረታ ብረት ሥራ ሐ. በሽመና መ. በቅርፃ ቅርፅ

   ሠ. በንድፍ ሥራ ረ. በሥዕል ሥራ
5. ልዩ ሥልጠና አግኝተው ከሆነ ለምን ያህል የጊዜ ርዝመት?

   ሀ. ከ1 እስከ 7 ቀን ለ. ከ8 እስከ 15 ቀን ሐ. ከ16 ቀን እስከ 1 ወር

   መ. ከ1ወር እስከ 2 ወር ሠ. ከ2 ወር በላይ
6. ልዩ ሥልጠና ለመጨረሻ ጊዜ ካገኙ ምን ያህል ጊዜ ሆነዎት?

   ሀ. ከ1 እስከ 2 ዓመት ለ. ከ3 እስከ 5 ዓመት

   ሐ. ከ6 እስከ 10 ዓመት መ. ከ11 ዓመት በላይ
7. ልዩ ሥልጠና አግኝተው ከሆነ ስንት ጊዜ?

   ሀ. ከአንድ ጊዜ በላይ ለ. አንድ ጊዜ ሐ. ምንም አላገኘሁም
8. የማዕከሉ አስተባባሪ በግልጽ የታወቀ /የተቀመጠ/ የሥራ ድርሻ አለው? /ተሰጥቶታል?/ ካለ ዝርዝሩ ይገለጽ፤ ________________
9. መምህርነዎት/ነበሩ? በየትኛው ደረጃ? ____________



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

10. ለማዕከል አስተባባሪነት የመደበዎት ማን ነው?

ሀ. የት/ቤቱ አስተዳደር ለ. የመምህራን ጉባዔ

ሐ. የወረዳው ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት

መ. ሌላ ካለ ይገለጽ..........................

11. ለዚህ ሥራ የተመረጡ በምን መሥፈርት ተመዝነው ነው?..........................

12. የ1ኛ ደረጃን ሥርዓተ ትምህርት በተለይም የቋንቋን ሥርዓተ-ትምህርት ምን ያህል ያውቁታል?..........................

13. የመምህራን ዕለታዊና ወርሃዊ የማዕከል ተሳትፎ መመዝገቢያ መዝገብ አለ?

ሀ. አዎ ለ. የለም

14. በአሁን ጊዜ የመምህራን ዕለታዊና ወርሃዊ የማዕከል ተሳፎ ክትትልና ምዝገባ ይደረጋል?

ሀ. አዎ ለ. አይደረግም

15. ማዕከሉ ለመምህራን የሚሰጠውን የአገልግሎት ዓይነትና መጠን መዝግቦ የሚይዝበት መዝገብና አሠራር አለው? የማዋሻ ቅጽ ተዘጋጅቷል?..........................

16. በማዕከሉ ውስጥ የሚገኙ መርጃ መሣሪያዎችን በርዕስ፣ በይዘት፣ በመጠንና በአገልግሎት የሚገልጽ ዝርዝር /ካታሎግ/ ተዘጋጅቷል? ሀ. አዎ ለ. የለም

17. የ1ኛ ሳይክል አማርኛ መምህራን ወደ ማዕከሉ ምን ያህል ጊዜ ይመጣሉ?

ሀ. በብዛት ለ. በአነስተኛ ቁጥር /በመጠኑ/ ሐ. በጭራሽ አይመጡም

18. የአንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ማዕከሉን የሚያዘወትሩት በይበልጥ መቼ ነው?

ሀ. ዓመቱን በሙሉ ለ. በዓመቱ መጀመሪያ ሐ. በግምገማ ሰሞን

19. የተለየ የሙያ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ የሚጠይቁ የአንደኛ ሳይክል አማርኛ መምህራን ምን ያህል ናቸው?

ሀ. አብዛኛዎቹ ለ. ግማሽ የሚሆኑት ሐ. በጣም ጥቂቶቹ መ. ማንም የለም

20. ልዩ ልዩ መርጃ መሣሪያዎች እንዲሠሩላቸው በተለያየ ጊዜ ጥያቄ የሚያቀርቡ የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን ምን ያህል ናቸው?

ሀ. አብዛኛዎቹ ለ. ግማሽ የሚሆኑት

ሐ. በጣም ጥቂቶቹ መ. ማንም የለም

21. ማዕከሉ መምህራን ለመዋስ የሚጠይቁትን መርጃ መሣሪያ ምን ያህል ያሟላላቸዋል?

ሀ. የሚጠይቁትን ሁሉ ለ. በከፊል ሐ. ምንም አያሟላም

22. ማዕከሉ የመምህራን የውስት ጥያቄ የማያሟላ ከሆነ ለምን?________

23. የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል የአማርኛ መምህራን የራሳቸውን መርጃ መሣሪያ እራሳቸው ለማዘጋጀት ተስማሚ ሥፍራና የሥራ መሣሪያዎች ፍለጋ ወደ ማዕከሉ ምን ያህል ጊዜ ይመጣሉ?

ሀ. አዘውትረው ይመጣሉ::  ለ. አንዳንድ ጊዜ ይመጣሉ ::

ሐ. በጭራሽ አይመጡም::

24. የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል የአማርኛ መምህራን ወደ ማዕከሉ መርጃ መሣሪያ ለማዘጋጀት አዘውትረው የማይመጡ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል?________

25. ማዕከሉ ስለመርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ለመምህራን ትምህርት ሥልጠና በተደራጀ መልኩ የሰጠበት ጊዜ አለ?

ሀ. ከአንድ ጊዜ በላይ  ለ. አንድ ጊዜ  ሐ. ምንም የለም

26. በማዕከሉ ውስጥ ስለመርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም የሚያብራሩ ጽሑፎች አሉ?

26.1 ማኑዋል  ሀ. አለ  ለ. የለም

26.2 ሀንድ አውት  ሀ. አለ  ለ. የለም

26.2 መጽሐፍ  ሀ. አለ  ለ. የለም

27. የቋንቋ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት መሣሪያዎች /መርሐትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ/ በማዕከሉ ውስጥ ወይም በእጅዎ ይገኛሉ/ በተለይ የ3ኛና የ4ኛ ክፍል/

27.1 የ3ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት  ሀ. አለ  ለ. የለም

27.2 የ3ኛ ክፍል የተማሪው መጽሐፍ  ሀ. አለ  ለ. የለም

27.3 የ3ኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ  ሀ. አለ  ለ. የለም

27.4 የ4ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት  ሀ. አለ  ለ. የለም

27.5 የ4ኛ ክፍል የተማሪው መጽሐፍ  ሀ. አለ  ለ. የለም

27.6 የ4ኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ  ሀ. አለ  ለ. የለም

28. ማዕከሉ የተመደበ በጀት አለው? ሀ. አለው  ለ. የለውም

29. በጀት ካለው ምን ያህል ነው?________

30. ለማዕከሉ በጀት ሠርተው እንዲፈቀድ ለትምህርት ቤቱ ጥያቄ አቅርበው ያውቃሉ? ምን ምላሽ አገኙ?________

31. ማዕከሉ የሚጠበቅበትን አገልግሎት ለመስጠት ይችል ዘንድ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር የሚደረግለት ድጋፍና ክትትል ምን ያህል ነው?

ሀ. በጣም ከፍተኛ ነው::  ለ. አቅም በፈቀደ መጠን ነው::

ሐ. በጣም ዝቀተኛ ነው::          መ. ዝቅተኛ ነው   ሠ. ምንም የለም::

32. ማዕከሉ፣ የማዕከሉን አገልግሎት ለማሻሻል የሚረዳ የማቴርያልና የገንዘብ ድጋፍ ከትምህርት ቤቱ /መንግሥታዊ ካልሆኑ አካሎች/ አግኝቶ ያዉቃል?

ሀ. ከአንድ ጊዜ በላይ::   ለ. አንድ ጊዜ::   ሐ. አግኝቶ አያውቅም::

33. ለጥያቄ 32 መልስዎ አዎንታዊ ከሆነ ድጋፍ ያደረገው አካል ማን ነው?

ሀ. የትምህርት ቤቱ ወላጅ መምህር ህብረት/ወመህ/

ለ. ግለሰብ ዕርዳታ ሰጪ

ሐ. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

መ. ሌላ ካለ ይገለጽ________

34. ማዕከሉ መንግሥታዊ ካልሆኑ አካሎች ድጋፍ አግኝቶ ከሆነ የድጋፉ ዓይነት ምንድነው? /ከአንድ በላይ መልስ ሊሰጥ ይችላል/

ሀ. የማዕከሉን ሕንጻ ማሠሪያ/ማስፋፊያ

ለ. ልዩ ልዩ የመርጃ መሣሪያዎች መግዣ

ሐ. የጽሕፈት መሣሪያዎች

መ. ሌላ ካለ ይገለጽ________

35. ስለማዕከላት አደረጃጀት ወቅታዊ የጽሑፍ መመሪያ ደርሷችሁ ያውቃል? ከማን? መቼ?________________________________________________

36. ስለማዕከላት አደረጃጀትና አሠራር የሚያወሳ ጽሑፍ በእጅዎ ይገኛል? ከየት አገኙት?______________________________

37. ከ2000 ዓ.ም. መስከረም ወዲህ በማዕከሉ በአማርኛ ቋንቋ ዲፓርትመንት የዘጋጁት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት ምን ያህል ነው?

ሀ. ከ1-10   ለ. ከ11-20   ሐ. ከ21-30   መ. ከ30 በላይ

38. ከ2000 ዓ.ም. መስከረም ወዲህ ከትምህርት ሚኒስቴር ወይም ከክልል ትምህርት ቢሮ ወይም ከዞን/ወረዳ/ ማዕከላት የደረሳችሁ የአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያ አለ?

38.1 ካለ ዓይነቱ ይዘርዘር፣____________

38.2 ካለ ብዛቱ ምን ያህል ነው?

ሀ. ከ1-5   ለ. 6-10   ሐ. 11-15   መ. ከ16-20   ሠ. ከ21 በላይ

39. ዞን/ወረዳ/ ትምህርት ሚዲያ ማዕከል የት እንደሚገኝ/መኖሩን/ ያውቃሉ?

ሀ. አዎ   ለ. አላውቅም

40. ከ2000 ዓ.ም. መስከረም ወዲህ ወደ ዞን/ወረዳ ትምህርት ሚዲያ ማዕከሉ ለአዳዲስ ግኝቶች፣ ፈጠራዎች የአሠራርና የአጠቃቀም ዘዴዎች ልምድ

ለመለዋወጥ ምን ያህል ጊዜ ሄደው ያወቃሉ? ሄደው ጎብኝተው ከሆነ በማን ወጪ? ____________________

41. የትምህርት ቤት ቅርንጫፍ የትምህርት ሚዲያ ማዕከል ተጠሪ ቢሆንም፣ የሚታወቁበት የሥራ መደብ ምንድን ነው?

    ሀ. በሚዲያ ቴክኒሺያንነት    ለ. በመምህርነት    ሐ. በአስተዳደር ሠራተኛነት

    መ. ሌላ ካለ ይገለጽ____________

42. የአንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለማዕከሉ /ጠቀሜታ/ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? ዓላማና ተግባሩን ያደንቃሉ? ይደግፋሉ? ያውቃሉ? ያምኑበታል?____________________

43. የአንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚዲያ ማዕከላትን ዓላማና ተግባር እንዲያውቁ፣ ለመማር- ለማስተማሩ ሥራ የሚሰጡትን ከፍተኛ ግልጋሎት አምነው ዘወትር እንዲጠቀሙባቸው ቅስቀሳ ይደረጋል? መቼ? እንዴት? የመምህራኑስ አመለካከትና ምላሽ ምን ይመስላል? ____________

44. በአሁኑ ሰዓት የሚያስተምሩ ከሆነ በሳምንት ስንት ክፍለ ጊዜ ያስተምራሉ? በዚህ የተነሣ በማዕከሉ ላይ የደረሰ ጫና አለ?____________________

## አባሪ 5

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድኅረ ምረቃ መርሐግብር

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## ከርዕሰ መምህራን ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ ጥያቄዎች

1. ትምህርት ቤትዎ ሚዲያ ቅርንጫፍ ማዕከል አለው?_______________
2. ካለ አደረጃጀቱን እንዴት ነው?_______________
3. የማዕከሉን ሠራተኛ /ቴክኒሽያን/ የሚመድበው ማን ነው?
   ሀ. የትምህርት ቤቱ አስተዳደር
   ለ. የመምህራን ጉባዔ/ በምርጫ/
   ሐ. የወረዳው ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት
   መ. ሌላ ካለ ይገለጽ_______________
4. የማዕከሉ አስተባባሪ በምን መመዘኛ ነው የሚመደበው?
   ሀ. በመርጃ መማሪያ አዘገጃጀት ያለው ዕውቀትና ችሎታው ከሌሎች መብለጡ ተረጋግጦ /ተወዳድሮ/
   ለ. ከወረዳ ጽሕፈት ቤት በምደባ ተልኮልን
   ሐ. ከትርፍ መምህራን መካከል ተመርጦ
   መ. ሌላ ካለ ይገለጽ_______________
5. የማዕከል ሠራተኛ መሆን ልዩ ጥቅም ያስገኛል ወይ?_______________
6. የማዕከሉ አስተባባሪ ያለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲችል የማስተማር ሥራ ጫናው /የክፍለ ጊዜያት ብዛት/ ተቀንሶለታል? በሳምንት ስንት ክፍለ ጊዜያት ያስተምራል?_______________
7. የማዕከሉ ሠራተኛ ልዩ ሥልጠና እንዲያገኝ የተደረገበት ጊዜ አለ? ለምን ያህል ጊዜ ? መቼ? የት?_______________
8. ትምህርት ቤትዎ መርጃ መማሪያዎችን ለመሥራት የሚያስፈልገውን ወጪ የሚያገኘው ከየት ነው?
   ሀ. ከራሱ የውስጥ ገቢ     ለ. ከመንግሥስት ከሚያገኘው በጀት
   ሐ. ከተማሪዎች ከሚሰበስብ ገንዘብ     መ. በጀት የለውም
   ሠ. ሌላ ካለ ይገለጽ_______________
9. ለትምህርት ሚዲያ ማዕከላት ሥራ ማስኬጃ የሚውል በጀት ሠርታችሁ ጠይቃችኋል? ምን ምላሽ አገኛችሁ?_______________

10. መምህራን መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀትና ለመጠቀም የሚያስፈልገውን ዕውቀት፣ ችሎታና አመለካከት በየጊዜው እንዲያሻሽሉ ለማድረግ የባለሙያ ምክርና ድጋፍ እንዲያገኙ ተሞክሯል?

ሀ. ብዙ ጊዜ ተሞክሯል ለ. ጥቂት ጊዜ ተሞክሯል

ሐ. ምንም ጊዜ አልተሞከረም

11. ለላይኛው ጥያቄ መልስዎ «አዎ» የሚል ከሆነ ድጋፉን እንዲያገኙ የተደረገው በምን መልክ መንገድ ነው?

ሀ. በአጫጭር ወርክሾፕ ለ. በጽሑፍ ሐ. ሌላ ካለ ይገለጽ______________

12. የመርጃ መሣሪያዎችን አዘገጃጀትና አጠቃቀም በሚመለከት በመምህራን መካከል የልምድልውውጥ የሚደረግበትን መንገድ /መድረክ አመቻችታችኋል /አዘጋጅታችኋል?

ሀ. ብዙ ጊዜ አዘጋጅተናል ለ. ጥቂት ጊዜ አዘጋጅተናል ሐ. አዘጋጅተን አናውቅም

13. የላይኛው መልስዎ አዎንታዊ ከሆነ ምን ዓይነት የልምድ ልውውጥ /መድረክ/ ነበር የተዘጋጀው? / ከአንድ በላይ መልስ ሊኖርዎ ይችላል/

ሀ. በትምህርት ቤቶች መካከል በተወካይ መምህራንና በማዕከል ሠራተኞች አማካኝነት

ለ. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በትምህርት ክፍሎች መካከል

ሐ. በአንድ ትምህርት ክፍል ወስጥ በግለሰብ መምህራን መካከል፣ የክፍል ጉብኝት በማድረግ

መ. በትምህርት ቤት አጠቃላይ ስብሰባ በማድረግ

ሠ. ሌላ ካለ ይገለጽ______________

14. በመርጃ መሣሪያዎች ዝግጅትና አጠቃቀም ረገድ ትጋትና የላቀ ውጤት ለሚያሳዩ መምህራን ማነቃቂያ ተሰጥቶ ያውቃል?

ሀ. በየጊዜው ይሰጣል:: ለ. አልፎ አልፎ ይሰጣል::

ሐ. ተሰጥቶ አያውቅም:: መ. ስለዘህ ጉዳይ እኔ መረጃ የለኝም::

15. ለላይኛው ጥያቄ መልስዎ አዎንታዊ ከሆነ ማነቃቂያው በምን መልክ ነው የሚሰጠው/የተሰጠው?

ሀ. በቃል ምሥጋና ለ. በጽሑፍ ምሥጋና

ሐ. ለትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብ በመግለጽ/በማወጅ

መ. የክረምትም ሆነ ሌላ የሙያ ማሻሻያ ትምህርት ዕድል ቅድሚያ በመስጠት

ሠ. ሌላ ካለ ይገለጽ______________

16. በአካባቢ የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎች ለመርጃ መሣሪያዎች ዝግጅት የሚውሉበት መንገድ ተፈልጎ ግኝቱን ለመምህራን ያስተዋወቃችሁበት ጊዜ አለ?

ሀ. ብዙ ጊዜ አስተዋውቀናል::   ለ. ጥቂት ጊዜ አስተዋውቀናል::

ሐ. አስተዋውቀን አናውቅም::   መ. ልዩ ግኝት እስካሁን አላጋጠመንም::

17. የንብረት አጠቃቀማችሁ ምን ያህል ተገቢ ነው? የሚሠሩት መርጃ መሣሪያዎች ከትምህርት ዓላማዎችአንፃር ፋይዳ ያላቸው መሆናቸውን፣ ለየትምህርት ዓይነቶቹና ምዕራፎች ተዛማጅነታቸውን፣ ለተማሪዎች የሚመጥኑና የተፈለገውን ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን ለመከታተል ይሞክራሉ?

ሀ. ዘወትር ይሞክራሉ   ለ. አልፎ አልፎ ይሞክራሉ ሐ. ተሞክሮ አያውቅም

18. ለላይኛው ጥያቄ መልስዎ አዎንታዊ ከሆነ ክትትሉን /ግምገማውን የሚያደርገው አካል ማን ነው?

ሀ. የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለ. የትምህርት ቤቱ የሥርዓተ ትምህርት ኮሚቴ

ሐ. ለዚሁ ዓላማ የተቋቋመ የባለሙያዎች ቡድን

መ. ሌላ ካለ ይገለጽ________________

19. የትምህርት ቤታችሁ ማዕከል መርጃ መሣሪያዎችን በውስት ወይም በስጦታ አግኝቶ ያውቃል?

ሀ. ያውቃል   ለ. አያውቅም

20. ለላይኛው ጥያቄ መልስዎ «ያውቃል» የሚል ከሆነ ከማን ከማን ነው ያገኘው?

ሀ. ከወረዳ /ዞን/ ትምህርት ሚዲያ ማዕከል ለ. መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች

ለ. ከወላጅ መምህር ሕብረት   መ. ሌላ ካለ ይገለፅ________________

21. የማዕከሉ አስተባባሪ በግልፅ የታወቀ/ የተቀመጠ/ የሥራ ኃላፊነትና ድርሻው ምንድን ነው?________________

22. በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሬዲዮ አለ? ምን ያህል? ካለስ ይሠራል?________________

23. በትምህርት ቤቱ ውስጥ ቴሌቪዥን አለ? ካለስ ይሠራል?________________

24. የቴሌቪዥን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ቴክኖሎጂ/ ማይክሮዌብ በዞኑ/ በወረዳው አለ? /ቴሌቪዥን ገብቷል?/________________

25. ከልዩ ልዩ ዲፓርትመንቶች የተውጣጡ ፍላጎትና መጠነኛ ተሰጥኦ ያላቸውን መምህራን ያካተተ የቴክኖሎጂ ኮሚቴ ቢቋቋም የሚያመጣው ለውጥ ይኖር ይመስሎታል?________________

26. የጠመኔ አቅርቦት ችግር አለባችሁ? ከየት ነው የምታገኙት? ምን ያህል?

________________

27. በትምህርት ቤቱ ውስጥ የየክፍሉ የተማሪዎች ብዛት በአማካይ ምን ያህል ነው?

________________

28. የጥቁር ሠሌዳ ችግር /እጥረት/ አለ? ችግር ካለ ምን መፍትሔ ለማግኘት ተሞክሯል? ____________

29. በየክፍሉ ከጥቁር ሠሌዳ ሌላ ሌሎች ሠሌዳዎች አሉ? ካለ ዝርዝራቸው ይገለጽ፤

____________

30. የትምህርት ቤት ሚዲያ ማዕከል አስተባባሪው በትምህርት ቤቱ አስተዳደር የሚታወቅበት የሥራ መደብ መምህርነት ነው ወይስ ድጋፍ ሰጪ የአስተደደር ሠራተኝነት ? መምህር አይደላችሁም ተብለው የደረጃ ዕድገት የተነፈጋቸው አሉ፤

____________

31. መምህራን የትምህርት ሚዲያ ማዕከላትን ዓላማና ተግባር /ጠቀሜታ/ ዓውቀውና አምነው ዘወትር እንዲጠቀሙባቸው ግፊት ያደርጋሉ? በምን መልክ ? የመምህራኑስ አመለካከትና ዓቋም ምንድን ነው? ____________

32. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ እጥረት አለ?

____________

33. የተማሪው መማሪያ መጻሕፍት በወቅቱ ትምህርት ቤት ይደርሳሉ?

____________

34. የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ትምህርት ቤት የሚደርሰው በአማካይ በየትኛው ወር ነው? ____________

35. የተማሪ-መጽሐፍ ጥመርታው ምን ያህል ነው?

____________

36. እጥረት ካለ ለእጥረቱ መፍትሔ ይሆናል ብላችሁ የምትሠሩት አሠራር ካለ ቢገልጹልን ? ____________

37. ማዕከሉን ለማጠናከርና የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል ምን ምን እርምጃ መወሰድ አለበት ይላሉ?

____________

38. ስለማዕከሉ ሁኔታ፣ ስለማስተማሪያ መርጃ መማሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ሌላ አስተያየት ካለ? ____________

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸውና የፈረምኩት፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራ መሆኑን፣ በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎችና ምንጮችም በሙሉ የጠቆምኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ::

ስም: ጌታቸው ኮቺ

ፊርማ:

አድራሻ: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል አዲስ አበባ::

ቀን: 16/10/2000

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY